# የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከ1847 እስከ 1983

## AAUP BOOKS CURRENTLY IN PRINT

* Abebe Dinku. 2007. *A Textbook of Building Construction* Br. 40
* አሌሳንድሮ ትሪዩልዚ እና ተሰማ ታዓ:: ፲፱፻፺፬ ዓ.ም:: *የወለጋ የታሪክ ሰነዶች:- ከ1880ዎቹ እስከ 1920ዎቹ (ኢ.አ.አ.)* Br. 65.00
* አማኑኤል አብርሃም:: ፲፱፻፺፭ ዓ.ም:: *የሕይወቴ ትዝታ* Br. 32.00
* Andargatchew Tesfaye. 2004. *The Crime Problem and Its Correction*, Vol. II Br. 55.00
* Bahru Zewde. 2007. *A History of Modern Ethiopia 1855-1991 (2nd edn.)* Br. 35.00
* Bahru Zewde. 2002. *Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century*, Co-published with James Currey Publishers, Oxford & Ohio University Press, Athens Br. 40.00
* Balsvik, R. 2005. *Haile Sellassie's Students: The Intellectual and Social Background to Revolution, 1952-1974*, Co-published with Michigan State University Br. 40.00
* Crummey, D. 2000. *Land & Society in the Christian Kingdom of Ethiopia, from the Thirteenth to the Twentieth Century*, Co-published with the University of Illinois Press and James Currey Publishers, Oxford Br. 50.00
* David Turton.(ed.). 2007. *Ethnic Federalism* Br. 30
* Fekade Azeze. 1998. *Unheard Voices: Drought, Famine and God in Ethiopian Oral Poetry* Br. 20.00
* ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም:: ፲፱፻፺፫ ዓ.ም:: *ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)* Br. 60.00
* Gutt, E. and Hussein Mohammed. 1997. *Siltè-Amharic-English Dictionary* Br. 50.00
* Ketema Alemu. 2003. *Digital and Analogue Communication Systems* Br. 60.00
* ሚሊዮን ነቅንቅ:: ፲፱፻፺፪ ዓ.ም:: *ትልቋ ኢትዮጵያ፣ የብዙ ነገዶች ማህበረሰብ* a translation of Donald Levine's *Greater Ethiopia*. 2000 Br. 20.00
* Mulugeta Eteffa. 2007. *The Bitter Honey* Br. 25.00
* Rubenson, S. (ed.). 2000. *Internal Rivalries and Foreign Threats: 1869-1879, Acta Æthiopica* Vol. III, Co-published with Rutgers University Br. 50.00
* Rubenson, S. (ed.). 1994. *Tewodros and His Contemporaries 1855-1868, Acta Æthiopica* Vol. II, Co-published with Lund University Press Br. 65.00
* Taffara Deguefé. 2003. *A Tripping Stone: Ethiopian Prison Diary* Br. 40.00
* ተክለ ጻድቅ ሥራሱ:: ፲፱፻፺፱ ዓ.ም:: ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ፲፰፻፺፰-፲፱፻፷፮ ዓ.ም.
* Tsegaye Tegenu. 2006. *Evaluation of the Operation and Performance of Ethnic Decentralization System in Ethiopia: A Case Study of the Gurage People, 1992-2000* Br. 55.00
* Wolde-Ghiorgis, Woldemariam. 2004. *Principles of Electrical and Electronic Instrumentation* Br. 55.00
* Yared Amare. 1999. *Household Resources, Strategies and Food Security in Ethiopia* Br. 20.00
* Ydlibi, M. 2006. *With Ethiopian Rulers: A Biography of Hasib Ydlibi* Br. 40.00

## Forthcoming

* ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ የማይጨው ዘመቻና የጉዞው ታሪክ

**NB: All prices are at local wholesale rate.**

# የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ታ ሪ ክ

## ከ1847 እስከ 1983

ባሕሩ ዘውዴ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

1999

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ
ፖስታ ሣጥን ቁጥር፣ 1176
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ፣ ቀጥታ + 251-011-123 97 46
ፋክስ፣ + 25+1-011-124 32 91
ኢ-ሜል፣ aau.press@ethionet.et

© አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ/ባሕሩ ዘውዴ፣
፪ሺህ ዓ.ም.

መጀመሪያ በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. ታተመ
ተሻሽሎ በ፪ሺህ ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ

ገጽ

የፎቶግራፍ ዝርዝር ........ viii
የካርታ ዝርዝር ........ x
የፎቶግራፍ ምንጮች ........ xi
መቅድም (1) ........ xiii
መቅድም (2) ........ xvi
መግቢያ ........ 1

ምዕራፍ አንድ፤ ቀደምት ሁኔታዎች ........ 11

1. የኢትዮጵያ የውስጥ ሁኔታ በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ........ 11
   የሰሜን ኢትዮጵያ ግዛቶች ........ 11
   የደቡብ ኢትዮጵያ መንግሥቶችና ሕዝቦች ........ 15
   ሰሜንና ደቡብን የሚያገናኘው የንግድ መስመር ........ 20

2. የውጭ ተፅዕኖ ........ 23
   የአውሮጳውያን እንደገና ዐይናቸውን ወደ ኢትዮጵያ ማቅናት ........ 23
   የግብፅ መስፋፋት ........ 24

ምዕራፍ ሁለት፤ አንድነትና ነፃነት (1847-1888) ........ 27

1. የመጀመሪያው ሙከራ፤ ካሣ-ቴዎድሮስ ........ 27
   ቴዎድሮስና ዘመናዊ ሥልጣኔ ........ 31
   ቴዎድሮስና የውጭ አገር ሰዎች ........ 37
   የቴዎድሮስ ፍጻሜ ........ 42
2. አዲስ ያንድነት ስልት ........ 46
3. የውጭው አደጋ መባባስ ........ 53
   ጉንደትና ጉራ፤ሰላም ያልተገኘበት ድል ........ 56
4. መተማ፤ የሞት ጉዳና ........ 60
5. የዘመናዊት ኢትዮጵያ መመሥረት ........ 65
   የመስፋፋቱ ሂደት ........ 67
   የአዲስ አበባ ልደት ........ 75
   ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ፤ «ክፉ ቀን» (1880-1884) ........ 78
2. የውጭ አደጋ መወገድ ........ 80
   የአድዋ ዘመቻ ........ 85

ምዕራፍ ሦስት፤ ከአድዋ እስከ ማይጨው (1888-1928) ........ 89

1. የአድዋ ድል በታሪክ ያለው ሥፍራ ........ 89
2. የማኅበረ-ኤኮኖሚያዊው ሥርዓት ........ 94
   የትርፍ ምርት ማካበቻ ስሌት ........ 94
   ንግድ ........ 102

## ማውጫ

ገጽ


የሞኖፖል ውሎች (ኮንሴሽን) ........ 108
ዘመናዊ ትምህርትና የለውጥ ፈላጊ ምሁራን መብቀል .... 112
3. የፖለቲካ ሁኔታዎች ........ 120
ዘመነ መደላደል (1888-1898) ........ 120
የሥልጣን ትግል (1900-1923) ........ 124
የወራሴ መንግሥት ጥያቄ ........ 124
ዘመነ ኢያሱ ........ 131
በፍጹማዊ ሥልጣን ጎዳና (1909-1923) ........ 139
የፍጹማዊ አገዛዝ መመሥረት (1923-1928) ........ 150

ምዕራፍ አራት፤ የኢጣልያ ወረራ (1928-1933) ........ 159

1. ጦርነት ........ 159
2. የኢጣሊያ አገዛዝ ........ 169
3. የአርበኞች ትግል ........ 174

ምዕራፍ አምስት፤ ከነፃነት እስከ አብዮት (1933-1966) ........ 187

1. ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ........ 187
የእንግሊዝ የበላይነት ዘመን ........ 187
ኢትዮጵያና አሜሪካ ........ 192
2. የማኅበረ-ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ ........ 198
እርሻና የመሬት ይዞታ ........ 199
ንግድና ኢንዱስትሪ ........ 205
3. የፍጹማዊ አገዛዝ መጠናከር ........ 209
ንጉሠ ነገሥቱ ........ 209
መኳንንቱ ........ 213
የተሻሻለው የ1948 ሕገ መንግሥት ........ 216
የጭቆና አውታር ........ 218
4. ተቃውሞ ........ 219
አድማዎች ........ 220
የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ........ 222
የገበሬዎች አመፅ ........ 225
ኤርትራ፤ ፌዴሬሽን፣ ውህደትና የመገንጠል ጥያቄ ........ 229
የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ........ 231

ምዕራፍ ስድስት፤ አብዮትና መዘዙ ........ 237

1. ሕዝባዊ አመፅ ........ 238
2. አዝጋሚው መፈንቅለ መንግሥት ........ 241
3. ወታደራዊ አገዛዝና ባላንጣዎቹ ........ 246
4. ደርግ በማርክሳዊ ርዕዮት ጎዳና ........ 254
5. «ከኋድ መንግሥቱ አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!» ........ 260
6. ፍፃሜ ........ 268
ብሔርተኛ አመፅ ........ 269




## ማውጫ

ገጽ


የኤኮኖሚ ቀውስ ........ 274
ግላስኖስትና ፔሬስትሮይካ ........ 275
የመጨረሻው ሰዓት ........ 276

መደምደሚያ ........ 281
ዋቢ መጻሕፍት ........ 287
ዝርዝር ማውጫ ........ 299

# የፎቶግራፍ ዝርዝር


ገጽ

1.1 ሐረር ከተማ በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ........ 20
2.1 «ሴባስቶፖል» የተባለው የዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ በመቅደላ አቀበት ላይ ሲጎተት ........ 30
2.2 የአፄ ቴዎድሮስ እስረኞች ........ 43
2.3 ደጃች ካሣ ምርጫ (የኋላው ዐፄ ዮሐንስ) ........ 47
2.4 የጐጃሙ ገዥ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ........ 49
2.5 የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ እንግዳ ........ 52
2.6 የምፅዋ ወደብ በ19ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ላይ ........ 62
2.7 የሌቃ ነቀምቴው ገዥ ደጃች ገብረ እግዚአብሔር (ኩምሳ) ሞሮዳ .. 68
2.8 የጅማው ገዥ ዳግማዊ አባ ጅፋር ........ 69
2.9 የሐረሩ ገዥ ዐሚር አብዱላሂ ........ 69
2.10 የወላይታ ንጉሥ ካዋ ጦና........ 70
2.11 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክና ከዘመኑ መኳንንት ጥቂቶቹ ........ 71
2.12 የከፋው ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ........ 74
2.13 ከእንጦጦና ከአዲስ አበባ በፊት የሸዋ ነገሥታት መዲና የነበረችው አንኮበር ........ 75
2.14 አራዳ የአዲስ አበባ የንግድ ማዕከል፣ 1928 ........ 77
2.15 የትግሬው ገዥ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ........ 86

3.1 ገባርና ልጁ፣ ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ ........ 96
3.2 የውጭ አገር ጎብኝዎች ድርጎ ሲቀበሉ ........ 97
3.3 ደጃች (ኋላ ራስ) ደምስ ነሲቡ፣ የወለጋ ገዥ ........ 98
3.4 ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል ........ 99
3.5 መሐል አዲስ አበባ (የኋላው ፒያሣ)፤ 1927 ........ 103
3.6 ከፈረንሣይ ለመጣ የልዑካን ቡድን የክብር ግብዣ በተደረገበት ወቅት ........ 104
3.7 የድሬዳዋ ባቡር ጣቢያ ........ 110
3.8 የአበሻ ባንክ፣ አዲስ አበባ ........ 111
3.9 በ1903 ወደ አውሮጳ የሄደው የልዑካን ቡድን ........ 113
3.10 ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ (ዶ/ር ቻርልስ ማርቲን) ........ 114
3.11 ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ቀንጮ ምሁር ........ 116
3.12 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣ ደራሲና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ........ 116
3.13 ተፈሪ መኰንን ት/ቤት በተቆረቆረበት ዘመን ........ 117
3.14 የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ተማሪዎች ........ 118
3.15 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ........ 121
3.16 ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል፣ የሐረር ገዥ በ1897 ወደ ኢትዮጵያ ከመጣው የጀርመን ልዑካን ቡድን ጋር ........ 122
3.17 ልጅ ኢያሱ ከአባቱ ከራስ ሚካኤል ጋር ........ 127
3.18 እቴጌ ጣይቱ ብጡል ........ 128
3.19 ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር፣ የአድዋ ገዥ ........ 129
3.20 አቡነ ማቴዎስ፣ ለ38 ዓመታት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ........ 130
3.21 ከሳሽና ተከሳሽ አብሮ የሚታገትበት የቁራኛ ሥርዓት ........ 133
3.22 ሌባ ሻይ፣ ተጠርጣሪውን ለማደን በዝግጅት ላይ ........ 134
3.23 ነጋድራስ (ኋላ ቢትወደድ) ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና «ጠቅላይ ሚኒስትር» ........ 137
3.24 ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ........ 138
3.25 ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ የጦር ሚኒስትር ........ 142
3.26 ደጃች ባልቻ ሳፎ፣ የአድዋ ጀግናና የተፈሪ መኰንን ቀንደኛ ባላንጣ ........ 143
3.27 በ1920 በራስ ተፈሪ ላይ ያመፀው ደጃች አባውቃው ብሩ ........ 144
3.28 ራስ ጉግሣ ወሌ፣ የንግሥት ዘውዲቱ ባልና የበጌምድር ገዥ ........ 145
3.29 የአንቾም ጦርነት በሰዓሊ ዐይን ሲታይ ........ 148
3.30 ለመጀመሪያው ፓርላማ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንግግር ሲያደርግ ........ 153
3.31 የ1923ቱ ሕገ መንግሥት አርቃቂ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ........ 154
3.32 የጎጃሙ ገዥ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ........ 155
3.33 የትግሬው ገዥ ደጃች (ኋላ ራስ) ሥዩም መንገሻ ........ 156
3.34 የክብር ዘበኛ ጦር፣ 1928 ........ 158

4.1 በራስ ሙሉጌታ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ከባድ ሽንፈት ያየበት የአምባ አራዶም ኮረብታ ........ 164
4.2 የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ ይገዙ ........ 165
4.3 ወደ ኦጋዴን ግንባር የሚዘምት ወታደር ዘመዶቹን ሲሰናበት ........ 166
4.4 ስመ ጥሩው አርበኛ ራስ አበበ አረጋይ ........ 174
4.5 የሸሬ የጦር ግንባር አዛዥና የጥቁር አንበሳ ጦር መሪ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ........ 177
4.6 የደቡብ ጦር ግንባር አዛዥ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው ........ 178
4.7 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከመጣሉ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ........ 180
4.8 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከተጣለ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ........ 181
4.9 አዲስ ዓለም የነበረው የኢጣልያ ምሽግ እንዲሰበር ከፍተኛ ሚና የተጫወተችው ስመ ጥሩዋ የውስጥ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ........ 182
4.10 የጥቁር አንበሣ ድርጅት ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓለመ ወርቅ በየነ ........ 184

5.1 የአሜሪካ የጦር ሠፈር በቃኘው (አሥመራ) ........ 194
5.2 የጭነት ከብቶችና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዲ.ሲ. 3 አውሮፕላን ሜዳውን ሲሻሙ ........ 196
5.3 ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ........ 210
5.4 ከ1933 እስከ 1948 ባለው ጊዜ ሥልጣኑ ገኖ የነበረው ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ........ 214
5.5 ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው፣ ደራሲና ጠቅላይ ሚኒስትር ........ 215
5.6 ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ........ 215
5.7 ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ የክብር ዘበኛ ጠቅላይ አዛዥ ........ 219

*Bringing Africa Together: The Story of Ethiopian Airlines*. Addis Ababa, 1988: 5.2.
ሕዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ:: *የሕወኃት ሕዝባዊ ትግል*:: አዲስ አበባ፣ 1992: **6.8**

# *መቅድም*

***A History of Modern Ethiopia*** የተሰኘው መጽሐፍ በ1984 ታትሞ ገበያ ላይ ከዋለ ጀምሮ ተወዳጅነት እንዳላጣ የሚያመለክቱ ሁለት ሁኔታዎች አሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በብዛት እየተሸጠ ነው:: ሁለተኛ ደግሞ እዚህ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ሳይሆን በውጭ በተለይ በአሜሪካ ሀገር በርከት ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በማስተማሪያ መጽሐፍነት ግልጋሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ይሁን እንጂ በውጭም ሆነ ባገር ውስጥ መጽሐፉን ገዝተው ሲያነቡ የሚታዩት በአያሌው የውጭ ሀገር ሰዎች ናቸው:: ለዚህም አንዱ ምክንያት መጽሐፉ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መዘጋጀቱ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ ግን የታሪኩ ዋና ባለቤት የሆነው ኢትዮጵያዊ ዜጋ መጽሐፉን አንብቦ ካልደገፈውም ሆነ ካልነቀፈው ግቡን መቷል ለማለት እጅግ ያዳግታል::

ስለዚህም ነው ይህን መጀመሪያ በእንግሊዝኛ የጻፍኩትን መጽሐፍ ወደ አማርኛ እንድመልስ የተነሳሳሁት:: ትውልዳችን ሐሳቡን ባገሩ ቋንቋ ከማስተላለፍ ይልቅ በእንግሊዝኛ ወይም በሌላ የውጭ ቋንቋ ማስተላለፍ እንደሚቀለው ሁላችንም የምናውቀው ነገር ነው:: ባገር ቋንቋ ሐሳብን ለሕዝብ የማስተላለፉን ተግባር በዕድሜ ለቀደሙን ምሁራን ትተነዋል:: አንዱም ይህን የትርጓሜ ሥራ እንድጀምር ያስገደደኝ የነሱ አግባብ ያለው ወቀሳ ነው:: በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነቱን እንደገና እንዲመረምር በተገደደበት ባሁኑ ጊዜ ሙያችን የታሪክ ምርምር የሆነ ምሁራን ያገኘነውን መረጃና የደረስንበትን ድምዳሜ ለሕዝቡ በቀላሉ በሚገባው ቋንቋ የማስተላለፍ ግዴታ አለብን ብዬ እገምታለሁ::

መፈለግና መወጠን አንድ ነገር ነው፤ መፈጸም ደግሞ ሌላ:: መተርጎሙ የመጻፉን ያህል አስቸገረኝ ለማለት አልደፍርም:: ይሁን እንጂ ቀላል አልነበረም:: በመጀመሪያ የጊዜ ችግር ነበር:: የትርጉሙ ሥራ የዓመት ዕረፍት (ሳባቲካል) ባገኘሁበት ዘመን በ1985 የመጀመሪያዎቹ ወራት በእንግሊዝ አገር በኦክስፎርድ ተጀመረ:: ፍጹም ፋታ ያገኘሁበት ጊዜ በመሆኑም በጥቂት ወራት ውስጥ አብዛኛውን ሥራ ማከናወን ቻልኩ:: ይሁን እንጂ ዕረፍቴን ጨርሼ ከተመለስኩ በኋላ የማስተማርና ኋላም ያስተዳደር ጫና ስለበዛብኝ የተረፈውን ሥራ ለማገባደድ ከበፊቱ የበለጠ ጊዜ ወሰደብኝ::

ሌላው ብዙ ጊዜ የጠየቀው ዘመኖቹን ከአውሮጳ ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር መለወጡ ነው:: በትምህርትና ምርምር ዓለም እንደዋዛ የምንወረውረውን ዓመተ ምሕረት በኢትዮጵያ አቆጣጠር አቻውን ለማግኘት ወሩንና አንዳንዴም ቀኑን ጭምር ማወቅ አስፈላጊ ነበር:: ይህም ራሱን የቻለ አንድ የምርምር ሥራ የሚጠይቅ ሆነ:: እ.ኤ.አ. እያሉ ማለፉ ቀላል ነበር:: ግን ትረካውን ጉራማይሌ ማድረጉ ለደራሲውም ሆነ ላንባቢው የማይመች በመሆኑ አድካሚውን መንገድ ከመከተል ሌላ አማራጭ አልነበረም::

የአተረጓጎሙ ስልት ከሞላ ጎደል ቃል በቃል ሲሆን የእንግሊዝኛው የአስተሳሰብ ዘይቤ አማርኛውን አለቅጥ እንዳልተጫነው ተስፋ አደርጋለሁ:: አልፎ አልፎም አንዳንድ በእንግሊዝኛው ዝግጅት ያልወጡና ቢወጡም ለዛቸው

ሊጠፉ ይችል የነበሩ የአማርኛ ሰነዶችን በስፋት ጠቅሻለሁ:: በእንግሊዝኛው ዝግጅት ከፍተኛ ተወዳጅነት ያገኙትን ፎቶዎች ግን እንዳሉ አገባባቸውንም ሳልለውጥ በአማርኛውም እንዲወጡ አድርጌያለሁ:: የተጨመረ አንድ ዋና ፎቶ ቢኖር የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ነው:: የጊዜውን ሁኔታ በቅጡ ባለማጤን የቀድሞውን ንጉሠ ነገሥት አንድ ፎቶ በመንሣቴ ተወቅሼ ነበር:: እኔ ግን ያኔ ላንድ ፎቶ ስል የመጽሐፉን ተስፋ ማጨለም ፍላጎት አልነበረኝም:: አሁን ግን ይህን ለማስተካከል ጊዜው ፈቅዷል::

መጽሐፉ የኢትዮጵያን የቅርቡን ዘመን ታሪክ ጥያቄዎች በሙሉ ይመልሳል የሚል የድፍረት አስተሳሰብ የለኝም:: የተሞከረው በአስተማማኝ መረጃዎች ላይ ተመሥርቶ ዋና ዋናዎቹን አጉልቶ ለማውጣትና የወደፊት የምርምር አቅጣጫዎችንም ለመተለም ነው:: በተለይም ከ1966 ወዲህ አገሪቷ ያለፈችበት ውጣ ውረድ አለመዘገቡ ቅሬታ ማሳደሩ የማይቀር ነው:: ይሁን እንጂ መጽሐፉ በእንግሊዝኛ በተዘጋጀበት ወቅት ያንን ምዕራፍ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለታሪክ ፍርድ ማቅረቡ እጅግ አዳጋች ነበር:: ለአማርኛውም የተለየ ማስተካከያ ማዘጋጀቱ አግባብ መስሎ አልታየኝም:: ወደፊት፣ ምናልባትም ብዙ ሳይርቅ ለሁለቱም አንድ የ«ማሳረጊያ» ምዕራፍ በማዘጋጀት አሻሽዬ ለማውጣት ዕቅድ አለኝ::

የአማርኛው ፍቺ አንድ ያስከተለው የራሱ የሆነ ችግርም አለ:: እንግሊዝኛ አንተና አንቱን የማይለይ ሲሆን በአማርኛ ግን በተለይ ነገሥታትን በአንቱነት መጥራቱ የተለመደ ነው:: ደራሲው ይህን ልማድ ባለመከተሉ አንዳንድ አንባቢዎችን ግር ማሰኘቱ፣ ምናልባትም ማስቆጣቱ፣ አይቀር ይሆናል:: ዐፄ ቴዎድሮስንና ምኒልክን አንተ ማለቱ በባህላችንም አልፎ አልፎ የተለመደ ነው፣ በተለይ በሥነ ጽሑፋዊ አቀራረብ:: ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ግን አንተ ማለቱ በዘመኑ ላደገ ሰው ወደዘለፋነት ያጋደለ መስሎ ነው የሚታየው:: ነገሩ ከባድ ቢሆንም የዚህን መጽሐፍ ተዋንያን ትንሽ ትልቅ ሳልለይ በአንተታ አቅርቤያቸዋለሁ:: ለዚህም ያለኝ ምክንያት ቀደም ሲል በውይይት መጽሔት (ሴሪ.3፣ ቅፅ. 2፣ ቁ.1) ካቀረብኩት ያልተለየ በመሆኑ እሱኑ ልጠቅስ እወዳለሁ፤

> ... በታሪክ መድረክ ሚናቸውን ተጫውተው ያለፉ ሰዎች እንደ ተውኔት ገፀ ባሕርያት ናቸው:: ስለሆነም የዕለት ተዕለት ሰብአዊ ግንኙነቶችም ሆኑ በመሪና ዜጋ መካከል ያለው ግንኙነት ሕሊናችንን ሳይጫነው መርምረናቸው ልንፈርድባቸውም ሆነ ልንፈርድላቸው ይገባል:: ሁለተኛ ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው አንዱን አንቱ ሌላውን አንተ ብሎ ከመተረክ ለመዳንም ይህኛ ውን አጻጻፍ የተሻለ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::

በርግጥም ያማርኛን መጻሕፍት አገላብጦ ያየ ሰው ሰዎችን «አንተ» ወይም «አንቱ» ለማለት አንዳችም ሥርዓት አለመኖሩን ይረዳል:: «አንተታ» ወይም «አንቱታ» አብዛኛውን ጊዜ የሚተረክለትን ሰው ቅለት ወይም ክብደት ሳይሆን የተራኪውን የግል ስሜት የሚያንጸባርቁ ናቸው:: ስለሆነም ያገር ሰው አንቱ፣ ባዕድ አንተ፤ የመሀል አገር ነገሥታት አንቱ፣ የዳር አገር ባላባቶች አንተ፤ መኳንንት አንቱ፣ የዝቅተኛ መደብ አባላት ደግሞ አንተ ሲባሉ



እናስተውላለን:: ስለዚህ ምርጫው ወይ ሁሉንም አንቱ ወይ ሁሉንም አንተ ማለት ነው:: እኔ የኋለኛውን መርጫለሁ::

በእንግሊዝኛው ቅጂ እንደጠቀስኩት ሁሉ ለምርምር ሥራዬ አመቺ ሁኔታ የፈጠሩልኝን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ክፍለ ትምህርትን፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋምንና የምርምርና ኅትመት ቢሮን እንደገና ላመሰግን እወዳለሁ:: በተመሳሳይም የመጀመሪያውን ቅጅ አንብበው ማሻሻያ ሐሳብ ለሰጡኝም ሆነ በተለያየ መንገድ የሞራልም ሆነ የማቴሪያል ድጋፍ ለቸሩኝ እንደገና ስማቸውን ባልዘረዝርም ምስጋናዬ ይድረሳቸው::

በተለይ የአማርኛውን ትርጉም ሳዘጋጅ የትርፍ ጊዜዋን በመሰዋት ረቂቁን በኮምፒዩተር ተይባ ለሕትመት ያበቃችው ወ/ሮ ዓለምፀሐይ ዘውዴ ትልቅ ባለውለታዬ ነች:: እንዲሁም ሥራውን ለማጠናቀቅ ላተጉኝና የመጨረሻውን ረቂቅ አይተው አቀራረቡን እንዳሻሽል ለረዱኝ ለቀድሞውና ለአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ኃላፊዎች ለዶ/ር አምሳሉ አክሊሉና ለፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ጥልቅ ምሥጋናዬ ይድረሳቸው::

በመጨረሻም፣ የምርምር ሥራዬ አስገድዶኝ በቂ ጊዜ ባልሰጣቸውም ይህንኑ በትዕግሥት በመቻል የሞራል ብርታት ለሚሰጡኝ ለባለቤቴ ለመሰንበት ሽንቁጤና ለልጆቼ ካሌብና ጽዮን ባሕሩ ምስጋናዬን ለመግለጽ ይህን መጽሐፍ አበርክቸላቸዋለሁ::

ባሕሩ ዘውዴ
ጥቅምት 1989
አዲስ አበባ

# የሁለተኛው እትም መቅድም

መጀመርያ በእንግሊዝኛ ከተጻፈ በኋላ ወደ አማርኛ ተመልሶ በ1989 የታተመው ይህ መጽሐፍ፣ የመጀመርያው እትም ተሸጦ አልቆ ከገበያ ከወጣ ብዙ ዓመታት አስቆጥሯል፡፡ የዚያን ጊዜ በጻፍኩት መቅድም ውስጥ የአብዮቱ ዘመን ባለመካተቱ ሊሰማ የሚችለውን ቅሬታ በሚከተለው መንገድ ገልጬው ነበር፤

> … ከ1966 ወዲህ አገሪቷ ያለፈችበት ውጣ ውረድ አለመዘገቡ ቅሬታ ማሳደሩ የማይቀር ነው፡፡ ይሁን እንጂ መጽሐፉ በእንግሊዝኛ በተዘጋጀበት ወቅት ያንን ምዕራፍ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለታሪክ ፍርድ ማቅረቡ እጅግ አዳጋች ነበር፡፡ ለአማርኛውም የተለየ ማስተካከያ ማዘጋጀቱ አግባብ መስሎ አልታየኝም፡፡ ወደፊት፣ ምናልባትም ብዙ ሳይርቅ ግን ለሁለቱም አንድ የ«ማሳረጊያ» ምዕራፍ በማዘጋጀት አሻሽዬ ለማውጣት ዕቅድ አለኝ፡፡

ይህ እትም ዘግይቶም ቢሆን ያን የተገባውን ቃል ለማክበር የተዘጋጀ ነው፡፡ የዘገየበት ዋነኛ ምክንያት በመሓሉ ረጅም ዘመን የደከምኩበትን የቀድሞ ምሁራን ታሪክ ጨርሼ ለማሳተም ሙሉ ትኩረቴን ወደዚያ በማድረጌ ነበር፡፡ አሁን እነሆ የእንግሊዝኛው ቅጂ ሁለተኛው እትም ተሻሽሎና ተስፋፍቶ በመውጣቱ ይህንን የአማርኛ ቅጂም ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች አወዛጋቢ የሆነውን የቅርብ ዘመን ታሪክን ለመጻፍ አይደፍሩም፡፡ ይህም በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንዱ ገና ትኩሳቱ ያልበረደለትን የታሪክ ሂደት ሚዛናዊ በሆነ መልክ መተረኩም ሆነ መገምገሙ ኀሊናን በብርቱ የሚፈትን በመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ ለታሪኩ በዋቢነት የሚያገለግሉት ሰነዶችም ገና ለሕዝብ ክፍት አይሆኑም፡፡ አሁን እነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል ባይባሉም ተቃለዋል፡፡ የደርግ ሥርዓት ስላለፈ፣ ለታሪክ ፍርድ የሚቀርብበት ጊዜ መጥቷል፡፡ ምንም እንኳ የደርግ ሹማምንት የፍርድ ቤት ሂደት ገና ያልተጠናቀቀ ቢሆንም የአብዮቱ ዘመን ትኩሳት በርዷል፡፡ በተጨማሪም፣ የአብዮቱን ዘመን አስከትሎ አያሌ መጻሕፍት ተጽፈዋል፤ ብዙ የግል ትዝታዎችም ይፋ ሆነዋል፡፡ ስለሆነም ነው የዚህኛው እትም ዋነኛ መለዮ የሆነው ስድስተኛው ምዕራፍ ሊጻፍ የቻለው፡፡

ይህ ማለት ግን ይህ ምዕራፍ የአብዮቱን ዘመን ውስብስብ ገፅታ በምልኣት ይተርካል ማለት አለመሆኑን ከማንም በላይ የምገነዘበው እኔው ራሴ ነኝ፡፡ ዘመኑ ወሳኝ፣ መረጃውም ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ የሚሄድ ቢሆንም፤ የመጽሐፉን ጠቅላላ ሚዛን ሳለማፋለስ ስል በተወሰነ ርዝመት ማቀብ ነበረብኝ፡፡ ዞሮ ዞሮ የአብዮቱ ዘመን ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት ውስጥ አሥራ ሰባት ዓመት ብቻ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም፡፡

በዚህ አጋጣሚ፣ የስድስተኛውን ምዕራፍ ረቂቅ አይተው አስተያየት ለሰጡኝ ለሥራ ባልደረቦቼ ለተባባሪ ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለና ለፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ምስጋናዬን ልገልፅ እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም ለአማርኛው ትርጓሜ መነሻ የሆነውን የእንግሊዝኛውን ቅጂ ፈጥኜ እንዳዘጋጅ ላተጋኝ የጀምስ ከሪ አሳታሚዎች ዳይሬክተር ደግላስ ጆንሰንና አሁንም እንደ በፊቱ ፎቶዎቹን በማዘጋጀት ለረዳኝ ታማኝ ወዳጄ ደኒ ዠራር ጥልቅ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ባሕሩ ዘውዴ
ጥቅምት 1999
አዲስ አበባ

# መግቢያ

ኢትዮጵያ ግዛታዊ ቅርጺ አንዴ እየጠበበ ሌላ ጊዜ እየሰፋ ለረጅም ጊዜ የኖረች በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ የምትገኝ ሀገር ናት:: ይህ ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪቃ ክፍል በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአፍሪቃ ቀንድም ተብሎ ይታወቃል:: ይህን ስያሜ ያገኘበትም ምክንያት ግልጽ ነው:: ኢትዮጵያና የምሥራቅ አጎራባች አገሮቿ ሱማሊያና ጂቡቲ የሚገኙበት ይህ ክፍለ አህጉር እንደ ቀንድ ሹሎ የወጣ ቀይ ባሕርንና የሕንድ ውቅያኖስን የሚያለያይ የምድር አካል በመሆኑ ነው:: የኢትዮጵያ ሌሎቹ ዋና አጎራባች አገሮች በስተምዕራብ የምትገኘውና ረጅም ድንበር የምትጋራዋ ሱዳን ስትሆን፣ በስተሰሜን ኤርትራ በስተደቡብ ደግሞ ኬንያ ያዋስኗታል::* እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በውጭ ሀገር፣ በተለይም በእንግሊዝኛ ጸሐፊዎች ዘንድ፣ ኢትዮጵያን አቢሲኒያ በሚለው ስያሜ መጥራቱ የተለመደ ሆኖ ቆይቶ ነበር:: ኢትዮጵያውያንም ቢሆን በተለይም እርስ በርስ በሚነጋገሩበት ጊዜ አበሻ የሚለውን ስያሜ መጠቀማቸው እስካሁንም ያለ ነገር ነው:: በገላጭ ቅጽልነቱም ኢትዮጵያዊ ከሚለው ይበልጥ ተመራጭ ሆኖ እናገኘዋለን:: «የሐበሻ መድኃኒት»፣ «የሐበሻ ምግብ»፣ የመሳሰሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል:: ሐበሻ ወይም በውጭ ትርጓሜው አቢሲኒያ የሚለው ቃል ከክርስቶስ ልደት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኙ ከነበሩት ነገዶች የአንዱ መጠሪያ ነበር ተብሎ ይገመታል::

ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ መሠረቱ ግሪክ ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት በውል ከታወቀችው ከግብፅ በስተደቡብ የሚገኘው የአፍሪቃ ክፍል የሚጠራበት አጠቃላይ ስም ነበር:: ይሁንና ከክርስቶስ ልደት በኋላ አገባቡ ጠበብ እያለ አሁን ኢትዮጵያ የምትገኝበት አካባቢ መጠሪያ ለመሆን በቃ:: ስያሜውን ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ በጠበበና እስካሁንም ቋሚ በሆነ መልኩ የምናገኘው በ4ኛው ምእተ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስትናን እምነት የተቀበለው የአክሱም ንጉሥ ዔዛና በድንጋይ ላይ ባስቀረፀው አንድ ጽሑፍ ላይ ራሱን የኢትዮጵያ ንጉሥ ብሎ ሲጠራ ነው:: ከዚያም በተከታታዮቹ ምእተ ዓመታት በጊዜው በተጻፉ ጽሑፎች አክሱም የኢትዮጵያውያን ከተማ፣ አፄ ካሌብ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ንጉሥ ተብለው ሲጠቀሱ ስናይ ስያሜው ቋሚ መልኩን እየያዘ መምጣቱን እንረዳለን:: በ14ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ ላይ የተጻፈው ክብረ ነገሥት የተሰኘውና ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ያደረገችውን ጉዞ የሚያትተው መጽሐፍም ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ የአሁኒቱ ኢትዮጵያ ካለችበት ግዛት ጋር ያለውን መያያዝ ይፋ (ኦፊሲዬል) አድርጎታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት መደበኛ መጠሪያቸውም «ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» ወይም «ንጉሠ ኢትዮጵያ» ሆኖ ቆይቷል::

የአሁኒቱ ኢትዮጵያ ከሜሪዲያን መሥመር በስተምሥራቅ በ$33^0$ እና $48^0$ እንዲሁም ከምድር መቀነት (ኢክዌተር) በስተሰሜን በ$3^0$ እና $15^0$ መካከል ትገኛለች:: በምድር መቀነት አካባቢ በመገኘቷ በቅጡ ለማያውቋት የውጭ ሰዎች የፀሐይ ሐሩር የጠነከረባት አገር መስላ ትታያቸዋለች:: ይሁን እንጂ አብዛኛው

---

* ይህ እዚህ የተገለጸው የኢትዮጵያ ድንበርና የጎረቤቶቿም አሰላለፍ መጽሐፉ በተጻፈበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ እንጂ የቀድሞውንም ሆነ የወደፊቱን ሁኔታ አያመለክትም:: ያለንበት የታሪክ ወቅት የአፍሪቃ ቀንድ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የዓለም መንግሥታትን ይዞታና ድንበር ደፍረን ለመናገር የማንችልበት ሆኗል::

የኢትዮጵያ ክፍል ደጋማ በመሆኑ በተመሳሳይ የምድር ቀጣና ከሚገኙት አብዛኛ ዎቹ የአፍሪቃ፣ የእስያና የአሜሪካ አገሮች የቀዘቀዘ አየር አጎናጽፏታል:: ስለሆነም እንደ ኢትዮጵያ ዓመቱን ሙሉ በተመጣጣኝ የአየር ጠባይ የታደሉ አገሮች እጅግ ጥቂቶች ናቸው:: እንደ ተቀረው ዓለም በክረምት ሰው ሠራሽ ሙቀት፣ በበጋ ሰው ሠራሽ ማቀዝቀዣ አያስፈልጋትም::

የአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ዓይነተኛ መልክአ ምድር በአያሌ የወንዝ ሸለቆዎች የተለዩ ከረብታዎች የሚገኙበት ደጋማ ወለል ነው:: ከነዚህም ሸለቆዎች ዋነኛው ታላቁ የስምጥ ሸለቆ ነው:: ይህ ሸለቆ ከመካከለኛው ምሥራቅ ተነስቶ፣ የቀይ ባሕርን ሰንጥቆ፤ የኢትዮጵያን ደጋማ አካል ከሁለት ገምሶ ወደ ኬንያና ከዚያም አልፎ ወደ ታንዛኒያ ይዘልቃል:: የኢትዮጵያ ዋነኛው የደጋ ክፍል ከዚህ ሸለቆ በስተምዕራብ ይቀራል:: የሀገሪቱ ከፍተኛ ተራራ የሆነው ራስ ዳሽን (4620 ሜ) የሚገኘውም በዚሁ ክፍል ነው:: ከስምጥ ሸለቆ በስተምሥራቅ የሚገኘው ክፍል ደግሞ የባሌ፣ የአርሲ፣ የሲዳሞ፣ የሐረር ደጋማ ሥፍራዎች የሚገኙበት ነው:: ከሀገሪቱ የደቡብ ምዕራብ ጫፍ በስተቀር የሀገሪቱ ደጋማ ክፍል ዙሪያውን በቆላማ ስፍራዎች የታጠረ ነው ማለት ይቻላል:: በአጠቃላይም የደጋው ክፍል ወደ ቆላው ዝግ ብሎ የሚቆለቆል ሲሆን በስተሰሜን ምሥራቅ ግን ይህ ሽግግር የገደልነት ባሕርይ አለው::

የሰሜኑ ደጋማ ሥፍራዎች አምባ ተብለው የሚታወቁ ኮረብታዎች የሞሉበት ነው:: እነዚህ አምባዎች በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ዓይነተኛ የሆነ ሚና ተጫውተዋል:: ለወህኒነት ተመርጠዋል (እንደ አምባ ግሼን ወይም አምባ ወህኒ)፤ ታላላቅ ጦርነቶችም ተካሂደውባቸዋል (እንደ አምባ አላጌ በ1888 እና እንደ አምባ አርዓዶም በ1928):: በኢትዮጵያውያን አሰያየም የሀገሪቱ ክፍሎች እንደ ከፍታቸው መጠን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ:: እነሱም ደጋ፣ ቆላና ወይና ደጋ ናቸው:: የመጀመሪያው ከፍታና ብርዳማነትን፣ ሁለተኛው ደግሞ ዝቅታና ሞቃትነትን ሲያመለክቱ አብዛኛውን የሀገሪቱን ክፍል ያቀፈው ወይና ደጋው ደግሞ የሁለቱ አማካይነትን ያመለክታሉ:: ይሁን እንጂ ከረጅም ጊዜ አጠቃቀም በኋላ እነዚህ ስያሜዎች የከፍታና የአየር ሁኔታ መግለጫ ስያሜ ከመሆንም ባሻገር የባሕርይና የአኗኗር ስልት መግለጫዎችም ለመሆን በቅተዋል::

የሀገሪቱ ወንዞች በአራት ዋና መደቦች ይከፈላሉ:: የመጀመሪያው መደብ ተከዜን፣ ዐባይን፣ ባሮን ያቀፈ ሲሆን እነሱንም አንድ የሚያደርጋቸው በሙሉ ወደ ምዕራብ ፈሰው ከትልቁ የዐባይ ወንዝ ጋር መገናኘታቸው ነው:: ከነዚህ ከሦስቱ በጣም ዝነኛ የሆነው ዐባይ ነው:: ብዙ ዘፈኖች ተደርሰውለታል:: ብዙ ተረቶችና ወጎችም እሱን መነሻ አድርገውታል:: ምንጩን የጣና ሐይቅን ለማግኘትም አያሌ የውጭ ሀገር ተጓዦች ለዘመናት ደክመዋል:: ሁለተኛው መደብ ገናሌንና ዋቤ ሸበሌን ያቀፈ ሲሆን ሁለቱም ወንዞች ወደ ሕንድ ውቅያኖስ የሚፈሱ ናቸው:: ሦስተኛው መደብ መነሻው ላይ ጊቤ፣ ወረድ ሲል ግን ኦሞ ተብሎ የሚታወቀው ወንዝ ሲሆን ኢትዮጵያና ኬንያ ወሰን ላይ ወደሚገኘው የቱርካና (ሩዶልፍ) ሐይቅ ይፈሳል:: ባራተኛው የወንዝ መደብ የሚገኘው ደግሞ አዋሽ ሲሆን ከምዕራብ ሸዋ ተራራዎች ተነሥቶ የሚሄድበትን ያጣ ይመስል ከባዘነ በኋላ የስምጥ ሸለቆን እያራሰ አፋር በረሃ ሲደርስ አሸዋ ውስጥ ገብቶ ይቀራል::



ከጣና ሐይቅ በስተቀር የሀገሪቱ ሐይቆች የሚገኙት በአብዛኛው በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ነው:: ይህን የሐይቆች ሰንሰለት በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፤ የሰሜኑ ክምችት (ዝዋይ፣ ላንጋኖ፣ አብያታ፣ ሻላና አዋሳ)፣ በመሐል የሚገኙት አባያና ጫሞ፣ በደቡብ ጫፍ የሚገኘው ቱርካና:: በተጨማሪም ደብረ ዘይት አካባቢ ከአያሌ ዘመናት በፊት በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ምክንያት የተፈጠሩ ሐይቆች ይገኛሉ:: ከነዚህም ቢሾፍቱ፣ ሆራና ራቅ ብሎ ደግሞ የዝቋላን ተራራ ሐይቅ መጥቀስ ይቻላል::

ድርቅ እየበረከተ ያፋልሰው ጀመር እንጂ የኢትዮጵያ መሬት በዓመት ሁለት ጊዜ በዝናብ ይርሳል:: ዋነኛው የዝናብ ወቅት ከሰኔ እስከ መስከረም የሚቆየው የክረምት ወራት ሲሆን፣ ይህ ምድርን እንደ ሞፈር የሚያርስ ዝናብ የሚከሰተው ከፍተኛ የአየር ግፊት ካለበት አትላንቲክ ውቅያኖስ የሚነሳ እርጥበት አዘል አየር ዝቅተኛ የአየር ግፊት በሚገኝበት የሳሃራ በረሃ ላይ በሚያደርሰው ተጽዕኖ ነው:: ይህ ዝናብ አዘል አየር ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ካጠገበ በኋላ ጉልበቱ እየቀነሰ ወደ ሰሜንና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ይዘልቃል:: ሁለተኛው የዝናብ ወቅት ከመጋቢት እስከ ግንቦት ባለው ወቅት የሚመጣው የበልግ ዝናብ ሲሆን፣ መነሻውም ከሕንድ ውቅያኖስ የሚነሳው ሞንሱን ተብሎ የሚታወቀው ነፋስ ነው:: የዝናብ ወራት ለሰብል ዕድገት ካለው ወሳኝነት በተጨማሪ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዐቢይ ሚና ተጫውቷል:: በተለይ በክረምት ወራት የወንዙ ሙላት፣ የመሬቱም ጭቃና ድጥ የማያላውስ በመሆኑ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ተግ የሚልበት ጊዜ ነበር:: ሌላው ለጦርነት መታቀብ ምክንያት በጀሌነት ይሰለፍ የነበረው ገበሬም የክረምት ወራት ወደ እርሻው መመለስ የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ ነበር::

ይህ ከላይ የተገለጸው የዝናብ ስርጭት ባገሪቱ የደን ሀብት ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል:: በስተደቡብ ምዕራብ ዓመቱን ሙሉ ማለት ይቻላል የሚጥለው ከባድ ዝናብ በዚህ አካባቢ ለሚገኙት ጥቅጥቅ ያሉ ደኖች መነሾ ሆኗል:: ምንም እንኳ በጭፍጨፋና በሐሩር ቅንብር የአካባቢው የደን ሀብት ቀድሞ ከነበረው ከዐሥር አንዱ ብቻ የተረፈ ቢሆንም፣ አሁንም ከሀገሪቱ የደን ሀብት ስድሳ አምስት ከመቶው የሚገኘው ከዚያው አካባቢ ነው:: እንደ ዝሆን ጥርስና እንደ ቡና የመሳሰሉት ከተፈጥሮ የሚገኙት የንግድ ሸቀጦችም ለረጂም ጊዜ የሚመጡት ከዚሁ አካባቢ ሆኖ ቆይቷል:: የሀገሪቱ ሰሜንና ማዕከላዊ ሥፍራዎች ቀድሞ ዘርዘር ባሉ ጫካዎችና ሣር ለበስ መሬት የተሸፈኑ ሲሆኑ አሁን ግን ወትሮ ከነበረው የደን ሀብት በእጅጉ ያነሰ ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ አካባቢዎች ለረጅም ጊዜ ብዙ ሰዎች የሠፈሩባቸውና ገናና መንግሥታት ተቋቁመው ከተሞች የተቆረቆሩባቸው በመሆናቸው ነው:: ይህ የደን ሀብት መራቆት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄዶ አሁን ኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ተመጽዋች ያደረጋትን ተከታታይ ድርቅ አስከትሏል::

በሰሜንና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የሚገኘው አማካይ የሆነ የአየር ሁኔታ ለአያሌ የእህል ዘሮች መብቀል አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል:: ከነዚህም ውስጥ ዋነኛው በሀገሪቱ ብቻ የሚበቅለው የሕዝቡ የምግብ አለኝታና የሀገሪቱም መለዮ የሆነው ጤፍ ነው:: ጤፍ ሰሜንና ማዕከላዊ ኢትዮጵያን መጋቢ የሆነውን ያህል የደቡብ ሕዝብ ዋና አሳዳሪ ደግሞ እንሰት ተብሎ የሚታወቀው ተክል ነው:: የሀገሪቱ ሰፊ የግጦሽ መሬትም በአፍሪቃ አህጉር ተወዳዳሪ የማይገኝለት የቀንድ ከብት ሀብት ባለቤት አድርጓታል:: የቀንድ ከብት ዘላን (በወቅቱ አጠራር አርብቶ

አደር) ተብለው ለሚታወቁት በቆላማ ሥፍራዎች ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ብቸኛ መተዳደሪያ ይሁን እንጂ በደጋ ሥፍራዎች ለሚገኙት በርሻ ለሚተዳደሩ ኢትዮጵያውያንም የማይናቅ ድጎማ ያበረክታል:: ላሞች በወተታቸው፣ በሬዎች ደግሞ ተጠምደው በማረስ ያገለግላሉ::

እንደ ብዙ ሌላ የአፍሪቃ ሀገሮች ሁሉ ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ የብዙ ብሔረሰቦች አገር ናት:: የቋንቋ ጠበብት እነዚህን ቋንቋዎች በአራት መደቦች ከፍለዋቸዋል:: ከነዚህም መደቦች ውስጥ ሦስቱ ሰፍሮ ሰዝያቲክ ከሚባል እናት ቋንቋ የመነጩ ናቸው:: ስሙ እንደሚያመለክተው ሁሉ የአፍሮ እስያዊ የቋንቋ ዝርያዎች በሰሜኑ የአፍሪቃ ክፍልና በደቡብ ምዕራብ እስያ የሚነገሩ ሲሆን በኢትዮጵያ የሚገኙት ደግሞ ኩሻዊ፣ ኦሞአዊና ሴማዊ የሚባል አጠቃላይ ስያሜ ተሰጥቷቸዋል:: የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የዕድሜ ቀዳሚነት ሲኖራቸው የሴማዊ ቋንቋዎች ባንፃሩ የኋላ ዘመን ናቸው::

አራተኛው የቋንቋ መደብ ከሦስቱ የተለየ ዝርያ ያለው ዐባይ ሰሐራዊ የሚባል ነው:: ይህም እንደገና ስሙ እንደሚያመለክተው በዐባይና በሳሐራ በረሃ አካባቢዎች የሚናገሩ ቋንቋዎችን ያጠቃለለ ነው:: በኢትዮጵያ የሚገኙት ዐባይ ሰሐራዊ ተናጋሪዎች፣ በማያቋርጥ ሐረግ ማለት ይቻላል፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ የሀገሪቱን የምዕራብ ድንበር ጥግ ይዘው የሚገኙ ናቸው:: ከነዚህም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፤ በደቡብ ምዕራብ ኤርትራ የሚገኙት ኩናማዎች፣ በመተከልና ምዕራብ ወለጋ የሚገኙት ጉሙዞች፣ በወለጋ የሚገኙት በርጣና ኮማዎች፣ ከደጋው አፋፍ ላይ የሚገኙት ማጃንጊሮችና የባሮ/ሶባትን ፈለግ ይዘው እስከ ሱዳን ተንሰራፍተው የሚገኙት አኙዋክና ኑዌሮች ናቸው::

ከኩሻዊ ተናጋሪዎች መካከል በአክሱም ዘመን ዐቢይ ሚና የነበራቸው አገውና ቤጃ ነበሩ:: በአሁኑ ጊዜ ግን ቤጃዎች በአብዛኛው በሱዳን ውስጥ የሚገኙ ሲሆን አገዎች የበላይነትን ባገኘው የሴማዊ ቋንቋና ባህል ተውጠው የተረፉት በጎጃምና በወሎ ከሞላ ጎደል ባንድ አውራጃ ተከልለው ይገኛሉ:: ከዚህ ዋና ከሆነው የአገው እምብርት ፈንጠር ብሎ ብለን የሚባል ቀድሞ የፈለሰ የአገው ዝርያ በኤርትራ ውስጥ በከረን አውራጃ ይገኛል:: ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ዋነኛ ኩሻዊ ተናጋሪዎች ኦሮሞዎች ሲሆኑ እነሱም በ16ኛው ምእተ ዓመት ከደቡብ ኢትዮጵያ ተነሥተው በጥቂት ዓመታት አሁን የያዙትን ስርጭት ለማግኘት በቅተዋል:: በቋንቋ በጣም የሚቀራረቧቸው ሶማሌዎች ደግሞ በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲ፣ በሶማሊያና በኬንያ ተሰራጭተው አብዛኛዎች በአርብቶ አደርነት ኑሮ ይኖራሉ:: ሌሎች ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሐሩራማ በሆነው በስምጥ ሸለቆ ሰሜን ምሥራቅ ክፍል የሚገኙት አፋሮች፣ ከነሱ በስተሰሜን በደጋው ጫፍ ላይ የሠፈሩት ሳሆዎች፣ በደቡብ ሸዋ የሚኖሩት ሀዲያና ከምባታ፣ ከዚያም ቀጥለው ያሉት ጌዴኦና ኮንሶዎች ናቸው::

ኦሞአዊ የሚለው ስያሜ የሠረፀው ከኦሞ ወንዝ ስም ሲሆን አብዛኛዎቹ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎችም በወንዙ ግራና ቀኝ የሚገኙ ብሔረሰቦች ናቸው:: እነዚህ ብሔረሰቦች በተለይ የሚታወቁት ህልውናቸው የተመሠረተው በእንሰት ተክል በመሆኑና በተለይም እንደ ዶርዜ፣ የም (ጃንጀሮ)፣ ከፋና ወላይታ ያሉት በቀድሞ ታሪካቸው የደረጀ የፖለቲካ ሥርዓት ለማቋቋም በመቻላቸው ነው::



የሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሀገሪቱ የታሪክ ሂደት ዋነኛ ተዋናይ ሆነው ቆይተዋል:: በተከታታይ በሀገሪቱ የተቋቋሙት መንግሥታትም በነሱ መሪነት የተካሄዱ ነበሩ:: በተለይም በዚህ ረገድ የትግርኛና የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቀደምት ሚና ተጫውተዋል:: አሁን በቤተ ክህነት አካባቢ የተወሰነው የግዕዝ ቋንቋ የዚህ መደብ አንጋፋ ቋንቋ ሲሆን ለሌሎች የቋንቋ መደብ ተናጋሪዎችም የወል ቋንቋ (*ሊንጉዋ ፍራንካ*) ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል:: ለግዕዝ ከሁሉም የሚቀርበው ትግረ ሲሆን የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገኙት በሰሜንና ምሥራቅ ኤርትራ ነው:: የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በኤርትራ ደጋማ ክፍልና በትግራይ የሚገኙ ሲሆን፣ የሀገሪቱ የሥራ ቋንቋ የሆነው አማርኛ ደግሞ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛ ደጋማ ሥፍራዎች የሚኖረው ሕዝብ አፍ መፍቻ ቋንቋ ነው:: በመጨረሻም በኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዙሪያውን የተከበቡ ሦስት የሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ይገኛሉ:: እነሱም አርጎባ፣ ጉራጌና ሐረሪ (አደሬ) ናቸው::

በተለምዶ፣ ንግሥተ ሳባ (አዜብ፣ ማክዳ) ወደ ሰሎሞን ንጉሠ እሥራኤል ያደረገችው ጉዞ የኢትዮጵያ ታሪክ መጀመሪያ ተደርጎ ሲወሳ ቆይቷል:: ይህ ድርጊት ተፈጸመ የተባለበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ አንድ ሺ ዓመት ግድም ነበር:: ኢትዮጵያ የሦስት ሺ ዓመት ታሪክ አላት የሚለው አነጋገርም የመነጨው ከዚሁ ክስተት ነው:: ይሁን እንጂ ይህን የንግሥተ ሳባ ጉዞ የኢትዮጵያ ታሪክ መነሾ አድርጎ ለማቅረብ ሁለት ዐበይት ችግሮች ያጋጥማሉ:: አንደኛው ንግሥቲቱ ጉዞውን ያደረገችው በርግጥም ከኢትዮጵያ ምድር መሆኑ አሻሚ ስለሆነ ነው:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ንግሥቲቱ ከምድረ ኢትዮጵያ ለመሄዷ አስተማማኝ ማስረጃ ቢገኝ እንኳ፣ የሷ ጉዞና ጉዞውም ያስከተለው የቀዳማዊ ምኒልክ መፀነስ የሥርወ መንግሥትን እንጂ ያገርን ታሪክ ልደት ስለማያበስር ነው::

እውነተኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ አጀማመር ለማወቅ የጽሑፍ መረጃዎች ብቻቸውን ብዙም አያራምዱንም:: በቅርብ ከተደረጉ የአርኪዮሎጂና የቋንቋ ምርምሮች እርዳታ መሻት ይኖርብናል:: በዚህም ረገድ በ1960ዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉት የአርኪዮሎጂ ቁፋሮዎች የታሪክ ዕውቀት አድማሳችንን ከማስፋታቸውም በላይ ዓለም አቀፍ ሳይንሳዊ ትኩረትን ወደ አገራችን ስበዋል:: በተለይም በ1967 በአፋር በረሃ፣ ሐዳር በሚባለው ስፍራ ፈረንጆች «ሉሲ» ኢትዮጵያውያን «ድንቅነሽ» ብለው የሰየሟት እንስት ሰው–መሰል ቅሪት መገኘት የሰውን ልጅ አፈጣጠር ለማወቅ ለሚደረገው ጥረት አንድ ትልቅ እመርታ ሰጥቶታል:: የዚህ ቅሪት ዕድሜ በሶስት ሚሊዮን ተኩል ዓመት የተገመተ ሲሆን፣ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ከሉሲም ቀደም ያሉ ቅሪቶች (*ሰፋረንሲስ ራሚደስ*፣ «ሰላም») በዚያው አካባቢ ተገኝተዋል:: በኦሞ ሸለቆ ደግሞ እንዲሁ ከአንድ እስከ ሁለት ሚሊዮን ዓመታት የተገመቱ የሰው ቅሪቶች ተገኝተዋል:: በጊዜ ቀረብ እያልን ስንመጣ ደግሞ ሌሎች የቅድመ ታሪክ ክስተቶች እናገኛለን፤ እነዚህም ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ አምሳ ኪሎሜትር ርቀት ላይ መልካ ቁንጡሬ የተባለው የቅርብ ጊዜ የድንጋይ ዘመን ቅርሶች የሚገኙበት ሥፍራ እና በኤርትራ፣ በትግራይ፣ በሲዳሞና በሐረር የሚገኙት የዋሻ ሥዕሎች ናቸው::

የዚህ ቅድመ ታሪክ ዕድገት አንዱና ዋና ገጽታ እንስሳትና ዕጸዋትን የማስገበሩ ሂደት ነው:: ይህ ሁኔታ የተፈጸመው የዛሬ ስድስት ሺ ዓመት ግድም ነው ተብሎ ይታመናል:: በደቡብ ኢትዮጵያ እንሰት መጋቢነቱ ታውቆ መኰትኰት ሲጀመር በሰሜን ኢትዮጵያ ደግሞ ጤፍ ከሣርነት ወደ ሰብልነት ተሸጋግሯል:: ዳጉሳም በዚህ መልክ ጥቅም ላይ መዋል ሲጀምር ዘግየት ብለው ደግሞ ስንዴና ገብስ ወደ አካባቢው ሊገቡ ችለዋል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ ታላቅ የእርሻ ቴክኖሎጂ ለውጥ ተካሂዷል:: ይኸም የደጋውን የኢትዮጵያ ክፍል ከብዙ የአፍሪቃ አገሮች የለየውና እስካሁንም የሕዝቡ ሕይወት እምብርት የሆነው በሬ ጠምዶ የማረስ ዘዴ ነው::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ክስተቶች ናቸው በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለመንግሥት ምሥረታ መነሻ የሆኑት:: የዚህ መንግሥት ምሥረታ ሂደት ማሳረጊያ የአክሱም መንግሥት ነው:: ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ላለመሆኑ፣ ማለትም እንደ አክሱም በዝርዝር ባይታወቁም ቅድመ አክሱም መንግሥታት ለመኖራቸው፣ በቂ መረጃዎች አሉ:: በተለይ ከአክሱም በስተሰሜን የምትገኘው ዬሃ የነባር ባህልና ከውጭ፣ በተለይ ከደቡብ ዐረብ፣ የመጣ የውጭ ተጽዕኖ ቅምር የሆነ የሥልጣኔ ማዕከል እንደነበረች የምርምር ግኝቶች ይጠቁማሉ:: አክሱም ራሷ የገነነችው ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከአንደኛው እስከ ሰባተኛው መቶ ዓመት ነበር:: በተለይም ስመ ጥርነትን ያገኘችው ከፍተኛ የሕንፃ ቴክኖሎጂ ጥበብን በሚያንጸባርቁት ሐውልቶቿ፣ ቤተ መንግሥቶቿና ቤተ መቅደሶቿ ነው:: በተጨማሪም የአክሱም ዘመን ከተሞች ያበቡበት ዘመን ነበር:: ከነዚህም ዋነኞቹ መናገሻ ከተማዋ አክሱምና በቀይ ባሕር ወደብነቷ ዓለም አቀፍ ዝናን ያተረፈችው አዱሊስ ነበሩ:: ንግድ፣ የአገር ውስጥና የውጭ፣ የአክሱም ደም ሥር ነበር ማለት ይቻላል:: በውጭ ንግድ አማካይነትም አክሱም የሜዲተራንያን አካባቢ ንግድና ባህል አካል ከመሆን አልፋ ከሕንድና ከሩቅ ምሥራቅ ለመገናኘት በቅታ ነበር::

ተደጋግሞ እንደሚታየው በንግድ ዱካ ግዛት ማስፋፋት ይከተላል:: የአክሱም መንግሥት እንዲሁ እጅግ በገነነበት ወቅት አብዛኛውን የሰሜን ኢትዮጵያን፣ የደቡብ ዐረብንና የቀይ ባሕር ዳርቻን በመግዛት የቀይ ባሕርን በሙሉ በቁጥጥር ስር ለማድረግ በቅቶ ነበር:: በ4ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ የአክሱሙ ንጉሥ ዔዛና የክርስትናን እምነት በመቀበል ለሀገሪቱ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ከፈተ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ የክርስትና ሃይማኖት በተለይም የኦርቶዶክስ እምነት፣ የአብዛኛው የደጋው ክፍል እምነት ከመሆኑም በላይ የባህሉ መለዮ ሊሆን በቅቷል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቡን በእስክንድርያው ፖትርያርክ እንዲሾም መደንገጉም የሀገሪቱ መንግሥትና ቤተ ክህነት በዲፕሎማሲና በርእዮተ ዓለም ለዘመናት ከግብፅ ቤተ ክህነት ጋር ተሳስረው እንዲቆዩ አድርጓቸዋል:: የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሊሰየሙ የቻሉት በ1921 ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በራሷ ፖትርያርክ መተዳደር የቻለችው ግን በ1951 ነው::

ከሰባተኛው መቶ ዓመት ገደማ ጀምሮ የአክሱም መንግሥት እየተዳከመ መጣ:: የእስልምና ሃይማኖት መነሣትና ይህም በቀይ ባሕር ንግድ ላይ ያስከተለው መዛባት የአክሱምን ሕይወት አጠወለገው:: ቀድሞ የአክሱም ነገሥታት ዘመቻዎች ዒላማ የነበሩት ቤጃዎች እየተጠናከሩ መጡ:: የአክሱም መንግሥት እየተሸማቀቀ ፊቱን ወደ ደቡብ ማዞር ነበረበት:: በዚህ ሁኔታ ነበር



እስከዚያን ጊዜ ድረስ ለአክሱም ገብረው የነበሩት አገዎች የመንግሥት ሥልጣን ጨብጠው ስማቸውን መሰል የሆነውን የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ያቋቋሙት:: የዚህ ሥርወ መንግሥት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በውል ባይታወቁም ከ12ኛ ው መቶ ዓመት ጀምሮ ሥርወ መንግሥቱ እስካበቃበት እስከ 1262 ላለው ዘመን አስተማማኝ የታሪክ መረጃዎች ይገኛሉ:: ለዛጉዌ ነገሥታት እንደ ሀውልት ሆነው ሲያስጠሯቸው የኖሩትና የሚኖሩት በላሊበላ የሚገኙት ከቋጥኝ ተፈልፍለው የታነፁት አብያተ ክርስቲያናትም የዚህ ዘመን ዐቢይ ክንዋኔዎች ናቸው::

በ1262 ይኩኖ አምላክ የሚባል የአማራ መሪ የዛጉዌን መንግሥት ገርስሶ አዲስ ሥርወ መንግሥት ለማቋቋም ቻለ:: (በዚያን ወቅት አማራ የሚለው ስያሜ እንዳሁኑ ሰፊ ሳይሆን ዛሬ ወሎ በሚባለው ክፍለ ሀገር ይኖር የነበረ ቀድሞ ለዛጉዌ ከገበሩት ሕዝቦች ያንዱ መጠሪያ ነበር):: ይኩኖ አምላክ የመሠረተው ሥርወ መንግሥት «ሰለሞናዊ» በሚል ስያሜ ይታወቅ ነበር:: ይህን ስያሜ ይኩኖ አምላክና ተከታዮቹ የመረጡት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የተወለዱት ሐቀኞቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት መሆናቸውንና ሥልጣናቸውም ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን፤ ባንፃሩም የዛጉዌ አገዛዝ ሕገ ወጥ እንደነበር ለማመልከት ነው:: ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት እስካለንበት ዘመን ቀጥሎ አፄ ኃይለ ሥላሴ በ1967 ከሥልጣን ሲወርድ ፍጻሜውን አግኝቷል:: አፄ ይኩኖ ዓምላክና ተከታዮቹ፣ በተለይም አፄ ዐምደ ጽዮን (በ14ኛው መቶ ዓመት) እና አፄ ዘርአ ያዕቆብ (በ15ኛው መቶ ዓመት)፣ ከዛጉዌ የወረሱትን ግዛት በማስፋፋት ከአክሱም መንግሥት የሚተካከልና እንዲያውም የሚበልጥ ገናና መንግሥት ለማቋቋም በቅተዋል::

በዚሁ ዘመን የክርስትና እምነት ወደ ደቡብ (የዛሬው ሸዋና) ወደ ሰሜን ምዕራብ (ጎጃምና የጣና ሐይቅ አካባቢ) ሊስፋፋ ችሏል:: ባንፃሩም በአክሱም ዘመን ፍጻሜ ላይ ጠረፍ ጠረፉ ላይ መቆናጠጥ ጀምሮ የነበረው የእስልምና እምነት ወደ መሀል አገር እየዘለቀ መጥቶ በተለይ በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀዳሚ ሥፍራ ለማግኘት በቅቶ ነበር:: መሀል አገር የተዘረጋውን የንግድ መሥመር ተከትሎም ይፋት፣ ፈጠጋር፣ ደዋሮ፣ ባሊና ሀዲያ የሚባሉ የእስላም ግዛቶች ተመሥርተው ነበር:: ለሚቀጥሉት ሁለት መቶ ዓመታት ያህል «ሰሎሞናዊውን» መንግሥትና እነዚህን የእስላም ግዛቶች ባላንጣ ያደረጋቸው ከሃይማኖት ልዩነቱም ይልቅ ከዘይላ ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተዘረጋውን ጠቃሚ የንግድ መሥመር ለመቆጣጠር ያደርጉት የነበረው ፉክክር ነው:: በ15ኛው መቶ ዓመት ላይ ፉክክሩ በክርስቲያኑ መንግሥት የበላይነት ያከተመ መሰለ:: የእስላም ግዛቶቹም ይህንኑ የበላይነት ዐውቀው እየገበሩ መኖር ጀመሩ::

ይሁን እንጂ ይህ የኃይል ሚዛን በ16ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ተለወጠ:: በ1519 አሕመድ ኢብን ኢብራሂም ወይም በተለምዶ አጠራሩ አሕመድ ግራኝ የተባለ የአዳል መሪ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ጦሩን አነሣ:: በሚያስደንቅ የጦር አመራር ስልት የራሱን መንግሥት ሊያጠፉ አኮብኩቦ የነበረውን የአፋርና የሱማሌ ሕዝብ ፍልሰት ገርቶ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ተደጋጋሚ ድሎች ተጐናጸፈ:: በ1521 ሽምብራ ኩሬ ላይ (የዛሬው ሞጆ አካባቢ) በክርስቲያኑ ንጉሥ አፄ ልብነ ድንግል ላይ የመጀመሪያውን ታላቅ ድል አገኘ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልብነ ድንግል ለዐሥራ ሦስት ዓመታት ካንድ ግዛቱ

ወደሌላው እንደተዋከበ ሕይወቱ አለፈች:: ከመሞቱ በፊት ግን የኋላ ኋላ ለግራኝ ራሱ መጥፊያ ሊሆን ያበቃውን አንድ እርምጃ ወስዶ ነበር:: ይኸውም ወደ ፖርቱጋል መልእክተኛ ልኮ እርዳታ እንዲመጣለት መጠየቅ ነው::

ከ12ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በኢየሩሳሌም ምድር የመስቀል ጦርነት (ክሩሴድስ) ተብሎ በሚታወቀው ውጊያ ከሙስሊሞች ጋር ፍልሚያ ገጥመው የነበሩት የአውሮጳ ክርስቲያኖች «ቄስ ዮሐንስ» (ፕሬስተር ጆን) የሚባል አንድ ገናና የሆነ አጋራቸው ሊሆን የሚችል የክርስቲያን ንጉሥ አለ በሚል ወሬ ስሜታቸው ተቀስቅሶ ነበር:: ይህን ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ሀብትና ገናናነትን ያጣመረ ንጉሥ ለማግኘትም አውሮጳውያን ሥራዬ ብለው ያዙ:: ብዙ ከባዘኑ በኋላ ልባቸው የኢትዮጵያ ንጉሥ ላይ አረፈ:: ፖርቱጋሎች የመጀመሪያ መላክተኛ በ15ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ ልከው ግንኙነት ከፈጠሩ በኋላ በ1512 አንድ ታላቅ የልዑካን ቡድን በመስደድ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ጥብቅ ወዳጅነት መሠረቱ:: ስለዚህም ልብነ ድንግል ጣረ ሞቱን የላከው የድረሱልኝ መልእክት ከንቱ ሆኖ አልቀረም:: ዓመት ሳይሞላው 400 የሚያህል የፖርቱጋል ጦር ሕንድ የሚያደርሰውን የባሕር ጉዞ በቀየሰው በቫስኮ ዳጋማ ልጅ በክሪስቶፈር ዳጋማ አዝማችነት የክርስቲያኑን ወገን እንዲረዳ ተላከ:: በዚህ ረዳት ጦር ታግዞም፣ በአባቱ በልብነ ድንግል እግር የተተካው ገላውዴዎስ በ1535 በወይና ደጋ ጦርነት አሕመድ ግራኝን ለማሸነፍ በቃ::

ይሁንና የዐሥራ አምስት ዓመት ተከታታይ ጦርነት ለክርስቲያኑም ሆነ ለእስላሙ መንግሥት አልበጀም:: ከዚህ ፍልሚያ በኋላ ተዳክመው በወደቁበት ወቅት ሁለቱንም እንደ ማዕበል የሚያጥለቀልቅ አንድ ከባድ የሕዝብ ፍልሰት መጣ:: ይህ የሕዝብ ፍልሰት በቅርቡ የኢትዮጵያ ታሪክ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነበር:: የኦሮሞ ሕዝብ ከደቡብ ኢትዮጵያ ተነሥቶ የግራኝ አዳል መንግሥትም ሆነ የክርስቲያኑ መንግሥት ይቆጣጠሩት የነበረውን የደጋ ክፍል አጥለቀለቀው:: የአዳል መንግሥት በኩርማን መሬት (ሐረር ከተማ) ተወስኖ እንዲቀር የክርስቲያኑ መንግሥት ደግሞ ወደ ሰሜን እንዲያፈገፍግ ተገደደ::

በዚህ ሁሉ መሐል የክርስቲያኑን መንግሥት የሚያናውጥ አንድ ሌላ ሁኔታ ተከሠተ:: መንግሥቱን ለማገዝ በመጡት የፖርቱጋል ወታደሮች ኮቴ ተከትለው የካቶሊክን እምነት ለማስፋፋት ኢየሱሳውያን የሚባሉ የእምነቱ ሐዋርያት ከ1549 ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጀምረው ነበር:: ነገሥታቱንም የካቶሊክን እምነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ብዙ ከደከሙ በኋላ በመጨረሻ በአፄ ሱስንዮስ ዘመን (1599-1625) የሠመረላቸው መሰለ:: የንጉሡ ሥልጣን እየተዳከመ፣ የመሳፍንቱ ደግሞ ባንፃሩ እያየለ መምጣቱ ያሳሰበው ሱስንዮስ ይህንኑ ችግር ይፈታልኛል ብሎ የካቶሊክን እምነት ተቀብሎ ያገሪቱ እምነት ነው ብሎ ዐወጀ:: ይሁን እንጂ ሀገሩ ዳር እስከ ዳር ስለተነሣበትና በዚሁ ሳቢያ የተነሣው የእርስ በርስ ጦርነትና የደም መፋሰስ ስላንገሸገሸው ዐዋጁን ቀልብሶ ዙፋኑን ለቀቀ:: በእግሩ የተተካው ልጁ ፋሲለደስም ሳይውል ሳያድር ኢየሱሳውያንን ከምድረ ኢትዮጵያ አባረረ::

ይህ የሆነው በ1625 ሲሆን በአራተኛው ዓመቱ ፋሲለደስ መጠሪያው የሆነችውን የጎንደርን ከተማ ቆረቆረ:: ከዚያ በፊት ለብዙ መቶ ዓመታት ነገሥታቱ እንደ ዘላን ከቦታ ቦታ እየዞሩ በድንኳን ይኖሩ ስለነበር የጎንደር እንደቋሚ መናገሻ ከተማ መቆርቆር ባገሪቱ ታሪክ ውስጥ አንድ ዐቢይ ምዕራፍ የሚከፍት ነበር:: በተለይም ለከተማይቱ ትልቅ ሞገስ የሰጣት ፋሲለደስ



የጀመረውና ተከታዮቹ የቀጠሉት የአብያተ መንግሥትና የአብያተ ክርስቲያን ማነፅ ተግባር ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ የከተማ ዕድገት የወቅቱን የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ከመሸርሸር አላዳነውም:: በ18ኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የነበረው ንጉሠ ነገሥት በትረ መንግሥት ከመጨበጡ በስተቀር ሥልጣኑ እየተዳከመ አሻንጉሊት ሆነ:: ይህ የታሪክ ዘመን ዘመነ መሳፍንት ተብሎ ይታወቃል:: የቅርቡ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ መቅድምም ይህ መሆኑ ነው::

# ምዕራፍ አንድ

# ቀደምት ሁኔታዎች

## የኢትዮጵያ የውስጥ ሁኔታ በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ

### የሰሜን ኢትዮጵያ ግዛቶች

የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን እየተዳከመ ለመምጣቱ ጉልህ የሆነ ማስረጃ በ1761 ታየ። በዚያን ዓመት የትግሬው መስፍን ራስ ሚካኤል ስሑል እስከዚያን ጊዜ ድረስ ባልታየ ድፍረት የጐንደርን ነገሥታት እንደ ጉልቻ መለዋወጥ ጀመረ። መጀመሪያ ያወኩትን የኦሮሞ ጭፍሮች እንዲከላከልለት ወደ ጎንደር የጋበዘውን አፄ ኢዮአስን ከዙፋን አውርዶ የራሱ ምርጫ የሆነውን ዳግማዊ ዮሐንስን አነገሠ። ዓመት ሳይሞላ ደግሞ ዮሐንስን አውርዶ የራሱ ምርጫ የሆነውን ዳግማዊ ተክለ ሃይማኖትን ዙፋን ላይ አስቀመጠ። ከዚህ በኋላ የንጉሠ ነገሥትነቱ ሥልጣን ከደረሰበት ቅሌት ሊያገግም አልቻለም። የራስ ሚካኤል አምባ ገነንነት ባጭሩ ቢቀጭም እሱ በቀደደው ገብቶ የየጁ ኦሮሞዎች መሪ የነበረው ዓሊ ጉዋንጉል የራሱን የመሳፍንት ሥርወ መንግሥት መሠረተ። በዘመኑ የነበረው አፄ ተክለ ጊዮርጊስም «ፍጻሜ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ» ተባለ። ከዚያን ወቅት ጀምሮ የመጨረሻው የየጁ መስፍን ዳግማዊ ዓሊ ወይም ዓሊ ትንሹ በአይሻል ጦርነት ላይ በደጃች ካሣ ኃይሉ (የኋላው ዳግማዊ ቴዎድሮስ) እስከተሸነፈበት እስከ 1845 ድረስ ያለው ዘመንም «ዘመነ መሳፍንት» ተባለ።

በዘመነ መሳፍንት ነገሥታት በተከታታይ ለወግ ዙፋን ላይ ይውጡ እንጂ ሥልጣን አልባ ነበሩ። ሥልጣን የነበረው በየጁ መሳፍንትና በሌሎች ግዛት መሳፍንት ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ይህ ነው የሚባል ሠራዊት የለውም ነበር። ወደ ዘመኑ ማብቂያ አካባቢ የዓመት ገቢው ከሦስት መቶ ማርትሬዛ ብር አያልፍም ነበር። ባንፃሩ የትግሬው መስፍን የራስ ወልደ ሥላሴ ሀብት በሰባ አምስት ሺ፣ የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በሰማንያ አምስት ሺ ይገመት ነበር።

ደብረታቦርን መዲናቸው ያደረጉት የየጁ መሳፍንት ከሥረ መሠረታቸው በብሔረ ሰብ ኦሮሞ፣ በሃይማኖት ሙስሊም ይሁኑ እንጂ ሥልጣን በያዙበት ጊዜና ከዚያም በኋላ ከአማራው የገዢ መደብ ጋር የተዋሐዱና በእምነታቸው ክርስቲያን ነበሩ። ከሌሎች መሳፍንት (ለምሳሌ ከትግሬ) የነበራቸው ቅራኔም ሥልጣንን የተመረኮዘ እንጂ ብሄረ ሰባዊም ሆነ ሃይማኖታዊ አልነበረም። ስሙ ያሳስት እንጂ ዳግማዊ ራስ ዓሊ ከባላንጣው ከደጃች ውቤ ያላነሰ የክርስትና ሃይማኖት ተቆርቋሪ ነበር። ከየጁ መሳፍንት ሁሉ ገናና ተብሎ የሚታወቀው ራስ ጉግሣ መርፅ (1796-1817) ከትግሬው መስፍን ከራስ ወልደ ሥላሴ ጋር ይፋለሙ የነበሩት አንዱ ሙስሊም ሌላው ክርስቲያን ሆነው ሳይሆን ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ እውነተኛው እምነት የትኛው ነው (ሁለት ልደት ወይስ ሦስት ልደት) በሚለው የዘመኑ አወዛጋቢ ክርክር ነበር።

የእስልምና ሃይማኖት ጠንክሮ የሚታየው ከበሽሎ በስተደቡብ በሚገኙት የኦሮሞ ግዛቶች አካባቢ ነበር:: ቀደም ብሎ አማራ፤ ከኦሮሞ ፍልሰት በኋላ ግን በአካባቢው በሰፈረው የኦሮሞ ነገድ ስም ወሎ ተብሎ ወደሚጠራው ክልል እስልምና የገባው ከግራኝ ጦርነት አስቀድሞ ነበር:: በ18ኛው መቶ ዓመት መገባደጃ ላይ ወረሂመኖን መሠረት አድርጎ «ማመዶች» የተባለ ሥርወ መንግሥት ወሎን መቆጣጠር ጀመረ:: ይህን ሥርወ መንግሥት የመሠረተውና ስሙንም ያወረሰው ሙሐመድ ዓሊ ወይም በፈረስ ስሙ አባ ጅቦ ተብሎ የሚጠራው ጦረኛ ነበር:: ይሁንና የአባ ጅቦ የልጅ ልጅ የነበረው አባ ጅሩ ሊበን ሲሞት ተከታዮቹ በጀመሩት የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የማመዶች ሥልጣን ማሽቆልቆል ጀመረ:: ይህም ሁኔታ የወሎን ግዛት እያዳከመ መጥቶ በ19ኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የትግሬና የሸዋ መሳፍንት የሚፋለሙበት አውድማ አደረገው::

በዚያን ዘመን ትግሬ የሚለው መጠሪያ ለዛሬይቱ ትግራይ ብቻ ሳይሆን መረብ ምላሽ በሚል ስያሜ ይታወቅ የነበረውን የኤርትራን ደጋማ ክፍልና የቀይ ባሕርንም ዳርቻ ያጠቃለለ ነበር:: በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ይህን ግዛት በበላይነት የሚያስተዳድረው ራስ ወልደ ሥላሴ ነበር:: ግዛቱ ለባሕር ጠረፍ የቀረበ በመሆኑም ከአውሮጳውያን አገር ጎብኝዎች ጋር መጀመሪያ ለመገናኘት የቻለ መስፍንም እሱ ነበር:: የኢትዮጵያን የተለየ ሁኔታ በውል ያላጤነው የእንግሊዝ ተጓዥ ሄንሪ ሶልት በ1798 ከራስ ወልደ ሥላሴ ጋር በዋና መዲናው በእንጣሎ ላይ በተገናኙ ጊዜ የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ተገናኘሁ ብሎ አወሳ:: እንደውነቱ ከሆነ ግን በዚያን ጊዜ እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትር ሊኖር ቀርቶ የደረጀ ማእከላዊ አስተዳደርም አልነበረም:: ወልደ ሥላሴና ጎንደርን ይቆጣጠር የነበረው የየጁ መሪ ራስ ጉግሣ የተለያየ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ስለነበሩ ሄንሪ ሶልት የትግሬን ምድር ዘልቆ ወደ ጎንደር እንዲያመራም የትግሬው መስፍን አልፈቀደለትም ነበር::

ራስ ወልደ ሥላሴ በ1808 ከሞተ ከጥቂት ዓመት በኋላ በእግሩ የአጋሜው ደጃች ሱባጋዲስ ወልዱ የትግሬ የበላይ ገዥ ሆኖ ተተካ:: ወልደ ሥላሴ ከየጁ መሳፍንት ጋር የጀመረውን ፉክክርም ቀጥሎ በየካቲት 8፣ 1823 ደብረ ዓባይ ላይ ከራስ ማርዬ ጉግሣ ጋር ጦርነት ገጠመ:: ሁለቱም መሪዎች ሕይወታቸው በዚያ ጦር ሜዳ ላይ አለፈች:: የማርዬ ወገን ቢያሸንፍም መሪያቸው ድሉን ባይኑ ሳያይ ወደቀ:: ሱባጋዲስም በአሸናፊው የየጁ ጦር ተይዞ ተገደለ:: የሱባጋዲስ ሞትም የትግሬ ውድቀት ሆነ:: ሁኔታው ያመቸው ለስሜኑ መስፍን ለደጃች ውቤ ነበር:: የትግሬ ሠራዊት አውራውን አጥቶ ሲበተን ውቤ ያለብዙ ድካም ሥልጣኑን እስከ ባሕር ጠረፍ ዘረጋ:: ይህን ሰፊና ቁልፍ የሰሜን ኢትዮጵያ ግዛት (ስሜንና ትግሬን ያጠቃለለ) ተቆናጦም ማዕከለ ሥልጣን የሆነችውን ጎንደርን ለመቆጣጠር ፊቱን ወደ ደቡብ አቀና:: የዚህም ውጤት በየካቲት 1 1834 ደብረ ታቦር ላይ ከየጁው መስፍን ከዳግማዊ ዓሊ ጋር ያደረገው ውጊያ ነበር:: በውጊያውም ውቤ ድል አደርጎ ድንኳኑ ውስጥ ፈንጠዚያ ላይ እንዳለ ዘግይተው ጦር ሜዳው በደረሱ የዓሊ ደጋፊዎች ሲማረክ የደብረ ታቦር ጦርነትም በሚያስገርም ሁኔታ ድል አልባ ሆኖ ቀረ::

ይህ ሁሉ የተጧጧፈ የማእከላዊ ሥልጣን ሽሚያ ሲደረግ የማታ ማታ የሀገሪቱ ታሪክ ዐቢይ ተዋንያን የሚሆኑት ሁለት ግዛቶች ከሞላ ጎደል ዳር ሆነው ይመለከቱ ነበር:: እነዚህም ጎጃምና ሸዋ ነበሩ:: የነሱ ትኩረት ማዕከላዊ ሥልጣን



ከመጨበጥ ይልቅ ባካባቢያቸው ያሉትን የኦሮሞ ግዛቶች ማስገበሩ ላይ ነበር:: ይሁንና ጎጃም ከጎንደር ፖለቲካ ጨርሳ ገሸሽ አላለችም ነበር:: መሪዋ ደጃች ጎሹ ዘውዴ በሰሜን ኢትዮጵያ ለበላይነት ከሚፋለሙት መሳፍንት አንዱ ለመሆን መጠነኛ ጥረት ያደርግ ነበር:: በዘመነ መሳፍንት ማንም ለማን የማይተኛ ነበርና ከባላንጣዎቹ አንዱና ዋነኛው የገዛ ልጁ ብሩ ጎሹ ነበር:: በ1834 ባደረጉት ውጊያም ብሩ አባቱን አሸነፈው:: እያደርም ጎሹ የበላይነት የማግኘት አቅሙ እያነሰ ሲሄድ የዳግማዊ ዓሊን የበላይነት ተቀብሎ በመተባበር በሚያስደነግጥ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የካሳ ኃይሉን (የቴዎድሮስን) ኃይል ለማቆም ሞከረ:: ሁለቱም ሳይሆንላቸው ቀርቶ ጎሹ ጉር አምባ ላይ (ኅዳር 19፣ 1845) ዓሊ ደግሞ አይሻል ላይ (ሰኔ 23፣ 1845) ለመጨረሻ ጊዜ ድል ተነሡ::

ባንፃሩ ከዓባይ በስተደቡብ ምሥራቅ የምትገኘዋ ሸዋ የዚህ የተጧጧፈ የስልጣን ትግል ወላፈኑ እንጂ እሳቱ አይደርስባትም ነበር:: መሪዎቿም የሰሜኑን ፍልሚያ ትተው ቀስ በቀስ የአካባቢያቸውን የኦሮሞ ግዛቶቸ እያስገበሩ ሥልጣናቸውን ያደረጁ ነበር:: ሰሜን ኢትዮጵያን አቋርጠው የመጡ የአውሮጳ ተጓዦች ሸዋ ምድር ሲደርሱ በሚያዩት አንፃራዊ ሰላምና ድሎት ይደነቁ ነበር:: ይህ ማለት ግን የሸዋ መሳፍንት የጎንደርን ነገር እርግፍ አርገው ትተው ነበር ማለት አይደለም:: እውነተኛዎቹ የልብነ ድንግል (ስለዚህም የሰሎሞን) ወራሾች መሆናቸውን ለማሳየት የሚያደርጉት ጥረትም የጎንደርን መሳፍንት ብቻ ሳይሆን ነገሥታቱንም ጭምር እንደ ተቀናቃኝ ለማየታቸው ማስረጃ ነው:: መጠሪያ የማዕረግ ስማቸውንም ደረጃ በደረጃ እያሳደጉ፣ በ«አቤቶ» የጀመሩት «መርዕድ አዝማች»ን አልፈው «ንጉሥ» ከመባል ደረሱ:: ገናና ነኝ ያለው ማናቸውም የሰሜን መስፍን እንኳ «ንጉሥ» በሚለው ማዕረግ ከመጠራት ታቅቦ ነበር::

የዘመነ መሳፍንትን ዓይነተኛ ባሕሪ የምናየው ግን የሸዋ መሳፍንት ራሳቸውን «ንጉሥ» ከማለታቸው ሳይሆን «ንጉሠ ነገሥት» ካለማለታቸው ላይ ነው:: ጎንደር የተሰየሙት ነገሥታት አሻንጉሊት ቢሆኑም ቅሉ «ንጉሠ ነገሥት» ለሚለው ስያሜ ባለመብቱ እነሱ ብቻ መሆናቸውን ሁሉም መሳፍንት ተገንዝበው ነበር:: ስለዚህ የመሳፍንቱ የመጨረሻ ግብ ራሳቸው ዘውድ ለመድፋት ሳይሆን የደፋውን ንጉሠ ነገሥት ተቆጣጥሮ የበላይነትን ለማግኘት ነበር:: በየጁ መሳፍንት በተከታታይ ተይዞ የነበረው የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ልዩ ከበሬታ ያገኘውም የባለሙሉ ሥልጣንነት ይዘት ስለነበረው ነው:: ስለዚህም ነው የካሣ ኃይሉ «ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ» መባል የዘመነ መሳፍንትን ፍጻሜ በጉልህ ያበሠረ እርምጃ ሆኖ የሚገመተው:: ይሁን እንጂ ካሣም ይህን ደፋር እርምጃ «ቴዎድሮስ» በሚለው ትንቢታዊ ስም መደገፍ ነበረበት:: ሰሎሞናዊውን ቅብዐ ቅዱስ በፍካሬ ኢየሱሱ ቴዎድሮስ መተካት ነበረበት፤ ከውርደት፣ ግፍና መከራ በኋላ ተሐድሶና ፍትሕ ለማምጣት ከእግዚአብሔር የተላከ መሪ::

ሌላው ስለዘመነ መሳፍንት መጤን ያለበት ነገር ገዥዎች ይብዙ፣ ጦርነቱም ያታክት እንጂ ተገንጥዬ ለብቻዬ መንግሥት አቆማለሁ የሚል ግዛት አልነበረም:: ግዛታዊነት የማዕከላዊ ሥልጣን መወጣጫ እንጂ በራሱ ብቻውን የሚፈለግ አልነበረም:: በተመሳሳይ ሁኔታም በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ውስጥ «እውነተኛው እምነት የኔ ነው» በሚል የሃይማኖት ክርክር ደም የሚያፋስስ ክፍፍል ተፈጥሮ ነበር:: ይህ ከፀጉር በሰለለ ነጥብ ላይ ይደረግ የነበረ ክርክር ላሁን ዘመን ሰው በቀላሉ የሚገባ አይደለም:: በጊዜው ግን የደም ጎርፍ ያስከተለ ጠብ ቀስቅሷል:: ልዩነቱ የተከሰተው በክርስቶስ ባሕሪ ትርጓሜ ላይ ነበር:: ልዩነቶቹ ቀደም ብለውም የተከሰቱ ቢሆኑም በተለይ እየጎሉ የመጡት ግን

ኢየሱሳውያን መጥተው የኦርቶዶክስን እምነት በብርቱ ከተፈታተኑት በኋላ ነው። የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ለዚህ ፈተና የሰጡት የተለያየ መልስም በተለያየ ጎራ አሰለፋቸው። የእውነተኛው ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነን ባዮች ተዋሕዶ ወይም ተቀናቃኞቻቸው ባወጡላቸው ስም «ካራ» ተብለው ታወቁ። ተቀናቃኞቹ ደግሞ ቅባትና የፀጋ ልጅ ተባሉ። በሌላ አነጋገር ደግሞ ተዋሕዶዎች ሁለት ልደትና ቅባት እንዲሁም የፀጋ ልጆች ደግሞ ሦስት ልደት ይባሉ ነበር።

የእነዚህ የእምነት ልዩነቶች የታሪክ ጠቀሜታ ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ይልቅ በጊዜው በነበረው የፖለቲካ ትግል ላይ የነበረው ነጸብራቅ ነው። እምነቶቹ ከተለያዩ ግዛቶች ጋር በመቆራኘታቸው የተጧጧፈውን ግዛታዊ ፉክክር ርእዮተ ዓለማዊ ሽፋን ሰጡት። ለምሳሌ ቅባት የጎጃም፣ ካራ የትግሬ፣ የፀጋ ልጅ ደግሞ የጎንደር ርእዮት ሆነው ነበር። በፖለቲካ መስክ እንደታየውም እነዚህን የእምነት ልዩነቶች ለማስታረቅ የሞከረው ቴዎድሮስ ነበር። ይሁን እንጂ እሱም ቢሆን ሳይሳካለት ቀርቶ ውዝግቡ እልባት ያገኘው በመጋቢት 1870 በቦሩ ሜዳ በአፄ ዮሐንስ ሰብሳቢነት በተደረገው ጉባዔ ላይ የተዋሕዶ እምነት ብቸኛ ተቀባይነት ሲረጋገጥ ነው።

መሳፍንት ሥልጣን ሲቀራመቱ፣ ካህናት ፀጉር ሲሰነጥቁ፣ የሥርዓቱ ተሸካሚ የሆነው ገበሬ እነዚህን ሁሉ ለመመገብ ይዳክር ነበር። የኅብረተሰቡ አምራች ክፍልም እሱው ብቻ ነበር። ዘር ቆጥሮ በሚያገኘው ርስቱ ላይ በሬውን ጠምዶ እያረሰና ከብቱን እያረባ ክረምት ከበጋ ሳይለይ ይለፋ ነበር። ይሁንና በምርቱም ሆነ በጉልበቱ ላይ ሙሉ ቁጥጥር አልነበረውም። መሳፍንቱና ካህናቱ ከነገሥታቱ በሚያገኙት ጉልት አማካይነት ከገበሬው ልኩ ያልተደነገገ ግብር ይሰበስባሉ። ይህ የሕይወቱ ዓይነተኛ ባሕሪ የሆነው የመገበር ዕጣም ነው ገበሬውን «ገባር» የሚል መጠሪያ ያሰጠው። ገበሬው ለባለጉልቱ እህል ከመስፈር አልፎ ሁዳድ በማረስ፣ እህል በመፍጨት፣ ቤትና ጎተራ በመስራት የጉልበት ሥራ እንዲያበረክት ይገደድ ነበር። ይህ የጉልበት ሥራም ካለው ጠቅላላ የሥራ ጊዜ ከሦስት አንድ እጁን ይወስድበት ነበር። ፕላውደን የተባለው የእንግሊዝ ተጓዥ ቆንስል የገበሬውን ጣጣ እንዲህ አድርጎ ያብራራዋል፤

> ግብሩ ስፍር ቁጥር የለው ከቀዬ ቀዬም ይለያል፤ ገበሬው ለራስ ዓሊ ወይም ለሌላ ታላቅ ሹም እህል ይሰፍራል፤ አንዳንዴም ግብሩን በገንዘብ ይከፍላል። አልፎ ተርፎም ለመንግሥት ሁዳድ የእርሻ በሬ ይሰጣል። የአካባቢው ሹም አምሾ ወይም ሌላ መጠን እህል ያሰፍረዋል፣ ወታደሩንም በገበሬው ቤት ይመራል። የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደ በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ቅቤ፣ ማርና ሌላም የሚያገኘው ከገበሬው ነው። አገር በጎበኘ ጊዜ ቀልበው አስደስተው መሸኘት ይጠበቅባቸዋል። በሰበብ ባስባቡም አስተዋፅዖ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፤ ለምሳሌ ወይ ሹሙ ዘመቻ መሄዱ ይሆናል፣ ወይ መመለሱ፤ ወይ ፈረሱ ጠፍቶበት ይሆናል፣ ወይ ትዳር መሥርቶ። ወይ ደግሞ ንብረቱ በእሳት ጋይቶ ይሆናል፤ ወይ ያለ የሌለ ሀብቱ በጦርነት ወድሞ። ወይም ደግሞ ተዝካር ማውጣት ይኖርበታል። (Plowden, 137-138)

ጉልት ባብዛኛው የጦር አገልግሎት ዋጋ በመሆኑም ሥርዓቱ የጦረኝነትን ባህል የሚያዳብር ነበር። አርሶ ከማደር ወታደር መሆን የሚመረጥበት ወቅት ነበር። ገበሬው ተፈጥሮ በየጊዜው የምታመጣበት ፍዳ



(ድርቅና የአንበጣ መንጋ ወረራ) ሳያንስ በወታደር ምዝበራ ይሰቃይ ነበር። ስለዚህም ለአንድ ጦረኛ ጌታ በማደር ገበሬው ከአታካቹ ኑሮ (ማረስ፣ ማረምና መጎልጎል) ነፃ ከመሆኑም በላይ ከመዘረፍ ወደ መዝረፍ ይሸጋገር ነበር። የገበሬውን የሰቆቃው ኑሮ ከሁሉም ይበልጥ የከፋ ያደረገው ወታደር በገበሬው ቤት የመመራት (የመሰራት) ባህል ነበር። በዘመኑ የወታደር ደሞዝም ሆነ የስንቅ አገልግሎት ስላልነበረ ወደ ጦር ሜዳ የተሰማራ ወታደር ለራሱም ሆነ ለፈረሱ እህል የሚያገኘው ከገበሬው ቤት ነበር። ጦሩ ከመንደሩ እስከወጣ ድረስ በገበሬው ቤት፣ ንብረት፣ አንዳንዴም በሚስቱ የሚያዘው ወታደሩ ነበር። በዘመኑ ሰሜን ኢትዮጵያን ጎብኝቶ የነበረው የእንግሊዝ ተጓዥ ማንስፊልድ ፓርኪንስ አንድ ገበሬ ትንሽ ቅቤ ደብቆ ስለተገኘ ሲቀልባቸው የቆዩት ወታደሮች ዘነዘና ላይ ጠፍረው በቁሙ በእሳት እንደጠበሱት ተርኮልናል።

ይሁንና ገበሬው ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ጠላቶቹን በልጦ ለመገኘት የተለያየ ጥረት ያደርግ ነበር። እንደአንበጣ የወረረው የወታደር መንጋ እስኪያልፍለት ድረስ ባሳቻ ቦታ ጉድጓድ ቆፍሮ እህሉን ይቀብራል። አንዳንዴም ወታደር ከሚበላው እሳት ይብላው ብሎ ጦር ከመምጣቱ በፊት እህሉን ያቃጥላል። ጭራሽ መላው ሲጠፋበት ግን እርሻና ቤት ለምኔ ብሎ ይሰደዳል። ወይም ከላይ እንደጠቀስነው ላንዱ ጦረኛ አድሮ ተራውን ይዘርፋል። በዚህ ሁሉ መሀል ባገር ሀብት የሚደርሰው ጥፋት እጅግ ከባድ ነበር። ይህንኑ በሚመለከት ሁለት ሚሲዮናውያን ስለ ዋግ አውራጃ የሚከተለውን ጽፈዋል፤

> ዋግ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ግዛቶች የተለየ ግምት ሊሰጣቸው ከሚችሉት አንዱ ነው። የተሻለ መንግሥት ቢኖር ኖሮ በሕዝብ ብዛትም ሆነ በእርሻ ይበልጥ በበለፀገ ነበር። የገዛ ዜጋዎቹን በየዓመቱ የሚወር መንግሥት እስካልተወገደ ድረስ ግን ንግድ፣ ሥርዓት፣ እርሻና ማናቸውም የኑሮ መሻሻል ይኖራል ማለት ዘበት ነው። አሁን የተያዘው ፈሊጥ ግን አገረ ገዥ በየዓመቱ ወታደሮቹን ይዞ ይመጣና የፈለገውን ይወስዳል። ገበሬዎቹ እህላቸውን ደብቀው ወደ ተራራው ይሸሻሉ። አገረ ገዢውም በቁጣ ቤታቸውንና ማሳቸውን ያጠፋዋል። (Isenberg and Krapf, 486-487)

## የደቡብ ኢትዮጵያ መንግሥቶችና ሕዝቦች


**በ19ኛው** መቶ ዓመት የነበረው የኢትዮጵያ ሥዕል የተሟላ የሚሆነው **በስተደቡብ** ያገሪቱ ክፍል የነበሩት ሕዝቦችና ግዛቶች ታሪክም አብሮ ሲወሳ **ነው**። በመቶ ዓመቱ ሁለተኛ አጋማሽ ላይ አሁን የምናውቃትን ኢትዮጵያን **የፈጠረው** የደቡቡና የሰሜኑ ውህደት ነበር። እዚህ ላይ ደቡብ የምንለው የሸዋን **መንግሥት** ሳይጨምር ከዓባይ ወንዝ በስተደቡብና በዚያው እርከን የሚገኘውን **ክፍል** ነው። እነዚህንም ግዛቶች አንድ ከሚያደርጋቸው የጂምግራፊ **አቀማመ**ጣቸው ባሻገር በጎንደር ዙሪያ ይሽከረከር በነበረው የዘመነ መሳፍንት **ፖ**ለቲካ አለመሳተፋቸው ነው። የነዚህ የደቡብ ግዛቶች የፖለቲካ ሥርዓትም **ዝቅተኛ** ከሆነ የጋርዮሽ ኅብረተሰብ አንስቶ ከሰሜኑ ግዛቶች የማይተናነስ **የፖ**ለቲካ አደረጃጀት የሚታይበት ነበር። እንዲህ በጣም ከደረጁት መንግሥታት **ውስጥ** ለአብነት የከፋ፣ የወላይታና የየም (የጃንጀሮ) መንግሥታትን መጥቀስ **ይቻላል**። እነዚህ መንግሥታትም በኦሞ ወንዝ አካባቢ ከመገኘታቸው የተነሣ **ኦሟዊ** (ኦሞቲክ) መንግሥታት ተብለው ይታወቃሉ።

የከፋ መንግሥት የተመሠረተው በ14ኛው መቶ ዓመት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። መንግሥቱን የተመለከተ የጽሑፍ መረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገኘው በ16ኛው መቶ ዓመት ሲሆን፣ መንግሥቱ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የደረሰው በ17ኛው መጨረሻና በ18ኛው መጀመሪያ ላይ ነው። እንደ ወላይታና የም እንዲሁም እንደ ብዙ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ ኤኮኖሚው የተመሠረተው በእንሰት ተክል ላይ ነበር። የኅብረተሰቡ ዋና አምራች ክፍልም የመሬት ባለቤትነቱን ይዞ ጉልበቱን ለገዢው መደብ የሚገብር የገበሬ መደብ ነበር። ከዚህም ሌላ በዘረፋም ሆነ በንግድ አንዳንዴም በእዳ ክፍያ የተገኙ ባሮች አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረግ ነበር። የሥርዓቱ ቁንጮ «ታቶ» ተብሎ የሚታወቀው ንጉሥ ሲሆን እሱም «ሚክሬቾ» ተብለው በሚታወቁ አማካሪዎች ይታገዝ ነበር። የገዥው መደብ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን የተቀበለ ሲሆን አብዛኛው ሕዝብ ግን «ኢቤዴ ጉዶ» ተብሎ የሚጠራው የባህላዊ እምነት መሪ ተከታይ ነበር። የከፋ መንግሥታት በ18ኛው መቶ ዓመት መገባደጃና በ19ኛው መጀመሪያ ላይ ከተፈጠሩት የኦሮሞ መንግሥታት ጋር ይካሄድ ከነበረው የደራ ንግድ ግብር በመሰብሰብ የገቢ ምንጫቸውን ያዳብሩ ነበር። የዚህ ንግድ ዓይነተኛ ሸቀጦችም ባሮች፣ የዝሆን ጥርስ፣ ቡናና ማር ነበሩ።

የወላይታ መንግሥት ሥረ መሠረት ከከፋም ይቀድም ይሆናል ተብሎ ይገመታል። በ13ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ወይም በ14ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ በሸዋው መነኩሴ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተጠመቀው መተሎሚ የተባለው ገናና ንጉሥ የወላይታ ንጉሥ ነበር የሚል አፈ ታሪክም አለ። «ወላይታ መላ» የተባለውና ወላይታን እስከ 15ኛው መቶ ዓመት የገዛው ሥርወ መንግሥት የተመሠረተውም በዚሁ በመተሎሚ ነው ተብሎ ይታመናል። ይህ ሥርወ መንግሥት ከትግራይ መጡ የሚባሉ ወራሪዎች በመሠረቱትና ግዛቱ ለአፄ ምኒልክ እንዲገብር እስከተደረገ ድረስ በቆየው በ«ትግሬ» ሥርወ መንግሥት ተተካ። «ካዎ» በሚል የማዕረግ ስም የሚታወቀው የወላይታ ንጉሥ ሥልጣኑ በሕይወትም በንብረትም ላይ ፍጹማዊ የሆነ ነበር። የመሬት ሁሉ ባለቤት እሱ ሲሆን «ጎቃ» ተብለው የሚታወቁት ጦረኞቹም የሚተዳደሩት እሱ በሚቸራቸው መሬት ነበር። ይህን ፍጹማዊ አገዛዝ በመቃወም በ19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ ሕዝባዊ አመፅ ከተነሣ በኋላ ግን የካዎው ሥልጣን በመማክርት ሸንጎ እንዲለዝብ ተደርጓል።

የየም ሕዝብ የጊቤ ወንዝን የምዕራብ ዳርቻ ይዞ የሠፈረ በእርሻ የሚተዳደር ሕዝብ ነበር። በወላይታ እንደሆነው ሁሉ መንግሥቱ የሚመራው «ዲዳ» ወይም «ጋማ» ተብሎ በሚታወቀው ሥርወ መንግሥት ሲሆን ኋላ ከሰሜን በመጣ «ሞዋ» ተብሎ በሚጠራ ሥርወ መንግሥት ተተክቷል። የፖለቲካው ሥርዓት ቁንጮ «አምኖ» ተብሎ ሲታወቅ እሱም መለኮታዊ ባሕሪ አለው ተብሎ የሚታመን፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሥልጣን አጣምሮ የያዘ ነበር። ከሱ ስር ደግሞ «ዋሶ» በሚባለው ሊቀመንበርነት የሚመራ «አስቴሶር» የሚባል የመንግሥት መማክርት ጉባኤ፣ «ኤራሾ» ተብለው የሚታወቁ የክፍለ ሀገር ገዢዎችና «ገና» ተብለው የሚታወቁ የአውራጃ ገዢዎች ይገኙ ነበር። ኤኮኖሚው የተመሠረተው ለንጉሡ በሚገብሩ አራሽ ገበሬዎች ላይ ሲሆን





1. ኢትዮጵያ በ19ኛው መቶ ዓመት

ንግድና የእጅ ሥራ (በተለይም ብረት ማቅለጥና ሸመና) የአጋዥነት ሚና ነበራቸው። የውጭ ግንኙነትን በተመለከተ በተለይ በ19ኛው መቶ ዓመት አጎራባቹ ከሆነው ከጅማ አባ ጂፋር ጋር በነበረው ባላንጣነት የታወቀ ሲሆን

ይህም ሁኔታ እልባት ያገኘው መቶ ዓመቱ መገባደጃ ላይ ሁለቱም መንግሥታት ለምኒልክ እንዲገብሩ ሲገደዱ ነው።

ጅማ አባ ጂፋር በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ዓመት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከበቀሉት የኦሮሞ መንግሥታት አንዱ ነበር። ቀድሞ የኦሮሞ ሕዝብ የሚተዳደርበት ሥርዓት በዕድሜ እርከን በተመሠረተውና ዲሞክራሲያዊና ሬፐብሊካዊ ባሕርይ በነበረው የገዳ ሥርዓት ነበር። ነገር ግን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚኖሩት ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ምድር ከተከሰቱት ዋና ዋና ኅብረተሰባዊ ለውጦች እንደ አንዱ በሚቆጠር ሂደት የገዳ ሥርዓታቸውን ትተው ንጉሣዊ አገዛዝ መሠረቱ። የዚህ ለውጥ ዋና ምክንያት ኦሮሞዎች ቀድሞ የሚተዳደሩበት የከብት ርቢ እየቀነሰ ሄዶ በእርሻ መተዳደር መጀመራቸውና ይህም ያስከተለው የኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈል ነው ተብሎ ይገመታል። ከዚያም በላይ ኦሮሞዎች ወደ ምዕራብ እየገፉ ሲሄዱ በተከሰቱት ተከታታይ ጦርነቶች ምክንያት በገዳ ሥርዓት «አባ ዱላ» የተባለው የጦር መሪያቸው ሥልጣን እየገነነ «አባ ቦኩ» የተባለው የኅብረተሰቡ የፖለቲካ መሪ ሥልጣን እየኮሰሰ መምጣቱም ለዚህ ሥርዓት ለውጥ አስተዋፅ አድርጓል። ይህን ዓይነት ለውጥ የታየው በተለይ በሁለት የኦሮሞ አካባቢዎች ነው። የመጀመሪያው በጊቤ ወንዝ አካባቢ ሲሆን በዚህም ምክንያት መንግሥታቱ «የጊቤ መንግሥታት» በሚል መጠሪያ ይታወቃሉ። ሁለተኛው አካባቢ ደግሞ በወለጋ፣ በነቀምቴና በቄለም ነው።

የጊቤ መንግሥታት ተብለው የሚታወቁት አምስት ነበሩ። እነሱም ሊሙ እናርያ፣ ጅማ፣ ጎማ፣ ጉማና ጌራ ነበሩ። ስሙ እንደሚያመለክተው «ሊሙ እናርያ» በመካከለኛ ዘመን መሀል ሀገር ያለው የክርስቲያን መንግሥት ገባር በነበረው በእናርያ መንግሥት መቃብር ላይ የተቋቋመ መንግሥት ነበር። መጀመሪያ ላይ ከአምስቱም መንግሥታት ገኖ የወጣውም ይኸው የሊሙ እናርያ መንግሥት ነበር። ይህም የሆነው ከሰሜን ኢትዮጵያ ጋር ያገናኝ የነበረውን ዋና የንግድ መሥመር መቆጣጠር በመቻሉ ነበር። ይህ የሊሙ እናርያ ገናናነት በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ በነገሠው አባ ባጊቦ በሚባለው ንጉሥ ዘመን ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ በቅቷል። በ19ኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ግን ጅማ ይህን የበላይነት ተቀናቅኖ የመሪነቱን ቦታ ያዘ። የጊቤ መንግሥታት ከወለጋ አቻዎቻቸው የሚለዩበት አንዱ ሁኔታ በ19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ የቀድሞ እምነታቸውን ትተው የእስልምና ሃይማኖት በመቀበላቸው ነው።

በወለጋ ከበቀሉት መንግሥታት ዋናዎቹ ሁለት ነበሩ። አንደኛው በነቀምቴ አካባቢ በክሬ የተባለ ጦረኛ የመሠረተው «የሌቃ ነቀምቴ መንግሥት» ሲሆን እሱም በተከታዮቹ በሞሮዳና ኩምሳ (ኋላ ገብረ እግዚአብሔር በሚባል የክርስትና ስሙ የታወቀው) ዘመን እያደገና እየገነነ ሄደ። ከዚህ በስተምዕራብ ደግሞ ጆቴ ቱሉ የተባለ ሌላ ጦረኛ በ19ኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ከሱዳን ጋር የነበረውን ንግድ በመቆጣጠርና በጦር ዘመቻ አማካይነት «የሌቃ ቄለም»ን መንግሥት ሊያቋቁም በቃ።

የጆቴ ቱሉ መንግሥት በስተሰሜኑ አቆልዲ (አሶሳ)፣ ኾሞሻና ቤላ ሻንጉል (ቤኒ ሻንጉል) ከሚባሉት የሼኽ ግዛቶች (በተለይም ከአቆልዲ ጋር) አንዴ በሰላም ሌላ ጊዜ ደግሞ በጦርነት ይገኛኝ ነበር። ሦስቱም ግዛቶች የተመሠረቱት ከሱዳን የመጣ የገገር መደብ በአካባቢው የበርጣ ሕዝብ ላይ የበላይነትን ካገኘ



በኋላ ነው። ይህ ግን ከሱዳን የመጣ የመጀመሪያው ተጽዕኖ አልነበረም። በቀደሙት መቶ ዓመታት ከፉንጅ የመጡ ወይም «ፉንጅ» ነን የሚሉ ገዢዎችም እንዲሁ በበርጣው ሕዝብ ላይ ገዢነትን መስርተው ነበር። በምዕራብ ጎጃም የጉሙዙን ሕዝብ አስገብሮ የተመሠረተው የጉባ የሼኽ ግዛትም በተመሳሳይ ሁኔታ ነው። እነዚህ የሼኽ ግዛቶች በሙሉ የእስልምና ተከታዮች ናቸው። በአካባቢውም እስልምናን ለማስፋፋት አግዘዋል።

በስተምሥራቅ የሚገኘውና በአሚር የሚተዳደረው የሐረር መንግሥት ደግሞ በፊናው አንድ ትልቅ የእስልምና ሥልጣንና እምነት ማዕከል ነበር። የሐረር አሚሬት የአህመድ ግራኝ መንግሥት የነበረው የአዳል ወራሽ ሆኖ ይታይ እንጂ፤ ከኦሮሞዎች በደረሰበት ጥቃት የማዕከላዊ ዘመን ሥልጣንና ሞገሱ ኮስምኖ ነፃነቱን መለዮው በሆነው ግንብ ላይ መሥርቶ በከተማ የተወሰነ መንግሥት ሆኖ ነበር። ይሁን እንጂ የማታ ማታ ሐረሬዎችና የአካባቢው ኦሮሞዎች ተቻችለው በመኖር በንግድ፣ በጋብቻና በሃይማኖትም መተሳሰር ጀመሩ። የሐረር ድክመት ግን የውጭ ጣልቃ ገብነትን መጋበዙ አልቀረም። በ1868 በሙሐመድ ራዑፍ ፓሻ የሚመራው የግብፅ ጦር ከተማዪቱን ይዞ አሥር ዓመት ያህል የቆየውን የግብፅ ሥልጣን መሥርቷል። ይህን ማድረግ የቻለውም አሚሩንና የሰላም ጥሪውን አምነው የመጡትን የኦሮሞ ተወካዮች ያስርጎራሄ ከጨፈጨፈ በኋላ ነው።

በቀሩት የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍሎች ከላይ የተዘረዘሩትን ዓይነት የደረጁ መንግሥታት እምብዛም አይታዩም ነበር። በዛሬይቱ ጋምቤላ አካባቢ የሚኖሩት እኘዋኮች፣ «ኒያ»ና «ኩዋሪ» ተብለው በሚጠሩት መሪዎቻቸው የሚተዳደሩ ሲሆን ኢኮኖሚያቸውም እርሻን ከአደንና ፍራፍሬ ለቀማ ጋር ያጣመረ ነበር። ጎረቤቶቻቸው ኑዌሮች ደግሞ ዋና መተዳደሪያቸውና የሥጋዊም ሆነ የመንፈሳዊ ሕይወታቸው መሠረት የከብት ርቢ ነበር። ሁለቱም በደጋው ከሚገኙት ኦሮሞዎች ጋር በንግድ ይገናኛሉ። በስተደቡብና ደቡብ ምስራቅ ደግሞ እንዲሁ በከብት ርቢ የሚተዳደሩትና ድንበር የማያውቁት የቦረና ኦሮሞዎችና የሱማሌ ሕዝቦች ነበሩ። ይህ የከብት አርቢዎች ቀለበት የደንከልን በረሃ በያዙትና በኃይለኛ ነታቸውና በአገራቸው ንዳድነት ትብብር ነፃነታቸውን አስከብረው በቆዩት አፋሮች በኩል አልፎ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ይዘልቃል። ይሁንና አፋሮችም ቢሆኑ ከደጋው ጋር የንግድ ግንኙነት ነበራቸው። የባቲ ደማቅ ገበያ መሠረትም ይኸው ነው። ከአፋሮች በስተሰሜን የሚገኙት ሳሆዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ሲገኙ በባሕር ዳርቻና በደጋው መካከል ያለው ርቀት እየጠበበ በመምጣቱ ግን የነሱ መፈናፈኛ የተወሰነ ነበር። ስለሆነም ከደጋው መንግሥታት ጋር ይበልጥ የመቀራረብ ባሕርይ ይታይባቸዋል። በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ከነበሩት የትግሬ መሳፍንት አንዱ ደጃች ሱባጋዲስ የኢሮብ (ሳሆ) ተወላጅ መሆኑም ለዚህ አንድ ማስረጃ ነው።

በደጋው የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል ኩሻዊ የሆኑት ኮንሶዎች በእርከን እርሻ፣ ከእንጨት በተጠረቡ ቅርፆችና በድንጋይ ግንቦች የታወቀ ሥርዓት



1.1. ሐረር ከተማ በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ

ሲመሠርቱ ጋሞና ጎፋ የተባሉት መንግሥታት ደግሞ ከላይ የዘረዘርነው አሟዊ የደረጀ የፖለቲካ ሥርዓት ባህል ሌላ ማስረጃ ናቸው::

ቆላማውን ክፍል ሳይጨምር የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዓይነተኛ መታወቂያና ከሰሜኑም ክፍል የሚለያቸው የእንሰት ባህል ነበር:: በጎሣ በመከፋፈላቸው ምክንያት በ19ኛው መቶ ዓመት ብዙ ጥቃትና በባርነት መጋዝ የደረሰባቸው ጉራጌዎች፣ ሀዲያና ከምባታዎች የዚሁ የእንሰት ባሕል አካል ናቸው:: የሸዋ ኦሮሞዎችም እንደ ጉራጌዎች አንድ ወጥ የሆነ መንግሥት መመሥረት ባለመቻላቸው የሸዋው መንግሥት ገባር ሆነዋል:: ይህ የሸዋን ኦሮሞዎች የማስገበሩ ተግባር በተለይ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን ተጠናክሮ በንጉሥ ምኒልክ ማሳረጊያውን አግኝቷል:: በስተደቡብ የሚገኙት የአርሲ ኦሮሞዎች ደግሞ እርሻና ከብት ርቢን አጣምረው ሲኖሩ፣ ተወራራሽ እየሆነ በመጣው አባ ዱላ አስተባባሪነት የኅብረት ስሜት ሊፈጥሩ በቅተው ነበር::

## ሰሜንና ደቡብን የሚያገናኘው የንግድ መስመር

እነዚህ ለትንተና እንዲያመቸን ሰሜንና ደቡብ ኢትዮጵያ ብለን የለየናቸው ግዛቶች ፈጽሞ የማይገናኙ አካሎች ሆነው አይደለም:: በፖለቲካ ሥርዓትና በኑሮ ሁኔታ የተለያዩትን ያህል ሁለቱም ክፍሎች አንድ ወጥ በሆነ የንግድ ሠንሠለት ተሳስረው ኖረዋል:: በ19ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ የተከናወነው የሁለቱ ውሕደት ዋና መሠረትም ይኸው ንግድ ነበር::

በመካከለኛው ዘመንም የደቡብ ምዕራብ ግዛቶችን ከባሕር ጠረፍ ጋር የሚያገናኝ የንግድ መሥመር እንደነበር ይታወቃል:: ይሁንና ይህ ብዙ ግዛቶችን አቋርጦ የሚሄድ የንግድ መሥመር የተለየ እድገትን ያሳየው በ19ኛው መቶ ዓመት ነው:: ለዚህም አንዱና ዋነኛው ምክንያት በቀደሙት መቶ ዓመታት ተዳክሞ የነበረው የቀይ ባሕር ንግድ እንደገና ማንሠራራቱ ነው:: በዘመኑ ብዙ የአውሮጳ ተጓዦች ወደ አካባቢው መምጣታቸውና ስለሁኔታውም መዘገባቸው




የንግዱን ብዛትና ጠቃሚነት ለመረዳት አስችሎናል:: በዚህ ወቅት የኢትዮጵያን ምድር አቋርጠው የሚሄዱ ሁለት የንግድ መሥመሮች ነበሩ:: አንደኛውና በመጀመሪያው ዓመታት ጎላ ብሎ የሚታየው ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ከሰሜኑ ክፍል የሚያገናኘው የንግድ መሥመር ነበር:: ይህ መሥመር ከቦንጋ (ከፋ) ተነስቶ በጂሬን (ጂማ)፣ ሰቃ (ሊሙ እናርያ)፣ አሰንዳቦ (ሆሮ ጉድሩ)፣ ባሶ (ጎጃም)፣ ደረጣ (በጌምድር) አድርጎ ጎንደር ይገባል:: ከዚያም ሁለት ተከፍሎ አንዱ ሱዳንና ኢትዮጵያ ድንበር ላይ ወደምትገኘው ከተማ ወደ መተማ ሲዘልቅ ሌላው በአድዋ በኩል አድርጎ ቀይ ባሕር ዳርቻ ከምትገኘው ምፅዋ ይደርሳል::


ሁለተኛው የንግድ መሥመር ደግሞ አካሄዱ አግድሞሽ ነበር:: በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንደ ጎንደሩ መሥመር የደራ ባይሆንም የኋላ ኋላ ግን የሸዋ መንግሥት እየገነነ ሲሄድ እሱም የቀዳሚነት ስፍራን አግኝቷል:: ይህ መሥመር ከጂሬንና ሰቃ ተነሥቶ በሶዶና ሮጌ (የረር ተራራ አጠገብ) አድርጎ፣ የሸዋ የንግድ መዲና የነበረችው አልዩ አምባን ከመገበ በኋላ፣ የምሥራቅ ኢትዮጵያ የንግድ መናኸርያ ከነበረችው ሐረር ይደርሳል:: ከዚያም በሁለት ዘርፍ ወደ ዘይላና በርበራ ይዘልቃል:: እዚህ ላይ አንባቢ ማጤን ያለበት በ20ኛው መቶ ዓመት የኢትዮጵያ ዋነኛ የንግድ መገናኛ አውታር የሆኑት የጅቡቲና የአሰብ መሥመሮች በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ ገና ያልተቋቋሙ መሆናቸውን ነው::

በነዚህ የንግድ መሥመሮች ለገበያ ከሚቀርቡት ግንባር ቀደምነትን የያዙት ባሮችና ጨው ነበሩ:: ጨው ከጥልጣል በረሃ (ትግራይ) የሚገኝ ሲሆን ዋጋው ወደ ደቡብ ምዕራብ በገፋ ቁጥር እየተወደደ ይሄድ ነበር:: የጨው ተፈላጊነት በምግብ ማጣፈጫነቱ ብቻ ሳይሆን በአሞሌነት ቅርፁ የመገበያያ ገንዘብም ስለነበር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ መስተዋት፣ ጨሌ፣ ጨርቃ ጨርቅና የብረት ዕቃዎች ከውጭ አገር እየመጡ ከባሕር ወደቦች ወደ መሀልና ዳር አገር ይገቡ ነበር:: ባሮች ደግሞ ከደቡብ ምዕራብ ግዛቶች እየተነዱ ለገበያ ይቀርቡ ነበር:: ጥቂቶቹ አገሪቱ ውስጥ ለቤት አገልጋይነት ሲቀሩ አብዛኞቹ ግን ወደ ሱዳንና ዐረብ አገር ይሸጡ ነበር:: ባሮች የሚገኙበት መንገድ የተለያየ ነበር:: አንዳንዶቹ የጦር ምርኮኞች ነበሩ:: ሌሎቹ ደግሞ በፍንገላ የተገኙ ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ረሀብ ወይም እዳ ያስገደዳቸው ወላጆቻቸው የሸጧቸው ልጆች ነበሩ:: የባርያ ንግድ እጅግ እየተስፋፋ ከመሄዱም የተነሣ አንዳንድ በባርያ አቅርቦት የታወቁ መናኸርያዎች ሊፈጠሩ በቅተው ነበር:: ለምሳሌም የጁቤ (ጎጃም) እና ዐብዱል ራሱል (አልዩ አምባ አጠገብ) ባሮች በጨረታ የሚሸጡባቸው መዲናዎች ነበሩ:: ሌሎች ከዳር አገር የሚመጡ የንግድ ሸቀጦች የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅና ዝባድ ነበሩ:: በ19ኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ እስካሁን በንግድ የበላይነትን መያዝ የቻለው ቡና ብቅ ማለት ጀመረ::

ብዙ ፈተና ያለበትንና እያሌ ግዛቶችን የሚያቋርጠውን የንግድ መሥመር አንድ ነጋዴ ብቻውን እንደማይዘልቀው ግልጽ ነበር:: ስለዚህም ነጋዴዎች የንግድ እንቅስቃሴያቸውን በመጠኑም ቢሆን በተደራጀ መንገድ ማካሄድ ነበረባቸው:: በረጅሙ ጉዟቸው የሚመራቸውና የሚወክላቸው ሲራራ ከመሀላቸው መምረጥ ነበረባቸው:: ይህም ሰው ነጋድራስ (የነጋዴ ራስ ወይም አለቃ) እየተባለ መታወቅ ጀመረ:: ነጋዴዎቹ ለሌሊት ቁርና ለቀን ሐሩር



1.1. ሐረር ከተማ በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ




2. የንግድ መሥመሮች በ19ኛው መቶ ዓመት

ከመጋለጣቸውም ሌላ አያሌ ወንዞችን ማቋረጥና በየጫካው አድብቶ የሚጠብቃቸውን ሽፍታና ቀማኛ መቋቋም ነበረባቸው። ይህ አልበቃ ብሎ ደግሞ ሥፍር ቁጥር የሌላቸውን የመንደር አባ ቀሮዎችና ኃይላቸው የዳበረ ገዥዎችን ተለማምጠው ማለፍ ነበረባቸው። በዚህ ሁሉ ወቅት ሲያስፈልግ የጦር መሪ ሲያመች ደግሞ አፈ ጉባኤ ሆኖ ነጋዴዎቹን የሚመራው ነጋድራስ ነበር። ሌላ የነጋዴዎች የንግድ አሳር ደግሞ በየግዛቱ የሚጋረጥባቸው መቅረጫ ኬላ ነበር።ባንፃሩም የንግድ ቀረጥ ለፖለቲካ ባለሥልጣኖች የማይናቅ የገቢ ምንጫቸው ነበር።

ከነዚህ ላይ ከተዘረዙት ሁለት ዋና የንግድ መስመሮች በተጨማሪ ሦስት ሌላ የንግድ ግንኙነት መሥመሮች ነበሩ። ከነዚህም አንዱ በደጋው ክፍል የሚታየው ባካባቢ የተወሰነ የንግድ እንቅስቃሴ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ በቆላማ አካባቢ ሕዝቦችና በደገኞች መካከል የሚደረግ የንግድ ልውውጥ ነበር። ለዚህም በምሳሌነት መጥቀስ የሚቻለው በአኙዋክና በወለጋ/ኢሉባቦር ኦሮሞዎች፣ በአፋርና በወሎ መካከል የነበረውን ንግድ ነው። ሦስተኛው ደግሞ በጠረፍ



ግዛቶችና በአካባቢ አገሮች (ሱዳን፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ) መካከል የነበረው ንግድ ነው። ይህ «ድንበር ዘለል» ንግድ ኋላ ኢትዮጵያ ባውሮጳ የቅኝ ግዛቶች መከበብ ከጀመረች በኋላ እጅግ እያደገ መጥቶ የመሀል ሀገሩን ንግድ ባያሌው ተፈታትኖታል።

# የውጭ ተፅዕኖ

## የአውሮጳውያን እንደገና ዓይናቸውን ወደ ኢትዮጵያ ማቅናት

አፄ ፋሲለደስ በ1625 ኢየሱሳውያንን ካገር ሲያስወጣ ኢትዮጵያና አውሮጳ እህል ውሃቸው ያለቀ መስሎ ነበር። በርግጥም ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል ኢትዮጵያውያን የፈረንጅ ፊት ዳግም አያሳየን ብለው በራቸውን ዘግተው ይኖሩ ነበር። አገሪቱን ለመጎብኘትና ያዩትንም ለዓለም ለማሳወቅ ከቻሉት ከእስኮትላንዱ ተጓዥ ጀምስ ብሩስና ከፈረንሣዊው ሐኪም ሻርል ፖንሴ በስተቀር ጎብኝዎችም ሆኑ ተመራማሪዎች ኢትዮጵያን እምብዛም አልደፈሩም። ይህ ሁኔታ በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ መለወጥ ጀመረ። አውሮጳ ኢትዮጵያን በአዲስ ጉልበትና ባዲስ ስሜት ተጠጋች። ኢትዮጵያውያንም ጠንቀቅ ማለታቸው እንኳ ባይቀር ሳይጠቅሙን አይቀርም ብለው ተቀበሏቸው።

ይህ አዲስ የአውሮጳ ስሜት በኢትዮጵያ ምድር ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በጠቅላላው የአፍሪቃ አህጉር የታየው የአውሮጳውያን ሰርጎ መግባት አንዱ አካል ነበር። የአውሮጳ በአፍሪቃ መግባት ብዙ ገጽታዎች ቢኖሩትም ዋና አንቀሳቃሽ ኃይሉ ኢኮኖሚያዊ ነበር። በ18ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ የጀመረውና የአውሮጳን ሕይወት ከመሠረቱ የለወጠው የኢንዱስትሪ አብዮት በአውሮጳና በአፍሪቃ መካከል አዲስ ግንኙነት አስከተለ። አብዮቱ ያስከተለው የምርት መትረፍረፍ በአውሮጳ ድንበር ሊገታ አልቻለም። በገፍ የሚመረቱትን ሸቀጦች ለማራገፍ የአፍሪቃን ገበያ መቆጣጠሩ አማራጭ የማይገኝለት ነገር ሆነ። ስለሆነም እንደሌላው የአፍሪቃ አገሮች ሁሉ በዚህን ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት የአውሮጳ መንግሥት ወኪሎች ከሁሉም በላይ የንግድ አምባሳደሮች ነበሩ ማለት ይቻላል። በ1796 የኢትዮጵያን ምድር በመርገጥ በዘመኑ የመጀመሪያው አውሮጳዊ የሆነው እንግሊዛዊው ጆርጅ አነስሌ (ኋላ ቪስካውንት ቫሌንሺያ) ሁኔታ ከዚህ የተለየ አልነበረም። በአውሮጳ ወኪሎችና በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች መካከል በዘመኑ የተደረጉ ውሎችም ቢሆኑ ዓቢይ አንቀጻቸው የንግድ መስፋፋትን የተመለከተ ነበር። በዚህ ረገድ በ1834 በንጉሥ ሣህለ ሥላሴና በፈረንሣዊው ሮሼ ዴሪኩር መካከል ተደረገ የተባለውንና ኋላ ግን ሐሰት ሆኖ የተገኘውንና በ1842 በራስ ዓሊና በእንግሊዛዊው ዎልተር ፕላውደን መካከል የተደረጉትን ውሎች መጥቀስ ይቻላል።

አውሮጳውያን ወደ ኢትዮጵያ ማተኮር የጀመሩበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በዘመኑ እንደገና ያንሰራራውን የክርስትና እምነትን የማስፋፋት ተልዕኮ ነበር። ኢትዮጵያ ከ4ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ክርስቲያን የነበረች መሆኗ የአውሮጳ ሚሲዮናውያንን እንቅስቃሴ አልገታውም። ከዚያም በላይ በ16ኛውና በ17ኛው መቶ ዓመት ኢየሱሳውያን የካቶሊክን እምነት ለማስረፅ ባደረጉት ጥረት የደረሰው ጥፋትና እልቂትም ወደ ኋላ እንዲሉ አላደረጋቸውም። ያሁኑ የእጥምቆ እንቅስቃሴ ግን እንደ በፊቱ በካቶሊኮች ብቻ የተወሰነ አልነበረም።

እንዲያውም ግንባር ቀደም ሆነው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ዋና መሥሪያ ቤቱ ለንደን የነበረው «የቤተ ክህነት ሚሲዮናዊ ጉባኤ» የተባለው የፕሮቴስታንት ድርጅት አባላት ነበሩ:: ከነዚህም ጎላ ብለው የሚታዩት በትግራይና በቤጌምድር ይሰብክ የነበረው ሳሙኤል ጎባትና ባብዛኛው በሸዋ ግዛት ይንቀሳቀሱ የነበሩት ኢዘንበርግና ክራፕፍ ነበሩ:: ከካቶሊኮች ወገን ደግሞ በር ከፋቹ ጁሴፔ ሳፔቶ ሲሆን በሱ ፈለግ የመጣው ጆዩስቲኖ ደ ዣኮቢስ ደግሞ በ1832 በሰሜን ኢትዮጵያ የላዛሪስት ሚሲዮንን መሠረተ:: ከሰባት ዓመት በኋላ ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ሊንሠራፋ የበቃው የካፑቺን ሚሲዮን መሥራች ካርዲናል ማሳያ (አባ ማስያስ ተብሎ የሚታወቀው) ወደ አገሪቱ መጣ::

ከመንግሥት መልእክተኞቹና ሚሲዮናውያን ጎን ለጎን ደግሞ ሳይንቲስቶችና አገር ቃኝዎች ነበሩ:: ከነዚህም ውስጥ በምርምራቸው ጥልቀትና በጽሑፎቻቸው ብዛት የታወቁትን ጀርመናዊውን ኤድዋርድ ሩፔልንና ፈረንሳውያን ወንድማማቾቹን አንቷንና አርኖ ዳባዲን መጥቀስ ይቻላል:: የአውሮጳ ተመራማሪዎች ከሀገሪቱ ዕፀዋት አንስቶ እስከ ተለያዩት ብሔረሰቦች አኗኗር ድረስ የማይመረምሩትና የማይዘግቡት ነገር አልነበረም:: በምርምራቸውም ያሳዩት የነበረው ትጋትና ያለመታከት ያስደነገጠው የስሜኑ ገዥ ደጃች ውቤ ኃይለ ማርያም እንዲህ አለ ተብሎ ይነገርለታል::- «አንዱ ዕፀዋታችንን ይሰበስባል፣ ሌላው ደግሞ ድንጋዮቻችንን:: ምን እንደጠፋባችሁ አላውቅም፣ ያም ሆነ ይህ ግን እኔ አገር እንድታገኙት አልሻም::» (Rubenson, *Survival*, 54)

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው የአውሮጳ ትኩረት ገጽታዎች (ንግድ፣ ዲፕሎማሲ፣ ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴና ሳይንሳዊ ምርምር) የተያያዙና ተደጋጋፊም ነበሩ:: ሳይንቲስቶቹ ዕውቀት የጠማቸው ምሁራን ብቻ አልነበሩም፤ ብዙ ጊዜ በፖለቲካ ተግባርም ይሰማሩ ነበር:: ሚሲዮናውያኑም ቢሆኑ ብቻቸውን ሃይማኖት የሚያስፋፉ ሰባክያን ሳይሆኑ የመንግሥታቸው የሞራልና አንዳንዴም ቁሳዊ ድጋፍ ያልተለያቸው አምባሰደሮች ነበሩ:: ሚሲዮናውያኑም ሆኑ የመንግሥት ልዑካኑ አልፎ አልፎ የተመራማሪነት ካባ መደረባቸውም አልቀረም:: ሰባኪው ክራፕፍ በሸዋና በእንግሊዝ መካከል በተደረገው ውል ድርድር ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው:: እንዲሁም መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ሰር ጆርጅ አነስሌ የዕፀዋትንና ጂዖግራፊን ምርምር ከንግድ ማስፋፋት ተግባር ጋር አቀናጅቶ ነበር:: ሚሲዮናዊው ተግባርና ንግድም ተነጣጥለው የሚታዩ አልነበረም:: ቄስ በሄደበት ነጋዴ መከተሉ የተለመደ ነበር::

## የግብፅ መስፋፋት

ይሁንና ይኸ ሁሉ የዘረዘርነው የአውሮጳውያን እንቅስቃሴ ቅድመ ዝግጅት እንጂ የአስጊነት ባሕሪ ገና አልያዘም ነበር:: «የአፍሪቃ ቅርጫ» ተብሎ የታወቀው የአውሮጳውያን ግዛት የመካለል እሽቅድምድም የሚመጣው ገና በ19ኛው መቶ ዓመት የመጨረሻ ሩብ ላይ ነው:: በዚህ ወቅት አውሮጳውያን ገና በዳበሳና በዳሰሳ የሚሄዱ ይመስል ነበር:: ኢትዮጵያን ይበልጥ የሚያሰጋ እንቅስቃሴ የመጣው ከሩቅ ሳይሆን ከቅርብ፣ ከአውሮጳ ሳይሆን ከአፍሪቃ ነበር::



በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ታሪክ እንደ ግብፅ ጉልህ ሥፍራ የያዘ ኖሮ አያውቅም:: በተለይም ኢትዮጵያ ክርስትና ከተቀበለችበት ከ4ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ በእስክንድርያው ፓትርያርክ የሚሾም ግብፃዊ መሆኑ ያቺን አገር የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ መሪ ተዋናይ አድርጓታል:: አሁንም ከ19ኛው መቶ ዓመት መባቻ ጀምሮ ኢትዮጵያን በብርቱ የተፈታተነቻት ግብፅ ነበረች:: ኢትዮጵያም ይህን ለመቋቋም ባደረገችው አጸፋዊ እንቅስቃሴ ሳቢያ ለዘመናዊ ትንሣኤዋ በቃች::

በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ግብፅ ራሷ አብዮታዊ ሊባል በሚችል የለውጥ ሂደት ውስጥ ትገኝ ነበር:: ከ1790 እስከ 1794 የቆየው የናፖሊዎን አገዛዝ አጭር ቢሆንም ብዙ አሻራዎችን ትቶ ሄዷል:: ስድስት መቶ ዓመት ግብፅን ሲገዙ የቆዩትን «የማምሉኮችን» ሥልጣን የባሰ ከመገዝገዙም በላይ የፈረንሣይን አብዮት ጮራ በምድረ ግብፅ መፈንጠቁ አልቀረም:: ናፖሊዎንና ወታደሮቹ በተባበረ የእንግሊዝና የኦቶማን ጦር ቢባረሩም ነገር እንደ ቀድሞው ሊሆን አልቻለም:: አንደኛ እንግሊዝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለሕንድ ግዛቷ መሸጋገሪያ በሆነችው ግብፅ ላይ ተመሳሳይ አደጋ ዳግመኛ እንዳያንጃብብ መከላከልን የውጭ ፖሊሲዋ መሠረት አደረገችው:: ሁለተኛ ፈረንሣዮቹን ከምድረ ግብፅ ያባረረው ጦር ሁሉ ሲመለስ በኦቶማን ሠራዊት ውስጥ የአልባኒያን ጦር መርቶ የመጣው ሙሐመድ ዓሊ የፖለቲካ አዝመራው ስላጓጓው እዚያው ከተመ:: በማምሉኩ መቃብር ላይም አዲስ ሥርወ መንግሥት መሠረተ:: ይህ ሥርወ መንግሥት በ1944 በገማል ዐብደል ናስር እስኪወገድ ድረስ ግብፅን የገዛት ነው::

ሙሐመድ አሊ ማምሉኮችን አስወግዶ ለሥልጣኑ ደልዳላ ኤኮኖሚያዊና ወታደራዊ መሠረት ካበጀ በኋላ ወደ ውጪ ማማተር ጀመረ:: መጀመሪያ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ፣ በተለይም ወደ ሦርያ መስፋፋት ጀመረ:: ይህ በእንግሊዞች ሲቀጭበት ደግሞ ፊቱን ወደ ደቡብ አዞረ:: ያኔ ነው ለኢትዮጵያ አስጊ እየሆነ መምጣት የጀመረው:: በ1813 መካከለኛ ሱዳንን ይገዛ የነበረውን «የፉንጅ» መንግሥት ድል በማድረግ በሱዳን ላይ ቢያንስ ስድሳ ዓመት የቆየውን የግብፅን የበላይነት መሠረተ:: ከዚህ በኋላ ነው የግብፅ ተስፋፊ ሠራዊትና የኢትዮጵያ ጠረፍ ገዢዎች ድንበር ላይ መጋጨት የጀመሩት:: ይህን ባዲስ ጉልበት እየገፋ የመጣውን የግብፅ ኃይል ለማገድ በወልቃይት ደጃች ውቤ፣ በደምቢያ ደግሞ ደጃች ክንፉ ተሰለፉ:: የክንፉ ወንድም (ባባት ወገን) የሆነው ካሣ ኃይሉም (የኋላው ቴዎድሮስ) ይህንኑ የድንበር ፍልሚያ ከወረሰ በኋላ ነው ጉልበቱም እየጠነከረ አጠቃላይ አመለካከቱም እየተለወጠ የመጣው::

የግብፅ አደጋ በምዕራብ ድንበር ብቻ ሳይወሰን በምሥራቁም የባሕር ጠረፍ አንዣቦ ነበር:: ሙሐሙድ ዓሊ ዐረቢያን ሲይዝና ቀይ ባሕርን በሙሉ ሲቆጣጠር በኢትዮጵያ ላይ አዲስ አደጋ ተከሰተ:: የኦቶማን ቱርኮች በ1549 ምፅዋን ከያዙ ጀምረው አካባቢውን ቢቆጣጠሩም በ19ኛው መቶ ዓመት እጅግ ተዳክመው ነበር:: ምፅዋንና አካባቢውን የአበሻ ግዛታችን ነው እያሉ ይመጻደቁ እንጂ ለይስሙላ መሆኑን ራሳቸውም ያውቁት ነበር:: እንኳን የሩቅ አገር ግዛታቸውን ሊቆጣጠሩ የቅርቡም ከቁጥጥራቸው እያፈተለከባቸው ነበር:: ስለዚህም ነበር በዘመኑ አባባል ቱርክ «የአውሮጳው ሕሙም» ተብላ ትታወቅ የነበረው:: የምፅዋ ግዛትም የሚተዳደረው በቱርኮች ሳይሆን መጀመሪያ እነሱ ወኪል ባደረጓቸው ኋላ ግን ከቱርክ ነፃ ሆነው ከኢትዮጵያ የደጋ መሳፍንት ጋር በሰላምና አንዳንዴም ግብር በመክፈል ይኖሩ በነበሩት የአርቂቆ ናኢቦች ነበር::

በ1839 ግብፅ ምፅዋን ሙሉ በሙሉ ስትቆጣጠር ነገር መለወጥ ጀመረ:: በዛለው በኦቶማን ጉልበት እግር አዲስና ተስፋፊው የግብፅ ጉልበት ተተካ:: የሚገርመው ግን ኢትዮጵያውያን ሁለቱንም ባንድ ዓይን ነበር የሚያዩዋቸው፤ ባንድ ስምም ነበር የሚጠሯቸው:: ኦቶማንም ሆነ ግብፅ ለ19ኛው መቶ ዓመት ኢትዮጵያውያን «ቱርክ» ነበሩ::

ምዕራፍ ሁለት

# አንድነትና ነፃነት
# 1847 - 1888

## የመጀመያው ሙከራ፤ ካሣ ቴዎድሮስ

የውስጡንም ሆነ የውጪውን አደጋ፣ የሚፋለሙትን መሳፍንትም ሆነ የ«ቱርኩ»ን ከበባ፣ በቅጡ ተረድቶ ለመቋቋም የመጀመሪያውን ሙከራ ያደረገው ካሣ ኃይሉ ነው:: በ1847 «ዳግማዊ ቴዎድሮስ» ተብሎ ዙፋኑን ሲጨብጥ የዘመናዊት ኢትዮጵያን ልደት አበሰረ ተብሎ የሚገመተውም ለዚህ ነው:: ካሣ «ቴዎድሮስ» ለመሆን የበቃው በነበሩት ልዩ የግል ባሕርያቱ ነበር:: ራሱን አንድ ዐቢይ ተልዕኮ ለመፈጸም የታጨ አድርጎ ማየቱ፣ ወታደራዊ ችሎታውና ጀግንነቱ፣ እንዲሁም ደፋርነቱና አዲስ ሐሳብ ተቀባይነቱ ነበሩ:: ራሱን በራሱ ከሽፍትነት ወደ ዐፄነት ለማሸጋገር የቻለ ሰው ነበር:: በዘመነ መሳፍንት ተወልዶ የዘመነ መሣፍንት ማርከሻ ለመሆን በቃ::

ይሁን እንጂ ቴዎድሮስ ከጨረቃ የመጣ ሰው አልነበረም:: ትውልዱና ዕድገቱ ለኋላው የፖለቲካ ሕይወቱ መጠነኛም ቢሆን አስተዋፅዖ አድርገዋል:: ለሥልጣኑ መቆናጠጫና ለዘመኑ ፖለቲካም መለማመጃ ትምህርት ቤት የሆነውን ቋራን (ምንም እንኳ ኋላ በራሱ ኃይል ቢያደላድለውም) ከመነሻው ባለቤትነቱን ያወጀው የቤተ ዘመዱ ግዛት ስለሆነ ነበር:: በመቶኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ ከነበሩት የዘመነ መሳፍንት ተዋንያን አንዱ የደምቢያው ገዥ ደጃች ማሩ የካሣ ዘመድ ሲሆን ቋራን ጨምሮ በየቦታው ተበታትነው የሚገኙት ግዛቶችም በጥቅል «የማሩ ቀመስ» ተብለው ይታወቁ ነበር:: ደጃች ማሩ በ1820 «በኮሶ በር ጦርነት» ላይ ሲወድቅ ግዛቱ ወደ ደጃች ክንፉ ተላለፈ:: በጐንደር የተወለደውና አንዳንዴ ካሣ ማሩ እየተባለ ይጠራ የነበረው ካሣ ኃይሉም ወደ ቋራ የሄደው ከዚሁ ከኮሶ በር ጦርነት በኋላ ነው::

ካሣ ቋራ በደጃች ክንፉ ቤት አደገ:: በዚህን ጊዜ ከላይ እንደጠቀስነው ግብፆች ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ለመስፋፋት የሚያደርጉትን ጥረት በብርቱ ይፋለሙ ከነበሩት መሳፍንት አንዱ ደጃች ክንፉ ነበር:: በ1829 «ወድ ከልተቡ» በተባለ ሥፍራ በግብፅ ጦር ላይ ትልቅ ድል በመጎናፀፉም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ስመ ጥር ሆኖ ነበር:: የአባቱ ልጅ ለሆነው ለካሣ ግን ብዙም ፍቅር አያሳየውም ነበር:: የዚህም ምክንያት ክንፉ ካሣን የልጆቹ ጣውንት አድርጎ ስላየው እንደነበር ይገመታል:: ክንፉ «የማሩ ቀመስ»ን ለልጆቹ ለማውረስ ለነበረው ጽኑ ፍላጎት ካሣን እንቅፋት ሆኖ ስላየው የሚመለከተው በክፉ ዓይን ነበር:: የማታ ማታ ግን ያ ሁሉ ልፋትና ጠላትነት ከንቱ ሆነ:: ክንፉ እ.ኤ.አ. በ1839 ሲሞት «የማሩ ቀመስ» ለክንፉ ለልጆችም ሆነ ለካሣ አልሆነም:: የራስ ዓሊ እናት እቴጌ መነን ወረሰችው:: ያኔ ነው ካሣም በሥርዓት

ያጣውን ግዛት በጉልበቱ ለማግኘት የሽፍትነትን ጎዳና የመረጠው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌሎች እንደሱ ያኮረፉ ባለሟሎችንና ተራ ቀማኞችን እየመራ በቋራ በረሃ መንቀሳቀስ ጀመረ::

የካሣ ስብዕና የታነፀው በዚህ የሽፍትነት ዘመኑ ነው ቢባል እምብዛም ከእውነት የራቀ አይሆንም:: ዘላቂ የሆኑት የካሣ ባሕርያት ቅርፅ የያዙት በዚሁ ዘመን ነበር:: ከነዚህም ባሕርያት አንዱ ምቾትና ብልጭልጭ ነገር አለመውደድ ነው:: ካሣ፣ ኋላም ቴዎድሮስ፣ የወታደሮቹን ኑሮ የሚጋራ መሪ ነበር:: እንደገበሬ አርሶና ዘርቶ እንደ ወታደር ይዋጋ ነበር:: ሌላው ባሕሪው ደግሞ ለፍትሕና ለእኩልነት መቆርቆር ነበር:: እንደ ዝነኛው የእንግሊዝ ሽፍታ ሮቢን ሁድ ካሣም ከነጋዴዎች የዘረፈውን ገንዘብ ለገበሬዎች ማረሻ መግዣ ብሎ ይለግስ ነበር:: በኋላ ክፉ መዘዝ ያመጣበትን የቤተ ክህነትን መሬት ወርሶ ወታደሮቹን ለመቀለብ መሞከሩም የዚሁ የማደላደል ስሜት አንዱ ነጸብራቅ ነው::

ከሁሉም በላይ፣ካሣ በሽፍትነት ዘመኑ ነው ከግብፆች ጋር መጋጨት የጀመረው:: ቱርክ ብሎ ከሚጠራቸው ጋር ያደረገው የእድሜ ልክ ፍልሚያና ኢየሩሳሌምን ከነሱ ነፃ አወጣለሁ የሚለው ሕልምም የተፀነሰው እዚሁ ኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ላይ ነው:: በሕይወቱ ሽንፈትን ያላወቀው ካሣ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ማለት ይቻላል* ወታደራዊ ሽንፈት የቀመሰው በ1840 ደባርቂ በምትባል ሥፍራ ነው:: ጭፍን ድፍረትን እንጂ የጦር ሥልትና ዘመናዊ መሣሪያን ያልታደለው የካሣ ሠራዊት በግብፅ መድፍ እንደ ጭዳ ታረደ:: ካሣም ለካ ይኸም አለ ብሎ የወደፊት አቀጣጫውን ለማስላሰል ተገደደ:: ስልፍና መድፍ፣ እነዚህ ሁለቱ ካሣ ከደባርቂ ሜዳ ያገኛቸው ዐቢይ ትምህርቶች ነበሩ:: እነሱን ያልያዘ ሠራዊትም የድል ተስፋው የመነመነ መሆኑን ተረድቶ ሁለቱንም በጁ ማድረግ የእድሜ ልክ ጥረቱ ሆነ:: መጀመሪያ በግብፆች በኋላ ደግሞ በልብ ወዳጁ በእንግሊዛዊው ጆን ቤል (በኢትዮጵያዊ አጠራሩ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ) አማካይነት ሠራዊቱን ስልፍና የውጊያ ስልት ማስተማር ጀመረ:: ካሣ ለመድፍ ያለው አክብሮትም ደባርቅ ሜዳ ላይ ተረግዞ «ሴባስቶፖል» ብሎ የጠራው መድፉ ጋፋት ፋብሪካ ሲሠራ ታላቅ ልደቱን አገኘ:: ዳሩ ግን ያ ቴዎድሮስ የተመካበት መድፍ፣ ያ ከደብረ ታቦር እስከ መቅደላ አፋፍ በስንት አሳር ተጎትቶ የተወሰደው መድፍ፣ በእንግሊዞች ላይ ሳይሆን አበሻ መሀል ፈነዳ:: ቴዎድሮስም የሕይወቱን ከንቱነት፣ የሕልሙን ቅዠትነት በዚሁ ተረዳ::

የካሣ ስምና ዝና በቋራ አካባቢ እየገነነ ሲሄድ ባለ ሥልጣኖቹን ራስ ዓሊንና እናቱን እቴጌ መነንን ማሳሰብ ጀመረ:: ከኃይል ዘዴ ይሻላል ብለውም በጦር ያገኘውን የቋራን ግዛት መረቁለት:: በጋብቻ ለማሰርም የዓሊን ልጅ

*እንግሊዞች በቴዎድሮስ ላይ መቅደላ ላይ ያገኙትን ወታደራዊ ድል እንደ ድል መቁጠር ያስቸግራል:: በዚያን ጊዜ ቴዎድሮስ ያለቀለት ስለነበር እንግሊዞች ያለ ጠላት ተዋጉ ማለት ይቀላል::




ተዋበችን ዳሩለት:: ካሣ ለተዋበች ያለው ፍቅር ቋሚ የሆነውን ያህል ከአባቷና እናቷ ጋር ያደረገው እርቅ ግን ውሎ አላደረም:: ዜና መዋዕል ጸሐፊው ዘነብ እንደሚተርክልን በየጁ ቤተ መንግሥት በደልና ንቀት ቢበዛበት ካሣ እንደገና የሽፍትነት ኑሮውን ቀጠለ:: ዓሊና መነንም ካሣን ለማንበርከክ ጦር መላክ ያዙ:: የተላከው ሁሉ ግን የሽንፈት ጽዋን እየቀመሰ መመለስ ሆነ:: ከሁሉም ተረት ሆኖ የቀረው «ይኸን የኮሶ ሻጭ ልጅ አንጠልጥዬ አመጣለሁ» ብሎ የፎከረውና ተሸንፎና ተማርኮ የፋከራ ቃሉን በመራራ ኮሶ እንዲውጥ የተገደደው ደጃች ወንድይራድ ነበር:: ምርኮ ግን ለንግሥቲቱ ለመነንም አልቀረላትም:: ጦሯ በካሣ ጦር ተበትኖ ንግሥቲቱም ለጥቂት ቀናት የካሣ ምርኮኛ ሆኖ ነበር::

እነዚህ የመጀመሪያ የካሣ ድሎች ኋላ በዘመነ መሳፍንት አውራዎች ላይ የተጎናፀፋቸውን ተከታታይ ድሎች የሚያበስሩ ነበሩ:: የካሣን የጦር ጥበብ ባጎሉት በነዚህ ድሎች አማካይነትም የዘመነ መሳፍንት መሪ ተዋንያን በሚያስገርም ፍጥነት አንድ ባንድ ድል ሆኑ:: መጀመሪያ ጉር አምባ ላይ (ኅዳር 19፣ 1945) የራስ ዓሊ ታዛዥ የነበረው የጎጃሙ ደጃች ጎሹ ወደቀ:: ይህ ጦርነት ከጐንደር ብዙም ባልራቀ ሥፍራ ላይ መደረጉ ካሣ ከመከላከል ወደ ማጥቃት መሸጋገሩንና የመጨረሻ ኢላማውም የነገሥታቱ መዲና መሆኑን አመለከተ:: ከአንድ አምስት ወር በኋላ፣ በሚያዝያ 5 ቀን ደግሞ ካሣ አራት የራስ ዓሊን ደጃዝማቾች «ጎርጎራ ብቸኝ» በተባለ ጦር ሜዳ ላይ አሸነፈ፤ ከነዚህ ሁለቱ እዚያው ጦር ሜዳው ላይ ሞቱ:: ራስ ዓሊ እንዲህ እርቃኑን ከቀረ በኋላ የካሣን ጦር መመከት አልቻለም:: በሰኔ 26 ቀን አይሻ ላይ ጦሩ ተበትኖ እሱም ወደ እናት ሀገሩ የመመለስ ያህል ወደ የጁ ግዛት ማምለጥ ነበረበት:: ከዚህ በኋላ በካሣና በዙፋኑ መካከል የነበረው መሰናክል አንድ ብቻ ነበር፣ የስሜኑ ደጃች ውቤ:: እሱም በየካቲት 3፣ 1847 ደረስጌ ላይ የሽንፈት ጽዋ ቀመሰ:: ካሣ ለመንገሥ ወደ ጐንደር መመለስ አለብኝ ብሎ አላመነም:: እዚያው ደረስጌ ላይ ውቤ ባሳነፀው የማርያም ቤተ ክርስቲያንና ከግብፅ ባስመጣው ጳጳስ በአቡነ ሰላማ አማካይነት «ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» ተባለ::

እንደ ዘመነ መሳፍንት የፖለቲካ ባህል ቢሆን ኖሮ ቴዎድሮስ የሰሜን ኢትዮጵያን መሳፍንት አንድ ባንድ ድል አድርጎ ዘውድ ሲቀዳጅ «የፈለግሁት ተሟላልኝ» ብሎ በተዝናና ነበር:: ግን እሱ በዚህ በቃኝ አላለም:: በደረስጌ ማግስት ግንባሩን ወደ ወሎና ወደ ሸዋ አዞረ:: በዚህ ድርጊቱም በሰሜን ኢትዮጵያ አድማስ ተከልሎ የነበረውን የዘመነ መሳፍንት ፖለቲካ እንደማይታጠፍ አድርጎ አሰፋው:: የቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ አንዱ ትልቅ ውጤት ያንን ከጐንደር ፖለቲካ ገሸሽ ብሎ የነበረን ግዛት በማያሻማ ሁኔታ ወደ ማዕከሉ ጎትቶ ማስገባቱ ነው:: ይህ ሂደት ቀጥሎና አድጎ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲሆን ሸዋ ከድንበር ግዛትነት ወደ ማዕከልነት ልትሸጋገር በቃች::

ከሸዋ በፊት ግን ቴዎድሮስ ወሎን ማስገበር ነበረበት:: በዘመኑ ከነበረው ልምድ አንፃር የቴዎድሮስ የወሎ ዘመቻ እጅግ የተራዘመ ነበር:: ኩዳዴና ክረምት ያላገደው ስድስት ወር ያህል የፈጀ ዘመቻ ነበር:: የወሎዬዎች



2.1 «ሴባስቶፖል» የተባለው የዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ በመቅደላ አቀበት ላይ ሲጎተት

አይበገሬነትና የቴዎድሮስም ጨካኝነት አፍጠው መውጣት የጀመሩት በዚሁ ዘመቻ ነበር:: በፖለቲካዊም ሆነ በአካላዊ አነጋገር ወሎ የቴዎድሮስ መቀበሪያ ሆነች:: ጉድጓዱን መማስ የጀመረው ግን እሱ ራሱ ከዚሁ ከመጀመሪያው ዘመቻ ጀምሮ ነው:: መቀጣጫ ይሆናል ብሎ የጀመረው እጅና እግር የመቁረጥ ፌሊጥ የማታ ማታ ሰፊ የሕዝብ አመፅ አስነሣበት:: ዘመቻው በመስከረም መጀመሪያ ላይ መቅደላ ሲያዝ ለጊዜው አበቃ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው መቅደላና የቴዎድሮስ ሕይወት መያያዝ የጀመሩት:: መቅደላ የቴዎድሮስ የዘመናዊ መንግሥት መፈተኛ ላቦራቶሪ ነበረች:: መቅደላ ቴዎድሮስ በግራ በቀኝ ከተዋከበና ድፍን ኢትዮጵያ ካመፀበት በኋላ ቁስሉን እንደሚልስ አንበሳ ያፈገፈገባት ዋሻው ሆነች:: ከሁሉም በላይ መቅደላ በ1860 የእንግሊዝ ወታደሮች እጁን ለመያዝ ሲጣደፉ የተከታይ ትውልድን ስሜት በማረከና እስካሁንም በሚማርክ ድርጊት የገዛ ሕይወቱን ያሳለፈባት መድረክ ነች::




አምስት ወር ያህል የፈጀው የሸዋው ዘመቻም እንደ ወሎው የተራዘመ ነበር:: መንዝ፣ ግድምና ኤፍራታ አሜን ብለው ሲቀበሉ የቀሩት የሸዋ ግዛቶች ከሣህለ ሥላሴ ልጆች አንዱ በሆነው ሠይፉ እየተመሩ ተቃውሟቸውን ቀጠሉ:: በዚህ ሁሉ መሀል ንጉሡ ኃይለ መለኮት በድንገተኛ ሕመም ሲሞት የቴዎድሮስና የሸዋ መኳንንት ዓይን በንጉሡ ልጅ በምኒልክ ላይ አተኮረ:: ቴዎድሮስ ምኒልክን ለመያዝ ሲያባርር መኳንንቱ ላለማስያዝ ሲሸሹ ቆይተው በኅዳር 1848 «በረከት» ላይ ቴዎድሮስ ድል አድርጎ ንጉሣዊ ምርኮውን ይዞ ተመለሰ:: በሸዋም ላይ የኃይለ መለኮትን ወንድም ኃይለ ሚካኤልን በመርዕድ አዝማችነት ማዕረግ ሾመው:: ቴዎድሮስ የሸዋ መሳፍንት ከሣህለ ሥላሴ ጀምሮ የሚጠሩበትን የንጉሥነት ማዕረግ ሽሮ ቀድሞ ይጠሩበት የነበረውን ዝቅተኛውን የመርዕድ አዝማችነት ማዕረግ እንደገና ማደሱ የወደፊት ዓላማውን የሚጠቁም ነው:: «በኢትዮጵያ ምድር ካንድ በላይ ንጉሥ አይኖርም፤ ያም ንጉሥ እኔ ነኝ» ለማለት የፈለገ ይመስላል:: ይሁንና የቴዎድሮስ የሸዋ ድል ጊዜያዊ ነበር:: ገና ፊቱን መለስ ከማድረጉ ሠይፉ ሣህለ ሥላሴ አመፁን ቀጠለ:: በጎጃምና በስሜንም ቴዎድሮስን የጠበቀው አመፅ ነበር:: ስለሆነም የቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ የመጀመሪያው ምዕራፍ ወታደራዊ ድሎቹ ሁሉ ማሳረጊያ የሆነውን ያህል የውድቀቱም መጀመሪያ ነበር ማለት ይቻላል:: ታሪክ በእንዲህ ዓይነቱ እንቆቅልሽ የተመላች ናት::

## ቴዎድሮስና ዘመናዊ ሥልጣኔ

ፕሮፌሰር ዶናልድ ክራሚ የቴዎድሮስን ሕይወትና ገጸ ባሕርይ ሲገመግም «ማብራራቱና መተንተኑ ቢጎለውም የዘመናዊ ሥልጣኔ ሐሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር» በማለት ጽፏል:: ይህ ማለት ከቴዎድሮስ በፊት የነበሩት ነገሥታትና መሳፍንት አንዳንድ የዘመናዊ አሠራር ሐሳቦች ሳይገለጽላቸው ቀርቶ ነው ማለት አይደለም:: እንደ ቴዎድሮስ ግን በስፋትና ያለመታከት ሐሳቡን ግብ ለማድረስ የጣረ ንጉሥ አልነበረም:: ይሁን እንጂ ቴዎድሮስ ሀገሪቷን በዘመናዊ መንገድ ለመምራት የሚያስችለውን ንድፍ በደንብ ካለመቀረፁም ሌላ በሚወስዳቸው ተቃራኒ እርምጃዎች ምክንያት ከዓላማው ሊደናቀፍ በቃ:: የሚያደርጋቸውም የለውጥ ሙከራዎች በዳበሳ እንጂ ሁለገብ የሆነ የለውጥ ፕሮግራም ተከትሎ አልነበረም:: ከዘመነ መሳፍንት የወረሰው ማህበራዊና ፖለቲካዊ መዋቅር ብዙም ሊያራምደው አልቻለም:: ስለሆነም የጀመራቸው ወታደራዊና አስተዳደራዊ ለውጦች የኤኮኖሚና የቴክኖሎጂ መሠረት ስላልነበራቸው አየር ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ:: የአውሮጳውያንን የቴክኒክ እርዳታ ለማግኘት አጥብቆ ቢማፀንም የሚሰማው አላገኘም:: በመጨረሻም ቴዎድሮስ ብቸኛና ግራ የተጋባ የለውጥ ሐዋርያ ሆኖ ቀረ::

ቴዎድሮስ ይከተል የነበረውን የአስተዳደር ፖሊሲ ስንመረምር ባንድ በኩል የዘመነ መሳፍንት ማነቆ ምን ያህል ጠንካራ እንደነበርና በሌላ በኩል



2.1 «ሴባስቶፖል» የተባለው የዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ በመቅደላ አቀበት ላይ ሲጎተት

ደግሞ ቴዎድሮስም ራሱ ተለዋዋጭ እንደነበር እንረዳለን:: እንደሚታሰበውና እንደሚነገረው ቴዎድሮስ የአካባቢ ሥርወ መንግሥታትን በደፈናው አልሻረም:: እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ ከነዚያው ሥርወ መንግሥታት አባላት ውስጥ በተቻለ መጠን ተቀናቃኝ የማይሆኑትን እየመረጠ የአባቶቻቸውን ግዛት መረቀላቸው:: ለምሳሌም ትግሬ ላይ የአጋሜውን መሪ የደጃች ሱባጋዲስን ልጅ ካሣን ሲሾም፣ ወሎ ላይ ደግሞ በተከታታይ የአካባቢው መሪዎች ተወላጆች የሆኑትን ደጃች ሊበን አመዴንና አመዴ ዓሊን (የታወቀችው የወርቂትን ልጅ) አስቀመጠ:: መቅደላን ብቻ ምናልባት ለራሱ የዘመናዊ አስተዳደር ዓላማ እንዲመቸው ብሎ ከቅርብ ተከታዮቹ አንዱ ለሆነው ለግራዝማች ዓለሜ ሰጠ:: በሸዋም ቢሆን ምንም እንኳ ቀርቶ የነበረውን የመርዕድ አዝማች ማዕረግ እንደገና ሥራ ላይ በማዋል የሸዋን መሳፍንት ልካችሁን ዕወቁ ያለ ቢመስልም፣ ኃይለ ሚካኤልን በመሾሙ የሣህለ ሥላሴን ሥርወ መንግሥት አጸደቀው እንጂ አልሻረውም:: ለአካባቢ ገዢዎች ከመጀመሪያው ሥልጣን ላለመስጠት የወሰነው በጎጃም ብቻ ይመስላል:: ቴዎድሮስ ከጦር መሪዎች አንዱ የሆነውን እንግዳን ነው በራስነት ማዕረግ የጎጃም ሹም ያደረገው::

ይህ ቴዎድሮስ የተከተለው የአስተዳደር ፖሊሲ በደፈናው ሲታይ የዘመነ መሳፍንትን የመከፋፈል ስሜት የሚያጠናክር መስሎ ይታያል:: ከዘመነ መሳፍንት ግን የሚለይበት አንድ ዋነኛ ጉዳይ አለ:: ይኸውም ከቴዎድሮስ በፊት ገነው የነበሩት መሳፍንት የጐንደሩ ንጉሠ ነገሥት ያጸደቃቸው ሳይሆን በራሳቸው ጉልበት ግዛታቸውን የያዙ ሲሆኑ በቴዎድሮስ ዘመን ግን በአካባቢያቸው የፖለቲካ መሠረት ቢኖራቸውም በንጉሠ ነገሥቱ የተሰየሙ መሆናቸው ነው:: ይሁንና ቴዎድሮስ የራሴ ሰዎች ናቸው ያላቸው ታማኝ ሆነው አልተገኙም:: ቀደም ያለ የፖለቲካ መሠረት የነበራቸው ሹማምንትም ለማመፅ አልቸኮሉም:: ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ እንግዳና ዓለሜ ቴዎድሮስን ከዱ:: በተለይም የዓለሜ መክዳት ቴዎድሮስን በጦር ፍላፃ የተወጋ ያህል እንደተሰማው ሲነገር የቆየ ነው:: ባንፃሩ የሸዋው መርዕድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል ዓመታዊ ግብሩን በሥርዓት እንደከፈለ ኖረ:: ደጃች ካሣ ሱባጋዲስ ደግሞ ከዚህም የላቀ የታማኝነት ተግባር ፈጸመ:: በቴዎድሮስ ላይ አምፆ ከነበረው ከስሜኑ አገው ንጉሤ ተከታዮች አንዱ ጌታውን ያስደሰተ መስሎት የቴዎድሮስን አንገት ቆርጬ አመጣልሃለሁ ብሎ ፎክሮ ነበር:: ቀን ሲጥለው ይኸው ፎካሪ በካሣ እጅ ወደቀና ካሣም ያን የለፈለፈበትን ምላስ ቆርጦ ለቴዎድሮስ ላከለት:: ካሣ ይህን ሲያደርግ ባንድ በኩል ለደጃች ውቤ ተወላጅ ለሆነው ለአገው ንጉሤ ያለውን ጥላቻና በሌላ በኩል ደግሞ ለቴዎድሮስ ያለውን ባለውለታነት ለመግለጽ የፈለገ ይመስላል:: የደጃች ውቤ እስረኛ ሆኖ ወገቡ እስኪጎብጥ የማቀቀውን ካሣን ከደረስጌ ድል በኋላ ከእስር ነፃ ያወጣው ቴዎድሮስ ነበርና::



ቴዎድሮስ ከትግራይ የሚያገኘው ግን ለፍላፊ ምላስ ብቻ ሳይሆን በብዙ መቶ ሺ ብር የሚቆጠር ግብርም ነበር:: እንዲያውም ዋና የገቢ ምንጩ የሚመጣው ከዚሁ አካባቢ ነበር ማለት ይቻላል:: በቅርብ የተገኙ የቴዎድሮስ የግምጃ ቤት ሰነዶች እንደሚያስረዱት በያመቱ ወደ ሁለት መቶ ሺ ማርትሬዛ ብር የሚጠጋ ገቢ ያገኝ ነበር:: ይህም ከበጌምድር ከሚያገኘው ሃምሳ ሺ ብር ሲነፃፀር አራት እጅ የላቀ ሆኖ እናገኘዋለን:: ከዚህም ውስጥ ከሠላሳ አምስት ሺ ብር በላይ የሚመጣው የቴዎድሮስን ልጅ አልጣሸን ካገባው የሽሬና ዐድዋ አካባቢ ገዥ ከደጃች ባርያው ጳውሎስ፣ ሠላሳ ሁለት ሺ ያህል ከሐማሴንና ሠራዬ ገዥ ከደጃች ኃይሉ ተወልደ መድኅን፣ ከአሥራ ሰባት ሺ በላይ ደግሞ ከአካለ ጉዛይ ሹም ከባሻ ገብረ እግዚ ነበር::

የቴዎድሮስ ለውጥ የማምጣት ፍላጎት ጎልቶ የወጣው ከአስተዳደር መስክ ይልቅ በወታደራዊ መስክ ነው:: ወታደራዊ ኃይልና የፖለቲካ ሥልጣን ምንጊዜም ተወራራሽ በመሆናቸው፣ አገር አሠለጥናለሁ ያለ መሪ ሁሉ መጀመሪያ የሚያተኩረው በጦር ሠራዊቱ እንደሆነ ተደጋግሞ የታየ ነገር ነው:: ከቴዎድሮስ ቀደም ብለው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት እንኳ ከአውሮጳውያን ነገሥታት ጋር ያደረጓቸው የደብዳቤ ልውውጦች እንደሚያሳዩት የመጀመሪያ ጥያቄያቸው ከዘመናቸው ወታደራዊ ቴክኖሎጂ እንዲያቋድሷቸው ነው:: የዘር ሐረግ መዞ ሳይሆን በወታደራዊ ጡንቻ ሥልጣን ለተቀዳጀው ቴዎድሮስ የወታደራዊ ኃይል ወሳኝነት ከቶ የተሰወረ ሊሆንበት አይችልም:: ስለዚህም ሥልጣኑን ለማዳበር ሠራዊቱን በሦስት አቅጣጫዎች ማሻሻል አለብኝ ብሎ ተነሣ፤ በአደረጃጀት፣ በሥነ ሥርዓትና በጦር መሣሪያ:: ይሁንና በሌሎች መስኮች እንደታዩት ሁሉ በዚህም መስክ ቴዎድሮስ ያደረጋቸው የመሻሻል ሙከራዎች ቀጣይነትና ሁለገብነት የጎደላቸው ነበሩ::

በአደረጃጀት በኩል ቴዎድሮስ ለማድረግ የፈለገው ዐቢይ ለውጥ ተጠሪነታቸው ለመሳፍንቱ የነበረውን የተበታተኑትን ሠራዊቶች ባንድ አገር አቀፍ ብሔራዊ ሠራዊት መተካት ነው:: በዚህም መሠረት ከተለያዩ ግዛቶች የመጡ ወታደሮች ባንድ ሬጅመንት ተሰልፈው እንዲዋጉ በማድረግ ከጠባብ የአካባቢ ስሜት ተላቀው ሰፋ ያለ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ሞከረ:: ከዚያም በላይ የዐሥር አለቃ፣ ያምሳ አለቃ፣ የሺ አለቃ የሚባሉ አዳዲስ የማዕረግ ስሞች በመፍጠር እስካለንበት ጊዜ ድረስ በግልጋሎት የቆየውን የሥልጣን ተዋረድ መሠረተ:: ሌላው ቴዎድሮስ በአደረጃጀት በኩል ያመጣው ለውጥ ወትሮ ሠራዊቱን ያጅበው የነበረውን ጀሌ (የቤት ሠራተኛ፣ አሽከር፣ ወዘተ) በመቀነስ የሠራዊቱን በፍጥነት የመንቀሳቀስና ባጠቃላይም የውጊያ ችሎታ ማዳበር ነበር:: ስለልኩም ሆነ ስለአከፋፈሉ በውል የታወቀ መረጃ ባይኖርም ለሠራዊቱ ደመወዝ በመቁረጥ ወታደር በየባላገሩ ቤት የመምራትን አስከፊ ሥርዓት ለማስቀረትም ሞክሮ ነበር ይባላል:: በመጀመሪያዎቹ ዓመታት፣ የፍትሕ ስሜቱ በጭፍን ጭካኔ ከመታወሩ በፊት፣ ወታደሮቹ ገበሬውን ሲዘርፉ ያሰርጎራኌ ይቀጣል:: አንዳንዴ ወታደሮቹ ገበሬውን እየዘረፉ ቢያስቸግሩት ዙፋኑን ለመልቀቅም ይቃጣዋል፤ ሌላ ጊዜ ግን፣ የወሎ አማፅያን የሌሊት ዘቦቹን

ገድለው በቅሎዎቹን ቢነዱበት በበቀል እርምጃ ወታደሮቹ አካባቢውን እንዲዘርፉ ይፈቅድላቸዋል።

ሌላው እስከ መጨረሻው የቴዎድሮስን ሕሊና የማረከው ነገር ወታደራዊ ስነሥርዓት ነው። ከደባርቅ ውጊያ የቀሰመው አንዱ ትምህርትም ይኸው ነበር። ዳሩ ግን ሥነሥርዓትን በመቀጣጫነቱ እንጂ በአዎንታዊ ገጽታው ብዙም አልተገነዘበውም ነበር። በመጀመሪያው የወሎ ዘመቻው ወቅት የገዛ ወታደሮቹ ያለፈቃድ ተዋግተው ሰው ስለሞተና የጦር መሣርያ ቢማረክባቸው እጅና እግራቸው እንዲቆረጥ አዘዘ። ሸዋም ሲደርስ ዓመት ያህል በዘመቻ የቆየው ሠራዊት በመታከት ማጉረምረም ሲጀምር አርባ ስምንት የሚሆኑትን አኩሌታዎቹ በሰይፍ ተቆራርጠው እንዲሞቱ የቀሩት እንዲረሸኑ አደረገ። የአድማው ቀንደኛ መሪዎች የተባሉት ሁለቱ ደግሞ እጅና እግራቸው ተቆርጦ እንዲሰቀሉ አደረገ። ይህ ሁሉ መዓት የወረደው በሠራዊቱ መሀል «ንጉሡ ከሸዋም አልፈው ገና ኢየሩሳሌም ሊያዘምቱን ነው» የሚል ወሬ ስለተናኘ ነበር። በርግጥም በዚያን ጊዜ ከጐንደር ሸዋ ድረስ መጥቶ መዋጋት ኢየሩሳሌም ድረስ መሄድን መስሎ ሊታይ በመቻሉ የሠራዊቱ ሥጋት መሠረተ ቢስ አልነበረም። እንዲህ ዓይነቱ የመቀጣጫ እርምጃ ግን ስነሥርዓትን ሳይሆን አመፅን ነው የወለደው። በ1860 ቴዎድሮስ ለድል አድራጊው የእንግሊዝ ጦር መሪ ለሮበርት ናፒየር የጻፈው የስንብት ደብዳቤ ይህ ዕድሜ ልኩን የተመኘው ስነሥርዓት ምን ያህል የማይጨበጥ ጉም ሆኖበት እንደቀረ ያስረዳል። «ያገሬ ሰው ገብር፣ ሥራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በሥራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ»።

የቴዎድሮስ ወታደራዊ ለውጦች ሦስተኛ ገፅታ ደግሞ ሠራዊቱን በዘመናዊ መሣሪያ የማስታጠቅ ፅኑ ፍላጎት ነው። እርግጥ በግዥም ሆነ በምርኮ ቴዎድሮስ ብዙ የጦር መሣሪያ ማካበት ችሎ ነበር። የሱ ምኞት ግን ከውጭ የተሠራውን መሣሪያ በዚህም ሆነ በዚያ ማግኘቱ ሳይሆን ባገር ቤት ለማፍራት ነበር። ይህም ፍላጎት ገና በደባርቁ ውጊያ ማግስት ነበር ገሐድ የወጣው። የግብፆችን መድፍ አይበገሬነት በተከታዮቹ መስዋዕትነት ከተገነዘበ በኋላ ግንድ ፈልፍሎ ባሩድ በመቅበር ከሩቅ የሚፈነዳ መድፍ ለመሥራት ሞከረ። ይህንንም ሥራ ላይ ለማዋል እየተዘጋጀ እያለ ከወታደሮቹ አንዱ በጠላት እጅ ወድቆ ሲመረመር ሥቃይ ቢበዛበት ምስጢሩን ስላወጣ የዚህ የመጀመሪያ ሙከራ ውጤት ሳይታወቅ ቀረ። በኋላም ቴዎድሮስ የውጭ መንግሥታትን ያለመታከት ይወተውት የነበረው መሣሪያ ስጡኝ በማለት ሳይሆን ኢትዮጵያውያንን መሣሪያውን የመሥራት ጥበብ የሚያስተምሩ ጠቢባን ላኩልኝ እያለ ነበር።

የዚህ መሣሪያ የመፈብረክ የማይታጠፍ ዓላማ ማሳረጊያውም ጋፋት ሆነ። ደብረ ታቦር አጠገብ የምትገኘዋ ይህች ሥፍራ ከማንኛውም ሥፍራ ይልቅ የንጉሡ ዘመናዊ ሥልጣኔን የማስፋፋት ዕቅድ አምባ ሆነች። በተጨማሪም ጋፋት ንጉሡ ከአውሮጳውያን ሚሲዮናውያን ጋር የነበረው የሄድ መለስ ግንኙነት ነጸብራቅ ነበረች። ሚሲዮናውያኑ የመጡት ወንጌል እንሰብካለን፣ ፍቅር



እናስፋለን ብለው ነበር። ሺ ከአምስት መቶ ዓመት ክርስትናን ተቀብሉ በቆየ አገር ወንጌል እንሰብካለን ማለት ግን ለቴዎድሮስ አጉል መመጻደቅ ሆኖ ታየው። «እኔ የምፈልገው ሳይንሳችሁን እንጂ ሃይማኖታችሁን አይደለም» አላቸው። በጋፋት ትምህርት ቤት ከፍቶም ወጣት ኢትዮጵያውያንን የቀለምና የሙያ ትምህርት እንዲሰጧቸው አዘዘ። ሚሲዮናውያኑም የረሱትን የሳይንስ ትምህርት እየከለሱ ከብዙ ሙከራ በኋላ ንጉሡ የፈለጋቸውን መሣሪያዎች መስራት ጀመሩ።

ቴዎድሮስ ለዘመናዊ የጦር መሣሪያ ያለው ከፍተኛ ግምት መቅደላ ባቋቋመው መሣሪያ ግምጃ ቤት ይታይ ነበር። በሥርዓት የተጠበቁት ሰነዶች እንደሚያስረዱት በዚህ ግምጃ ቤት 15 መድፎች፣ 7 መንጀኒቆች፣ 11063 ልዩ ልዩ ጠመንጃዎች፣ 875 ሽጉጦችና 481 ሳንጃዎች፣ እንዲሁም 555 የመድፍና 83563 የቀላል መሣሪያ ጥይቶች ይገኙ ነበር። ይሁን እንጂ የጋፋት የዘመናዊ ሥልጣኔ መዲናነት ከጅምሩ ብዙ ለማለፍ አልቻለም። በዘመናዊ የእጅ ጥበብ የሠለጠኑ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ለማፍራት የነበረው ዕቅድ እምብዛም አልተሳካለትም። በሚሲዮናውያኑ የሚሠለጥኑት ከኅብረተሰቡ በሃይማኖት፣ በብሔረሰብ ወይም በኑሮ ደረጃ የተገለሉት ክፍሎች (ለምሳሌ ሙስሊሞች፣ ፈላሾች፣ የኦሮሞ የጦር ምርኮኞች) መሆናቸው ነገሩ ወትሮም ከነበረው የእጅ ሙያን ለተናቁ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከመተው ባህል ብዙም ራቅ እንዳላለ ያሳያል። በጋፋት መሣሪያ ፋብሪካ የተሠሩት መሣሪያዎችም በጦር ሜዳ ብዙም ለዩነት ማምጣት እንዳልቻሉ ቀደም ተብሎ እንደተገለፀው ከ«ሴባስቶፖል» ዕጣ ተረድተናል።

ሌላው ቴዎድሮስ ለውጥ ለማምጣት የፈለገበት ጉዳይ የባርያን ንግድ በተመለከተ ነበር። ከሸዋ ዘመቻ መለስ በጎጃም ሲያልፍ ባሶ ገበያ የተኮለኮሉትን ባርያዎች አይቶ ሁሉም አርነት እንዲያገኙ ካደረገ በኋላ ወዲያውኑ ቅጽበታዊ ውሳኔ ለመስጠት ባለው ልዩ ችሎታ ሴትና ወንድ እያፈጣጠመ አጋብቷቸዋል። ይህ በመላ ግዛቱ የባርያ ንግድ መከልከሉን የደነገገበት ዐዋጅ መቅድም ነበር። እንዲሁም በቃሉ (ወሎ) ወታደሮቹ በምርኮ ያገኟቸውን ባሮች እንዳይሸጡ አግዷቸዋል። የባርነትን ሥርዓት ግን ስር የሰደደ በመሆኑ ይመስላል ቴዎድሮስ ጨርሶ ለማስወገድ አልሞከረም። እንዲያውም የወሎው መሪ አመዴ በሽር አምፆ በሽምቅ ውጊያ ሲያዋክበው ተበሳጭቶ ወታደሮቹን የአመዴን ተከታዮች በሙሉ እየያዙ ለባርነት እንዲዳርጓቸው ፈቅዶላቸዋል።

በባህል ረገድ የቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የአማርኛ ቋንቋ ያበበበት ወቅት ነበር። የንጉሡን ደብዳቤዎች ከቀደሙት መሳፍንት ደብዳቤዎች ጋር ስናነፃፅር አማርኛ የቱን ያህል እንዳደገ መገንዘብ እንችላለን። በተለይም የዜና መዋዕል ጸሐፊው የደብተራ ዘነብ አማርኛ በቃላቱ ውበትም ሆነ ባጫጭር በረፍቀ ነገሮች ሐሳብን አሳምሮ የመግለጽ ችሎታው የዘመናችን የአማርኛ አጻጻፍ ስልት በር ከፋች ተብሎ ሊቆጠር ይችላል።

እንደማናቸውም ዘመናዊ ሥልጣኔን ሀገሩ ማስገባት የሚሻ መሪ ቴዎድሮስም ሥር ነቀል የሆኑ ለውጦች ለማምጣት ደልዳላ የፋይናንስ መሠረት እንደሚያስፈልግ ተገነዘበ:: ይህንን አደርጋለሁ እፈታለሁ ሲልም ነው ከቤተ ክህነት ጋር የተጋጨው:: ይህም ግጭት የፍጻሜው መጀመሪያ ሆነ:: ቴዎድሮስ ከጥንቱም ለካህናት ብዙ ፍቅር አልነበረውም:: «አረግራጊ፣ አቴና ወጊ፤ ወገቡን ሰባቂ» እያለ ይዘልፋቸውም እንደነበር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ወግ ነው:: ቴዎድሮስን የእግዚአብሔር መልእክተኛ አርጎ የሚያየውና ፕሮቴስታንት በመሆኑ ደግሞ ለካህናቱ ልዩ ጥላቻ የነበረው ዘነብ የንጉሡንና የካህናቱን ተፃራሪ ስነ ምግባር እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፤

> የዚህ ዘመን ካህናት በእውነት አልተከራከሩም ስለ ምድራዊ ንብረታቸው ነው እንጂ የነዚያስ ስራቸው ምንዝር አስማት ስካር:: የዚህን ዓለም ክብር ጌጥና ኩራት የማኅሌት ዘፈን ለሰው ለመታየት:: ብርን ለማግኘት ነው:: ቀን ቀን የሰውን ስራ ይሰራሉ የየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰብካሉ የሚሰማቸው የለም:: ሌሊት ከጋለሞታ ያድራሉና::... ይህንን ሁሉ ክፋት ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በሀበሻ ላይ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ ምንዝር የማይወድ:: ገንዘብ ሐሰት ሥርቆት የማይወድ ሽፍጥንም ሁሉ የማይወድ:: እግዚአብሔርን የፈራ:: እጅግ የሚሰጥ እንግዳ የወደደ ለታመመ የሚያዝን:: በአንዲት ሴት የቆረበ፣ [ዘነብ፤ 4-5]

በተጨማሪም ቴዎድሮስ የቤተ መንግሥትን ብቻ ሳይሆን የቤተ ክህነትንም አሐዳዊነት ለማረጋገጥ ታጥቆ የተነሣ መሪ ነበር:: ከዓላማዎቹ አንዱ ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል ክርስቲያኑን ሲያምስ የቆየውን የእምነት ልዩነት አስወግዶ ለቤተ መንግሥት ጠንካራ አጋር መሆን የምትችል ቤተ ክህነትን መመሥረት ነበር:: ለጥቂት ዓመታትም ይህ ዓላማው የተሳካ መስሎ ነበር:: እሱም ጳጳሱ አቡነ ሰላማ የሚከተለውን የተዋሕዶ እምነት ተቀብሎ፣ ጳጳሱም ቴዎድሮስ በጦር ኃይል ለያዘው ዙፋን ቡራኬውን ሰጥቶ፣ ጥቂት ዓመታት በስምምነት ቆዩ:: ግን ይህ የትብብር መንፈስ ዘለቄታ አላገኘም:: ቴዎድሮስ ከዜጎቹ ሁሉ የሚጠብቀውን ፍጹም ታዛዥነት ከካህናቱም ይጠብቅ ነበር እነሱ ደግሞ በአንደኛ ደረጃ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን ባዮች ስለነበሩ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቴዎድሮስና የካህናቱ ግንኙነት የማይፈታ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ቅራኔ ውስጥ ገባ:: ይህ የአስተሳሰብ ልዩነት የቂሶችን ጥምጥም አስመልክቶ በተነሣው ክርክር ተከሰተ:: ይህን ድራማ ደብተራ ዘነብ እንዲህ ሲል ይዘግበዋል፤

> ንጉሡ ካህናቱን ጥምጥም ጠምጥመው እንዳይቀርቡ በፊታቸው ከልክለው ነበርና፤ ካህናቱም ጥምጥም ክብራችን ነው ይበይኑልን



> አሉ:: ንጉሥ ቴዎድሮስም መለሱ አሉም ከታቦት በገባችሁ ጊዜ ስለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃላችሁ አሏቸው ካህናቱም እግዚአብሔር አድሮበታልና ብለን ነው አሉ:: ንጉሡም በኔ እግዚአብሔር አላደረብኝም:: እግዚአብሔር በእኔ አድሮ አይደለም የሚገዛ ባሉ ጊዜ:: ካህናቱም
>
> አዎን አሉ:: ንጉሡም እንግዲያው ምነዋ አሉ:: ያን ጊዜውንም እኔ ሥራት አስተምራችሁ ብዬ ነው እንጂ ጠምጥሙ ብለው በየኑላቸው:: [ዘነብ፤ 27]

ዋናው ግጭት ግን በመሬት ጉዳይ ነው የመጣው:: አሁንም ይህን መሠረታዊ የአመለካከት ልዩነት ዘነብ እንዴት አርጎ እንደሚያብራራው እንይ፤

> ከዚያም ወዲያ ካህናቱ ወደ ንጉሥ ቴዎድሮስ ጮኹ:: እያባትህ ብለው አዋጅ ተናገሩ እኛንም እንደ ጥንት እንደ ነገሥታቱ ያኑሩን አሉ:: ንጉሥ ቴዎድሮስም መለሱ አሏቸውም እኔ ምን ልብላ ሠራዊቴንስ ምን ላብላው:: እኩሌታውን የመስቀል መሬት እኩሌታውን እሪም ገዳም እያላችሁ ወስዳችሁት ባሉ ጊዜ:: አንዱ ካህን መለሰ አለም:: አራት ወር በጐንደር ተቀምጠው አርማጭሆን ጸገዴን ወልቃይትን ስሜንን ትግሬን ይብሉ አላቸው:: ዓራት ወር በዓሪንጎ ተቀምጠው በጌምድርን ላስታን የጁን ወረኢመኖን ወሎን ሸዋን ይብሉ:: ዓራት ወር ይባባ ላይ ተቀምጠው ሜጫን አገውን ዳሞትን ጐጃምን ይብሉ:: እንደ ጥንት ባለ ጊዜ ንጉሡ መለሱ አሉም:: እኔ ብቻዬን በሆንሁልሽ ጊዜ እንደ አጤ ኢያሱ በሻሽ አንቀሽ ልትገድይኝ::[ዘነብ፤ 28]

የካህናቱን ተቃውሞ በማጤን አራት ዓመት ካመነታ በኋላ ንጉሡ ካህናቱ ከሚያስፈልጋቸው በላይ ነው ብሎ የገመተውን መሬት በእጁ ብሎ በመውሰድ ለገባሮች አከፋፈለ::

## ቴዎድሮስና የውጭ አገር ሰዎች

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ቴዎድሮስን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ሥፍራ የሚያሰጠው የውስጥ ችግሮችን ለመፍታት ባደረገው ጥረት ብቻ ሳይሆን ከውጭ የሚመጣውን አደጋም ሆነ ዕድል ተረድቶ ዐጸፋውን በመመለሱ ነው:: በኢትዮጵያ ላይ የሚያንዣብቡ የውጭ ኃይሎች ሁለት ነበሩ፣ ግብፅና አውሮጳ:: ነገር ግን የውስጥና የውጭ ሁኔታዎቹ የተያያዙ እንደሆኑ ሁሉ የግብፅና

የአውሮጳ እውነታም ተደጋጋፊ ነበር። የቴዎድሮስ የውጭ ፖሊሲ መሠረት የአውሮጳን እርዳታ ማግኘት ነበር ቢባል ከውነት የራቀ አይሆንም። ንጉሡ የሚፈልጋቸውን የውስጥ ለውጦች ለማምጣትም ሆነ የ«ቱርክ»ን አደጋ ለመቋቋም ይህ እርዳታ ወሳኝ ነው ብሎ አመነ። ባንፃሩም አውሮጳውያን በዓለም አቀፍ ፖለቲካ ለቱርኮች የሚያደርጉት እርዳታ ከፍተኛ የመንፈስ ሽብር ፈጠረበት። እ.ኤ.አ ከ1853 እስከ 1856 በተደረገው በዓለም የታወቀው «የክራይሚያ» ጦርነት ክርስቲያኖቹ ፈረንሳይና እንግሊዝ ከሙስሊሙ የኦቶማን ቱርክ መንግሥት ጋር አብረው ኦርቶዶክስ የሆነችውን ሩሲያን እንዴት ሊወጉ እንደበቁ ከቶ ሊገባው አልቻለም። የቴዎድሮስ ስሌት የሃይማኖት ሲሆን፣ የአውሮጳ መንግሥታት ግን የቁሳዊ ጥቅም ነበር። ስለዚህም እነዚህ ለሩሲያ ያልተኙ ለኔስ ምን ያስተማምናሉ የሚል ሥጋት ቴዎድሮስን ያባንነው ነበር። የእንግሊዙን ቆንስል ካፒቴን ካሜሩንን አስሮ አገሪቱን ለወረራ ራሱንም ለሞት ያበቃው ከዚሁ ከ«ቱርኮች» ጋር ያሴሩብኛል ከሚል ጥርጣሬ ተነሥቶ ነው። ይህንንም ጥርጣሬውን ለእንግሊዝ መንግሥት ልዑክ ለካፒቴን ራሳም በ1858 በጻፈው ደብዳቤ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፤

> ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባላንጋራ ሁነውኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸውም በእግዚአብሔር ኃይል የምሠደውን በረከት ሎሌየን የሚቀበለኝ ሰው ይስደዱልኝ ብዬ የፍቅር ደብዳቤ ሠጥቼ (ካሜሩንን) ሰደድሁት። ከወዲያ ተላክሁ ብሎ የመጣበትን ከዚህ ተማክሮኝ የሄደበት ጉዳይ ትቶ ከቱርኮች ከማይወዱኝ ሰዎች ሂዶ ሲአዋርደኝ ሢንቀኝ ሰንብቶ መጣ። (Rubenson, *Acta II*, 284-285)

ቴዎድሮስ ለግብፆች የነበረው ከፍተኛ ጥርጣሬ የተፀነሰው በሽፍትነቱ ዘመን በድንበር ሲፋለማቸው ነበር። ከዚህም ጥርጣሬ የተነሣ ነው በ1849 ባልተለመደ ድፍረት ለጉብኘት የመጣውን የእስክንድርያውን ፖትርያርክ ቄርሎስና አቡነ ሰላማን ደርበ ያሰራቸው። የታሰሩበትም ምክንያት ንጉሡን ሳያማክሩ የግብፁ መሪ ለቴዎድሮስ ወታደራዊ እርዳታ እንዲልክ ስለጠየቁ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ግብፅ በሱዳን የነበራትን ሥልጣን ለማዳከም ቴዎድሮ በሌላ በኩል ደግሞ ግብፅ በሱዳን የነበራትን ሥልጣን ለማዳከም ቴዎድሮ ለሱዳን አማፅያን ድጋፍ ይሰጥ ነበር። ከዚህም አንዱ እ.ኤ.አ. በ1821 በግብፆ ላየ የተነሣውን አመፅ የመራው የመክ ኒምር ልጅ ወድ መክ ኒምር ይገኝበታል። እሱም ጥገኛ ከሆነበት ከኢትዮጵያ ምድር ወደ ሱዳን እየዘለቀ በቴዎድሮስ ስ ግብር ሁሉ ይሰበስብ ነበር። እያደር ግን የቴዎድሮስ ትኩረት በምዕራብ ጠረ ላይ ሳይሆን በምሥራቁ የባሕር ዳርቻ ላይ ሆነ። ምክንያቱም ከአውሮ የሚያገናኘው መሥመር ያ በመሆኑና እሱም በግብፆች ተጋርዶበት ስለነበ ነው። ለንግሥት ቪክቶሪያ በ1855 የጻፈው ደብዳቤ የሚያንጸባርቀውም ይህ የመከበብ ስሜት ነው። «ቱርኮች ከባህር ላይ ሆነው መልክተኛየን አናሳልፍ ብለው ቸግሮኝ ሳለ ቆንስል ኬምሮን መጣልኝ ወረቀትና የፍቅር በረከት ይዞ...



አሁንም መልክተኛየን ከቆንስል ኬምሮን ጋር የፍቅር በረከት ይዞ እንዳልሰደው ቱርኮች በባህር ላይ የማያስተላልፉልኝ ሆነ» (Rubenson, *Acta II*, 197-198) ፡፡

ቴዎድሮስ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር ወዳጅነት ለመመሥረት ፍላጎት ቢኖረውም ለእንግሊዝ የተለየ ፍቅር ነበረው። አሳዛኝ ዕጣውም ይህ የሱ ፍቅር በፀፋውን አለማግኘቱ ነው፤ እሱ ይውደዳቸው እንጂ እነሱ ብዙም አልተጨነቁለት። ይህን የመሰለ ለእንግሊዝ የተለየ አመለካከት ሊያድርበት የቻለውም ምናልባት ከሁለቱ እንግሊዛውያን ጆን ቤልና ዎልተር ፕላውደን ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ስለነበረው በዚሁ አማካይነት ይሆናል። ቤል ለንጉሡ ከመቅረቡ የተነሣ ሊቀ መኳስ ለመሆን የበቃ ነው። በ1840 የእንግሊዝ ቆንስል ሆኖ የመጣው ፕላውደንም እንዲሁ ለንጉሡ ቅርበት ነበረው። ሽፍቶ የነበረው የወንድሙ ልጅ ጋረድ ከንፉ በ1852 ፕላውደንን ሲገድለው ቴዎድሮስ በኃይለኛ ቁጣ ተነሥቶ ጋረድንና ተከታዮቹን ጨፍጭፏቸዋል። ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፈው ደብዳቤ እንዳስታወቀው «እነአቶ ቡላዲን (ፕላውደን) እና ሊቀ መኳስ ዮሐንስ... እጅግ እወዳቸው ነበረ የርስዎን ወዳጅነት ያገኘሁ እየመሰለኝ ሞት አይቀርምና የጠሉኝ ሰዎች እኔን ይክፋው ሲሉ ገደሉአቸው እኔም በእግዚአብሔር ኃይል ደመኞቼን አንድ ሳልተው ፈጀኋቸው የገዛ ዘመዶቼን»።

ካፒቴን ካሜሩንና ሌሎቹም አውሮጳውያን እስረኞች እንዲለቀቁ ሊደራደር ለመጣው ለእንግሊዛዊው መልእክተኛ ለሆርሙዝድ ራሳምም ቴዎድሮስ በ1860 የገለጸው ባንድ ወገን ለእንግሊዞች ያለውን ፍቅር በሌላው ደግሞ ከግብፆች ጋር ይመሳጠሩብኛል ብሎ በማመኑ ያደረበትን ቁጭት ነው። «ጥንት እንግሊዝ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ዘመድ ነበረ አሉ እኔም የጥንቱን ነገር እየሰማሁ እጅግ አጥብቄ እወዳችኋለሁ ዛሬ ግን ከቱርክ ጋራ አሙህ ጠሉህ ብለው ቢነግሩኝ እውነትን ይሆን ብየ ልቤ አወላወለብኝ» (Rubenson, *Acta II*, 312) የዚህ የፍቅርና የቁጭት ተቃርኖ ነው ቴዎድሮስን ከእንግሊዞች ያጋጨው። የታሪክ ምፀት ሆነና የልብ ወዳጄ ትሆነኛለች ብሎ ተስፋ የጣለባት አገር ደመኛ ጠላቱ ለመሆን በቃች።

ቴዎድሮስ የአውሮጳን የቴክኒክ ተራድኦ ለማግኘት ሳያቋርጥ የወተወተው የሀገሩን ኋላ ቀርነት አሳምሮ ስለተረዳ ነው። ከመረዳትም አልፎ መፍትሔውን ለማግኘት ሲል ለዓለም ሁሉ ለማወጅ የተዘጋጀ መሪ ነበር። በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም እንዲሉ የሀገሪቷን ኋላ ቀርነት፣ የሕዝቡን ድንቁርና፣ ለራሱም ባልሳሳ ቋንቋ ነበር የሚገልጸው። ይህንንም ለንግሥት ቪክቶሪያና ለራሳም በጻፋቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ተደጋግሞ እናገኘዋለን።

### ጥር 1858፤«የኢትዮጵያ ሰዎች ድንቁርነታችንን ዕውርነታችንን ሣይሰሙት አይቀሩም»

> መጋቢት 1858፤«አሁንም እኔ የምፈልገው እውር ነኝና ዓይኔ እንዲበራ ጥበብ ነው»
>
> ሚያዝያ 1858፤«የኢትዮጵያ ሰዎች እውር ነንና ዓይናችንን ያብሩልን እግዚአብሔር በሰማይ ያብራልዎ።»
>
> ሚያዝያ 1859፤«ከብት አለመፈለጌ ክብር ሁኜ አይደለም። ዕውር አህያ ነኝና ለጥበብ ዓይኔን ትከፍቱልኝ ብዬ ነው እንጂ በእግዚአብሔር ኃይል።» (Rubenson, *Acta II*, 266, 282, 296, 320)

እንዲሁም በ1858 የፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ የሆነውን ማርቲን ፍላድን ባለሙያዎች እንዲመለምልለት ወደ አውሮጳ ሲልክ ፈቃደኛ የሆኑ ጠቢባንን በሚገባ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን በማያሻማ ቋንቋ ለማሳወቅ መፈለጉን ከሚከተለው ማስተዋወቂያ እንረዳለን፤

> በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው የዳዊት የሰሎሞን ልጅ። ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ አቶ ፍላጥን በአይሮጳ ልኬ ሰድጀዋለሁ። ብልህ ሠራተኛ ፈልጌአለሁ። ከኔ የሚመጣን ሠራተኛ ሁሉ በደስታ እቀበላለሁ ቢኖርም ደስ አሰኘቼ አኖረዋለሁ። ብልሀቱንም አስተምሮ ወደ አገሬ እመለሳለሁ ቢል ደመወዙን ሠጥቼ ደስ አሰኝቼ እሰደዋለሁ። በእግዚአብሔር ኃይል የእግዚአብሔር እምነት ይሁንብኝ።
> (Rubenson, *Acta II*, 299)

ንጉሡ ከሚሲዮናውያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ስንመለከትም ለሱ ዋናው ቁም ነገር የአውሮጳን ቴክኖሎጂ ወደ ሀገሩ ለማስረፅ በሚያደርገው ጥረት ምን ያህል ያግዙኛል ወይ አያግዙኝም የሚለው ነበር። በዚህ ረገድ ለካቶሊኮቹ ብዙም ፍቅር አልነበረውም። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛ የካቶሊክ እምነት በሰሜን ኢትዮጵያ ሥር እየሰደደ በመሄዱ ሥልጣኔን ይጋሩኛል የሚል ሥጋት በቴዎድሮስ ዘንድ ስለተፈጠረ ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ ከፕሮቴስታንቶች ይልቅ ካቶሊኮች ከአንድ ኃያል መንግሥት (በተለይም ከፈረንሳይ ጋር) በቅርብ ስለተሣሠሩና ይህም የሀገሪቱን ነፃነት ለመተናኮል ያደፋፍራቸዋል የሚል ጥርጣሬ ስላደረበት ነው። ከዚያም በላይ በካቶሊክና በኦርቶዶክስ እምነት መካከል የነበረው ፉክክር አቡነ ሰላማንና የካቶሊኮቹን መሪ ጁስቲኖ ደ ዣኮቢስን ፊት ለፊት አጋጭቶ ነበር። ቴዎድሮስ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ከአቡኑ ጋር የትብብር ቃል ኪዳን ገብቶ ስለነበር በትሩን በካቶሊኮች ላይ ለማንሣት ተገደደ። በ1847 ደ ዣኮቢስ ካገር ሲባረር ኢትዮጵያውያን ተከታዮቹም ብዙ ጥቃት ደረሰባቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ካቶሊኮችና ፈረንሳዮች



የንጉሡ አውራ ጠላት ሆነው ለውድቀቱ ሌት ተቀን ይተጉ ጀመር። ለዚህም ኀላማቸው መሳካት ዓይነተኛ ተባባሪ ሆኖ ያገኙት ስሜነኛውን አገው ንጉሤን ነበር። ራሱን ንጉሥ ብሎ በመሰየም ለአመፁ ሞገስ ለመስጠት የሞከረው ንጉሤ ከፓሪስና ከቫቲካን ጋር የሞቀ ወዳጅነት ጀመረ። እነሱ በመሣሪያ ካገዙት የዙላን ወደብ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን እስከማረጋገጥ ደረሰ። ዳሩ ግን በ1853 ቴዎድሮስ በከፈተበት ዘመቻ ንጉሤ ሕይወቱ ስታልፍ፣ የሱና የካቶሊኮቹ ሰፊ ሰቅድ ተጨናግፈና ቀረ።

ከፕሮቴስታንቶቹ ጋር ግን ቴዎድሮስ በአብዛኛው ተወዳጅቶ ነበር። ለዚህም በቂ ምክንያቶች ነበሩ። አንዱ ምክንያት በጣም የሚያቀርባቸው ቤልና ፕላውደን ፕሮቴስታንት መሆናቸውና አቡኑም ቢሆን በልጅነቱ ግብፅ አገር በፕሮቴስታንት ሚሲዮን ትምህርት ቤት ተምሮ ያደገ መሆኑ ነው። ከዚያም በላይ የፕሮቴስታንቶች ዓላማ ባብዛኛው ኢትዮጵያውያንን ወደነሱ ዓላማ ከማስኮብለል ይልቅ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ተሐድሶ ለማምጣት መሆኑም በቴዎድሮስ ዘንድ ተቀባይነት አስገኝላቸው። እሱም ራሱ የሚፈልገው ከዚህ የራቀ አልነበረምና። በተጨማሪም ፕሮቴስታንቶች ከስብከት ባሻገር ጠቃሚ የሆኑ የእጅ ሙያዎች፣ እንደ አናጢነት፣ ግንበኝነትና የመሳሰሉ ለማስተማር ዝግጁ መሆናቸውም ጥበብን ለተጠማው ንጉሥ ማራኪነት ነበረው። ከዚህ ሁሉ የተነሣ ቴዎድሮስና ፕሮቴስታንቶች እጅግ ተቀራርበው በጋራ ቁርባን እስከማድረግ ደርሰው ነበር። ማየርና ቫልድማየር የተባሉት ሁለት ሚሲዮናውያንም ኢትዮጵያውያት አግብተው ነበር። ቫልድማየር ቴዎድሮስ ኀለም ሁሉ ከድቶት ብቻውን በቀረበት ጊዜ እንኳ አልተለየውም። አገሩን ለማደስ ከእግዚአብሔር የተላከ መስፍን አድርጎም ያየው ነበር። እንዲህም ብሎ ጽፎለታል፤

> ኃይልና ታላቅነት ሳያንሰው የምቾትና የቅምጥል ኑሮ የማያታልለው እንዲህ ያለ ንጉሥ ከቶ የት ይገኛል? የሁላችንም እምነት እግዚአብሔር ኃይሉን የለገሠው የሕዝቡንም ቁሳዊና መንፈሳዊ ደኅንነት ለማረጋገጥ የታጨ መሣሪያ መሆኑን ነው። (Crummey, *Priests & Politicians*, 126)

ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ፕሮቴስታንቶች ለቴዎድሮስ የተለየ አክብሮት ቢኖራቸውም እሱ ለደገሰላቸው የመሣሪያ መፈብረክ ሥራ ዝግጁ አልነበሩም። ተገደው እንጂ ፈቅደው አልሠሩለትም። የስብከት ሥራቸውንም ቢሆን በኦርቶዶክስ አማንያን ዘንድ እንዳያደርጉ ተከልክለው በፈላሻዎችና በመሳሰሉት ያልተጠመቁ ሕዝቦች ዘንድ ተወስነው ነበር። እንደ ደብተራ ዘነብ ያለ አንዳንድ ዋነኛ ሰዎችን ወደ እምነታቸው መቀየር ቢችሉም የካቶሊኮችን ያህል መስፋፋት አልቻሉም። የማታ ማታም ቴዎድሮስ በአውሮጳውያን ላይ በትሩን ሲያነሣ እነሱምን አልማራቸውም። እንዲያውም የንጉሡን ቁጣ ያነነፈለው በመጽሐፉ ውስጥ «ንጉሡ የኮሶ ሻጭ ልጅ ነው» ብሎ የጻፈው ሄንሪ

አሸተርን የተባለው ፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ ነው። በሱ የጀመረው እስራት ለሌሎቹም ሚሲዮናውያን ተረፈ።

## የቴዎድሮስ ፍጻሜ

ከዚህ በላይ እንዳየነው የንጉሡ የመጨረሻ ዓመታት በውስጥም ሆነ በውጭ ከዚህ በላይ እንዳየነው የንጉሡ የመጨረሻ ዓመታት በውስጥም ሆነ በውጭ
ዕልመትን የተላበሱ ነበሩ። በውስጥ ግዛት ከግዛት ሳይለይ አጠቃላይ አመፅ ተነሣበት። በውጭም ቢሆን እርዱኝ ብሎ እጁን ከዘረጋላቸው አወሮጳውያን ያገኘው መልስ ዝምታ ወይም ንቀት ብቻ ነበር። ከጭንቀትና ከመከፋት የተነሣ ጭካኔን መፍትሔ አድርጎ ያዘው። ጠላቱንና ወዳጁን መለየት አልቻለም። ይህም ሁኔታውን ሁሉም ላይ የቁጣው መቅሠፍት እኩል ወረደባቸው። ይህም ሁኔታውን አባባሰው። በውስጥ ጠላቶቹን ይበልጥ አበራከተበት፤ በውጭ ደግሞ ለፍቅርና ለወዳጅነት ደብዳቤዎቹ ደንታ ያልሰጡትን እንግሊዞች አስነሣበት። ሊረዱት ያልተዘጋጁት ሊያጠፉት ተነሡ። በነሱ ስሌት አወሮጳውያንን ለማሰር የሚጋበዝ የአፍሪቃ መሪ በቸልታ ሊታለፍ አይገባውም ነበር።

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ቴዎድሮስ ገና በ1847 ንጉሠ ነገሥት ከሆነ ጀምሮ አመፅ ተለይቶት አያውቅም። እስከ ዘመኑ ፍጻሜም አንዱን አመፅ አብርዶ ሳይጨርስ ሌላ እየተነሣበት ካንዱ ግዛት ወደ ሌላው እንደተንቀራጠጠ ነው ያሳለፈው። በጉጃም ተድላ ጓሉ የጎን አሾክ እንደሆነበት ቆየ። ወደ መናገሻ ከተማው ቀረብ ሲል ደግሞ የወልቃይቱ ጥሶ ጎበዜ የንጉሡን ሥልጣን እያዳከመ ይግረምህ ብሎ እንዴ ጐንደር ከተማን ለመያዝ በቃ። በላስታም ዋግ ሹም ጎበዜ (ኋላ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብሎ በቴዎድሮስ እግር የተተካው) አባቱ በቴዎድሮስ እጅ ሲገደል ካየ በኋላ ለመበቀልም ለሥልጣንም ሲል የአመፅ ባንዲራ አነሣ። በሸዋ ገና ከጧቱ ጀምሮ አልበገር ያለው ሠይፉ ሣህለ ሥላሴ ብቻ ሳይሆን ቴዎድሮስ ራሱ የሾመው በዛብህም ተነሣበት። በወሎም እንዲሁ የንጉሡ ሹም የነበረው የደጃች ሊበን አመዴ አመፅ አልበቃ ብሎ የአመዴ በሽር የደፈጣ ውጊያ ንጉሡን ይበልጥ ወደ ዕብደት ጐዳና መራው።

የፖለቲካ ዕድሉ እንዲህ አልሠምርለት ሲልና የሱም ቁጣ ቅጥ እያጣ ሲመጣ የቴዎድሮስ ሠራዊት እየመነመነ ሄደ። በ1858 ገደማ ሠራዊቱ እየከዳው ሲሄድ ቀድሞ በስድሳ ሺ ይገመት የነበረው ጦሩ ወደ ዐሥር ሺ አቆለቆለ። የንጉሡም የመንቀሳቀሻ ክልል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቶ በደብረ ታቦርና በመቅደላ መሥመር ተወሰነ። ይህም ቢሆን ባማፅያን ጥላ ሥር ወድቆ በ1860 መጀመሪያ ላይ ንጉሡ መቅደላ ላይ ለመመሸግ ተገደደ። ይህም ሽሽት የዓላማው መክሸፍ የመጨረሻው ምልክት ነበር። ኢትዮጵያን አንድ አደርጋለሁ ብሎ የተነሣው ጎበዝ ባንድ አምባ ተከተተ። በመጨረሻ ለእንግሊዙ የጦር መሪ ለሮበርት ናፒየር በጻፈው ደብዳቤ (የኑዛዜ ደብዳቤ ማለት ይቻላል) መቅደላን የአረማውያን ምሽግ ብሎ ይገልጸዋል። ይሁንና መቅደላ የቴዎድሮስን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ክስረት ብታመለክትም በተከታይ ትውልድ ላይ ከፍተኛ




ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ አሳድራለች። የቴዎድሮስ ሕይወት በሦስት ምዕራፎች ይጠቃለላል ማለት ይቻላል። እነሱም ቋራ፣ጋፋትና መቅደላ ናቸው። የመጀመሪያው ፖለቲካዊና ወታደራዊ መቆናጠጫው፤ ሁለተኛው የዘመናዊ ሥልጣኔ መዲናው እንዲሁም ሦስተኛው የመጨረሻ ምሽጉ ሆኑ። እዚህ ምሽጉም ነው የቀድሞም ሆነ ያሁኑ ዘመን ሠዓሊያን ያለመታከት እንደሚያሳዩን ሕይወቱን በሽጉጥ ያሳለፈው። በዚህ ድርጊቱም በእንግሊዞች የጦር ድግስ ላይ የምፀት ሣቁን ሥቆ አለፈ። እጁን ይዞ ለመመለስ የተላከው 32000 የእንግሊዝ ጦርም ባዶ እጁን እንዲመለስ ተገደደ።



2.2 የአፄ ቴዎድሮስ ምርኮኞች

ያን ያህል ጦር ወደ ሩቅ ኢትዮጵያ ለመላክ እንግሊዞች የወሰኑት በቀላሉ አልነበረም። ወጪ ያለበት ነገር በእንግሊዝ ፖርላማ በቀላሉ ተወስኖ አያውቅም። ግን በመጨረሻ አውሮጳውያን እስረኞችን ነፃ ማውጣትና እንዲያ የተዳፈረውን ንጉሥም መቅጣት አስፈላጊ ነው ተብሎ ስለታመነበት ጦሩ ተላከ። አውሮጳውያን የራሳቸው ጉዳይ ሲሆን የሚጽፉበት ስለማያልቅባቸው የዚያ የጦር ጉዞልም በታሪክ ከነበረው ጠቃሚነት እጅግ ተጋኖ ተተርኳል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የቴዎድሮስ ነገር ያከተመው ገና ጦሩ ወደ መሀል አገር መንቀሳቀስ ሳይጀምር ነው። ገና አንድ ጥይት ሳይተኮስ እንግሊዞች ጦርነቱን አሸንፈው



2.2 የአፄ ቴዎድሮስ ምርኮኞች

ነበር ማለት ይቻላል። ከላይ እንደጠቀስነው ቴዎድሮስ ሠራዊቱ ሁሉ እየከዳው ከጥቂት ታማኞቹ ጋር ብቻውን ቀርቷል። ባንፃሩም ባላንጣ የሆኑት መሳፍንት የእንግሊዞችን የዘመቻ ጉዞ ለማቃናት የተቻላቸውን ሁሉ ለማድረግ ወስነዋል። በዚህ ረገድ እንግሊዞች ከፍተኛ እርዳታ ያገኙት በትግሬ የበላይነትን እያገኘ ከመጣው ከካሣ ምርጫ (የኋላው አፄ ዮሐንስ) ነው። ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ባልተለመደ ሁኔታ ሁሉንም ገንዘብ እየከፈሉ ያገኙም ቢሆን፣ የእንግሊዝ ጦር ስንቅና የጭነት ከብት በማግኘት በኩል ከቶ ችግር አልነበረበትም።

ካሣ እንግሊዞችን ለመርዳት ለምን ወሰነ? በዚህስ ተግባሩ ኢትዮጵያን ከዳ ማለት አይደለም ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል፤ ተነሥቷልም። ድርጊቱን ለማጽደቅ ወይም ለመኰነን ሳይሆን አንዳንድ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። አንደኛ በዚያን ወቅት ቴዎድሮስ ድፍን ሀገር የጠላው መሪ ሆኖ ስለነበር እሱን ከሥልጣን ለማውረድ ማንኛቸውም መንገድ ትክክል መስሎ ይታይ ነበር። ሁለተኛ ካሣ የራሱን የሥልጣን ኮርቻ ለማደላደልና የኋላ ኋላም ዙፋኑን ለመያዝ እንግሊዝን የመሰለ ኃያል መንግሥት እርዳታና በጎ ፈቃድ ማግኘቱ ጠቃሚ መስሎ ታይቶት ነበር። ሦስተኛ እንግሊዞች የመጣንበትን የተወሰነ ዓላማ ከፈጸምን (ማለትም እስረኞችን ነፃ ካወጣንና ቴዎድሮስን ከማረክን) ሀገሩን ለቀን እንሄዳለን ብለው የገቡት ቃል ለካሣ አስተማማኝ ሆኖ ስለታየው ይሆናል። ያም ሆነ ይህ እንዲህ ያለ የውስጥ እርዳታ ማግኘቱ ለእንግሊዝ ጦር ዓላማ ሥምረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። ስለሆነም ጭነታቸውን ካራገፉበት ከዙላ ወደብ አንሥተው እስከ መቅደላ ድረስ እንግሊዞች ያላንዳች ሳንክና ጦርነት መድረስ ችለዋል። እነሱ ያን ያህል ሲጓዙ ካጋጠማቸው እክል የበለጠ ንጉሡ ከቅርቡ ከደብረ ታቦር ወደ መቅደላ ሲሄድ አጋጥሞታል፤ የበለጠ ጊዜም ፈጅቶበታል።

ደኅና አጋጣሚ ሆነና እንግሊዞች ተልዕኳቸውን እንደፈጸሙ ቃላቸውን ጠብቀው ወደ አገራቸው ተመለሱ። ይህም የነሱ ሳይውሉ ሳያድሩ መመለስ ለኢትዮጵያ ታሪክ ተማሪዎች ዕንቆቅልሽ ሆኖ ቆይቷል። ብዙ ጊዜ የሚነሣው ጥያቄ እንግሊዞች ኢትዮጵያ እምብርት ድረስ ያን ያህል ጦር ይዘው ገብተው እንዴት አገሪቱን ቅኝ የማድረግ ሐሳብ አልመጣባቸውም ነው። ዕንቆቅልሹን መፍታት የሚቻለው እንግሊዞች ይህን ጦር የላኩት አውሮጳውያን አፍሪቃን መቀራመት ከመጀመራቸው ከ20 ዓመታት ያህል በፊት መሆኑን ስንገነዘብ ነው። ቅድመ ቅኝ አገዛዝ ባሕሪ ያለው የናፒየር ዘመቻ በተከናወነበት ጊዜ እንግሊዝ በአካባቢው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ቁጥጥር በማድረግ ማስጠበቅ አለብኝ የምትለው ዘላቂ የሆነ የኤኮኖሚ ጥቅም ገና አልነበራትም። ይህንንም ሁኔታ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሎርድ እስታንሊ (ኋላ ኧርል ኦፍ ደርቢ የተሰኘው) በማያሻማ ሁኔታ እንዲህ ሲል አብራርቶታል፤

> የእንግሊዝ መንግሥት ዐፄ ቴዎድሮስ በመወገዱ ባገሪቱ ለሚደርሰው ነገር ደንታ የለውም። የወደፊት የኢትዮጵያ ዕጣ ምን እንደሚሆን፤ ምን



> ዓይነት ገዢ እንደሚተካ፤ ምን ዓይነት የርስ በርስ ጦርነት ወይ ሁከት እንደሚከተል፤ ይህ ሁሉ ጉዳያችን አይደለም። እርግጥ ነው ከሰብአዊ ርኅራኄ አንፃር፣ አገሪቱ በሥርዓት እንድትተዳደር ሕዝቡም ተደስቶና ረክቶ እንዲኖር እንመኛለን። ይሁን እንጂ ይህ ነው የሚባል የእንግሊዝን ጥቅም የሚመለከት ነገር በሌለበት አገር ማን ገዛ፣ እንዴት ገዛ ብለን ለመጨነቅ ግዴታ የለብንም።
> (Rubenson, *Survival*, 275 ስርዝ የተጨመረ)

ቴዎድሮስ እንደሆነ በሚያዝያ 3፣ 1860 «በአሮጌ» ጦርነት ማግስት ለባለድሉ ጀኔራል ናፒየር በጻፈው ደብዳቤ ለሕዝቡም ሆነ ለዓለም የመጨረሻ ቃሉን አሰምቶ አልፏል። ከዚህ ጦርነት በኋላ ነው እንግሊዞች የመቅደላን ምሽግ በመድፍ የደበደቡትና ንጉሡም ሕይወቱን ያሳለፈው። ይህ ደብዳቤ ፍጹም ቴዎድሮሳዊ የሆነ፣ የእድሜ ልክ ሕልሙንና ጥረቱን ያካተተ የታሪክ ሰነድ ነው። ለእንግለዛዊው ጀኔራል ይጻፍ እንጂ መልዕክቱ ለአገሬው ሕዝብ ነው። አልገዛ ላለው ሕዝቡ የሚቀርብ ወቀሳ ነው። ለደካሞች ያለውን ርኅራኄና ኢየሩሳሌምን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሣበት ዓላማ ሲከሽፍበት የተሰማውን ጸጸት ያጣመረ ሰነድ ነው። ባንድ ወገን አይበገሬነቱን እንደገና ሲያረጋግጥ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ያ እንዲያ የደከመበት የስነሥርዓት ጉዳይ እስከመጨረሻው አልሠምርለት በማለቱ የተሰማውን ቁጭት ይገልጻል። በተለይም ደግሞ የዕድሉ ሁሉ ቁልፍ አድርጎ የወሰደው መድፍ በመክሸፉ ያደረበትን ሐዘን ስሜትን በሚነካ ሁኔታ ይጠቅሰዋል። ባጭር አነጋገር ደብዳቤው የቴዎድሮስ ኑዛዜ ነው። ዓላማው ምን ምን እንደነበረ፣ ለምንስ እንዳልተሳካለት የሚገልጽ። አንባቢ በቅጡ እንዲገመግመው ከዚህ በታች በሙሉ ቃሉ ቀርቧል፤

> በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ በሶስትነት ባንድነቱ በክርስቶስ ያመነው ካሳ መቸም ያገሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁላችሁ ሽሽታችሁን አትተውም። ክርስቲያኑን ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ካረመኔ አገር አግብቸው ወንድ የሌላት ቆንጆ አለች ወንድ የነበራት ቆንጆ ነበረች ትላንትናም የሞተባት ትኖራለች ሽማግሌ ልጅ የሌለው ባልቴት ልጅ የሌላት እኔ የምጠውራቸው ብዙ በከተማየ አሉ። እግዚአብሔር ከሠጣችሁ ፍቀዱአቸው ያረመኔ አገር ነውና ያገሬ ሰው ገብር ሥራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በስራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ። እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አንድ እርሳስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ ብትቃጧቸው ከሮጡ ሰዎች ጋራ አልነበርሁም ጌታነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ሥታገል ውዬ ነው። ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል እስልምአል እያለ አስሩን

> ምክንያት ይሰጠኝ ነበረ:: እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይሥጠው እንደወደደ ይሁን እግዚአብሔር ቢሠጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረብኝ:: እግዚአብሔር ቢነሣኝ ልሞት እሣኄ ይህ ነበረ:: ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ ሰዎች ሢሸሹ ተነስቼ ማራጋት ልማድ ነበረኝ ጨለማ ከለከለኝ:: ትላንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ:: እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን እስለቅቃለሁ መስሉኝ ነበር:: ወንድ ያቀፈ ወንድ ተመልሶ አይታቀፍም::
> (Rubenson, *Acta II*, 354)

## አዲስ ያንድነት ስልት

ቴዎድሮስ ሲሞት የሥልጣን ጥያቄ እንደገና ተቀሰቀሰ:: ሦስት ተቀናቃኞች ብቅ አሉ:: በላስታ ዋግ ሹም ጉብዜ የቴዎድሮስ ዋነኛ ባላንጣ ሆኖ ከቆየ በኋላ ዙፋን ለኔ ይገባኛል አለ:: በመቅደላ ጦርነት ዋዜማ በአካባቢው ተፎካካሪው የነበረውን ወልቃይቴውን ጥሶ ጉብዜን ድል በማድረጉም የፖለቲካ የበላይነቱን ለማጠናከር ችሏል:: ይሁንና ከወራሪው የእንግሊዝ ጦር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ባለመመሥረቱ የወደፊቱ ባላንጣው ካሣ ምርጫ የታደለውን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ሳያገኝ ቀርቷል:: ካሣ በበኩሉ ከሥልጣን መቆናጠጫው ከተምቤን ተነሥቶ አብዛኛውን ከመረብ ወዲህ ያለውን የትግራይ ግዛት ከተቆጣጠረ በኋላ ሥልጣኑን ወደ መረብ ምላሽ ማስፋት ጀምሯል:: በስተደቡብ ደግሞ ምኒልክ ከመቅደላ እስር ቤት በ1857 ካመለጠ በኋላ ባባቱ ግዛት ሸዋ ላይ የበላይነቱን አረጋግጦ ፊቱን ወደ ሰሜን (ወደ ወሎ) አቅንቷል::

የነዚህ ያሁኖቹ ፉክክር ግን ከዘመነ መሳፍንት ሽኩቻ ባይነት የተለየ ነበር:: ቴዎድሮስ አንድ የማይሻር ለውጥ አምጥቶ ነው ያለፈው:: የድኅረ ቴዎድሮስ መሳፍንት እንደ ቀድሞዎቹ እንደ ልባቸው የሚያዙትና የሚቆጣጠሩት ንጉሥ አንግሠው እነሱ ከኋላ ሆነው መግዛት የሚሹ አልነበሩም:: እራሳቸው ዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ እንጂ:: በ1847 ካሣ ኃይሉ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብሎ ሲነግሥ በፖለቲካ ኃይልና በፖለቲካ ሥልጣን መካከል ያለው ልዩነት አክትሟል:: ዙፋን ዘሩን ከሰሎሞን ለሚያጣቅስ ብቻ ሳይሆን ለጡንቻኛውም በይፋ ክፍት ሆነች:: ስለሆነም ቴዎድሮስ እንደሞተ ዋግ ሹም ጎበዜ እራሱን አፄ ተክለ ጊዮርጊስ አሰኝቶ ነገሠ:: ምኒልክም እራሱን «ንጉሠ ነገሥት» ብሎ ለመጥራት ተሽቀዳድሞ ነበር:: ይሁንና ኋላ ከአዲሱ ንጉሥ ጋር ስምምነት ላይ ደርሶና የተክለ ጊዮርጊስን ዐፄነት ዐውቆ ከበሽሎ ወንዝ በስተደቡብ ያለው ግዛት ተመርቆለታል:: በጎጃም መግነን የጀመረው ራስ አዳል ተስማም ለአዲሱ ንጉሥ ገብቶ በዚያውም የንጉሡን እኅት በማግባት በጋብቻ ተሳሰረ:: ካሣ ምርጫም እህቱ ወ/ሮ ድንቅነሽ የዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ





2.3 ደጃች ካሣ ምርጫ (የኋላው. አፄ ዮሐንስ)

ሚስት በመሆኗ በጋብቻ ተሳስሮ ነበር:: ይህ ግን ከአመፅ እንዲታቀብ አላደረገውም:: አልገዛም ብሎ በመጽናቱም በሐምሌ 5፣ 1863 አድዋ አጠገብ አሰም ላይ ጦርነት ገጠሙ:: የካሣና የእንግሊዞች ወዳጅነትም ሥራውን ሠራ:: የንጉሡ ስድሳ ሺ ጦር በአምስት እጅ በሚያንሰው በካሣ አሥራ ሁለት ሺ ጦር ድል ተመታ:: የድሉ ቁልፍ ካሣ ከእንግሊዞች ያገኘው ዘመናዊ መሣሪያና እንግሊዛዊው የጦር አማካሪ ኪርክሃም ለካሣ ወታደሮች ያሳየው ዘመናዊ የውጊያ ስልት ነበር:: በንጉሡ ወገን 500 ሲሞቱ 1000 ቆስለው ንጉሡን ጨምሮ 24 ሺ ሰው ተማረከ:: የተክለ ጊዮርጊስ አጭርና ብዙም ፋይዳ ያልታየበት ዘመንም በዚሁ ተካተተ::

ከስድስት ወር በኋላ በጥር 13፣ 1864 ካሣ ምርጫ ዮሐንስ አራተኛ ተብሎ በትረ መንግሥት ጨበጠ:: ምንም እንኳ ዮሐንስ በቴዎድሮስ የተጀመረውን ጠንካራ ንጉሣዊ አገዛዝ እንደገና የመመሥረት ፍላጎት የወረሰ ቢሆንም የተከተለው መንገድ በእያሌው የተለየ ነበር:: ገና ከመጀመሪያው ለሥልጣን ፉክክር ራሱን



2.3 ደጃች ካሣ ምርጫ (የኋላው. አፄ ዮሐንስ)

ባጨበት ወቅት «ርእሰ መኳንንት» በሚለው ማዕረግ ሲጠራ የወደፊት እቅጣጫውን የተለመ ይመስላል። እራሱን በላቲን እንደሚባለው «የእቻዎች እውራ» እንጂ ፈላጭ ቆራጭ እርጎ ያየ አይመስልም። በቀጥተኛ አገባቡ ንጉሠ ነገሥት (የንጉሦች ንጉሥ) ለመሆን ነበር የሚሻው ማለት ይቻላል። ባንድ ወቅት ቴዎድሮስ ስለራሱ ሲናገር «የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም እጮኛ» ብሎ ፎክሮ ነበር። በርግጥም ኢትዮጵያን እንደ ቀናኢ ባል ነበር የሚወዳት። ዮሐንስ ግን ባገሩ የበላይነቱ እስከታወቀለት ድረስ ኢትዮጵያን ከእቻ መሳፍንቱ ጋር ለመጋራት ዝግጁ ነበር። ቴዎድሮስ ግዛታዊ ስሜትን ፊት ለፊት ሲጋፈጥ፣ ዮሐንስ ግን በዘዴ ለመያዝ፣ ካስፈለገም ለመፍቀድ ዝግጁ ነበር። ይህ የዮሐንስ ስልት ባንድ በኩል ነባራዊ ሁኔታ ከመገንዘብና እቅምን ከማወቅ የመነጨ በመሆኑ ብልኅነት የተመላበት ነበር። በሌላ ወገን ግን የአካባቢ ስሜትን የሚያደፋፍር በመሆኑ የማታ ማታ ለንጉሡ ለራሱ ጦስ እንደሆነበት እንገነዘባለን።

ዮሐንስ ባንድ ወገን የተገራ ክልላዊነትን ሲፈቅድ በሌላ ወገን ደግሞ በሁለቱ ዋነኛ ገባሪዎቹ፣ በሸዋው ምኒልክና በጎጃሙ እዳል፣ መካከል የተስተካከለ የኃይል ሚዛን ለመጠበቅ እጅግ ይጥር ነበር። ይህንም የሚያደርገው የሱ የበላይነት በነሱ እኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በውል ስለተገነዘበ ነው። ይሁን እንጂ ለዐፄያዊ ሥልጣን ዋና ተቀናቃኝ ለመሆን እቅምና ዝንባሌም የነበረው ምኒልክ በመሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ጎጃሙ ገዥ እንዲያዘነብል ይገደድ ነበር።

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ግን የዮሐንስና የእዳል ግንኙነት ይኸን ያህልም የሠመረ እልነበረም። እዳል የቀድሞው ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ታማኝ ጭፍራ ነበር። ስለዚህም ካሣ ሥልጣን እንደያዘ እዳልን ለማስገበር ከተተ። እዳልም ወደፊት ደጋግሞ እንደሚያሳየው ፊት ለፊት መጋጠምን ትቶ በደፈጣ ወጊያ ንጉሡን እታከተ። ስለዚህ ዮሐንስ እዳልን መሠረት ለማሳጣት ብሎ ከእዳል ጋር ተፎካካሪ የትውልድ ሐረግ ያለውን ደስታ ተድላን (ቴዎድሮስን የጐን ውጋት ሆኖ ሲያውከው የኖረው የተድላ ጓሉን ልጅ) ራስ እስኙቶ በጎጃም ላይ ሾመው። ሆኖም በሐምሌ 1866 እዳል ደስታን ድል ሲመታ ዮሐንስ እንደገና በእዳል ላይ ለመዝመት ካንገራገረ በኋላ ሐቁን ተቀብሎ የእዳልን የበላይነት እጸደቀ። እዳልም እምባጫራ ላይ በሥርዓት ታማኝነቱን ገልጾ ለንጉሡ እደረ።

የዮሐንስና የእዳል ወዳጅነት የጀመረው ከዚያ በኋላ ነው። ዮሐንስ በሚያሳስብ ሁኔታ እያደገ የመጣውን ምኒልክን ለመቋቋም ያለው ትልቅ እጋር እዳል መሆኑን ስለተረዳ ከዐባይ በስተደቡብ ወደሚገኙት ወደ እሮሞ ግዛቶች ለሚያደርገው መስፋፋት ቡራኬውን ሰጠው። እዳልም በፊናው ዮሐንስ ከግብፆች ጋር በጉንደትና በጉራ በሚፋለምበት ወቅት በበጌምድርና በስሜን የተነሣውን እመፅ በማክሸፍ ወሮታውን መለሰ። ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ በ1870 ንጉሠ ነገሥቱን እጅበ ልቼ ላይ ባላጋራው ምኒልክ ታማኝነቱን ሲገልጽ ለማየት በቃ። እዳል በዮሐንስ ዘንድ ከፍተኛውን ሞገስ ያገኘው በ1873 ተክለ ሃይማኖት ተሰኝቶ



«ንጉሠ ጎጃም ወከፋ» ሲባል ነው። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማስተዋል ያስፈልጋል። አንደኛ በዚያን ወቅት ከፋ ሲባል በውሱን አገባቡ የከፋን መንግሥት ብቻ ሳይሆን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ግዛቶች በጠቅላላው ማለት መሆኑን ነው። ሁለተኛ ዮሐንስ ተክለ ሃይማኖትን የከፋ ንጉሥ ብሎ በመሾም ምኒልክ ከዚያ አካባቢ እንዲታቀብ ግልጽ መልእክት ማስተላለፋን ነው። የዮሐንስ ሥጋት ምኒልክ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን መቆጣጠር ከቻለ ከዚያ በሚያገኘው ሀብት ዳብሮና ደርጅቶ የማይጋፋት ባላጋራ ይሆናል የሚል ነበር። የፈራውም አልቀረ ካንድ ዓመት በኋላ እምባቦ ላይ የምኒልክ ጦር የተክለ



2.4 የጐጃሙ ገዥ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት

ሃይማኖትን ጦር ድል ሲያደርግ የዮሐንስ ስሌት ከሸፈ። ተጨንቆና ተጠቦ የቀየሰው የሁለቱን መሣፍንት የኃይል ሚዛን የመጠበቅ ፖሊሲ በዚያው ተንኮታኩቶ ቀረ። ይባስ ብሎ፣ በ1880 ሁለቱ የቀድሞ ባላጋራዎች ይቅር ለግዜር ተባብለው በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የአመፅ ግንባር ፈጠሩ። በዚያም በአንድ ወገን በጣሊያኖች በሌላ ወገን በማህዲስቶች ተወጥሮ የነበረው ንጉሠ ነገሥት የመከራው ጽዋ ሞላ። በንዴትም ራሱ እንኳ ሊረዳው ያልቻለውን የቅጣት ማዕበል በጎጃም ላይ እዘነበ። ለራስ ዳርጌ በጻፈው ደብዳቤ እንደገለጸው «በእኔም



2.4 የጐጃሙ ገዥ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት

በድኃውም ኃጢአት እንደሆነ አይታወቅም አገሩን ሳጠፋ ከረምሁ»፡፡ (ጎሩይ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ 179)

ምኒልክ የዮሐንስ ተቀናቃኝ መሆን የጀመረው ገና ከመቅደላ አምልጦ ሸዋ እንደገባና ሥልጣኑን ማደላደል እንደጀመረ ነው፡፡ እድሉ ሆኖ ጠንካራና አንፃራዊ ብልፅግና የታደለ ግዛት ነው የወረሰው፡፡ ይህን የተደላደለ መሠረት ተቆናጦ ወደ ሰሜን መስፋፋት ጀመረ፡፡ ዐፄያዊ ዙፋን ለመጨበጥ ትክክለኛ ጉዳና ሆኖ የታየው ይኸው ነበር፡፡ የዚህ የመስፋፋት ፖሊሲ አንዱ ገጽታም እንደ ወረ ኢሉ ያሉ አዳዲስ ከተሞችን መመሥረት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የምኒልክ መስፋፋት ተቃውሞ ማስነሣቱ አልቀረም፡፡ ዝቅ ሲል ከወሎዋ መሪ ወይዘሮ መስተዋት እና ቀጥሎም ከልጇና ወራሿ አመዴ ሊበን (በፈረስ ስሙ አባ ዋጠው ተብሎ የሚታወቀው)፣ ከፍ ሲል ደግሞ ከዐፄ ዮሐንስ ከራሱ፡፡ በዚህ ሁኔታ ወሎ የዐፄውና የሸዋው ተቀናቃኝ መቀራመቻ ዐውድማ ሆነች፡፡ ነገር ግን ሁለቱ ኃያላን ፊት ለፊት ከመጋጨት ይልቅ በወኪሎቻቸው አማካይነት መፋለምን መረጡ፡፡ ስለሆነም ዮሐንስ አባ ዋጠውን ሲያስልፍ ሌላው የወሎ ባላባት ሙሐመድ ዓሊ ደግሞ በምኒልክ ጎራ ገባ፡፡ በመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዓመታት በሰሜን ጠረፍ ከግብፆች ጋር ተፋጦ ለነበረው ዮሐንስ ከዚህ የተሻለ አማራጭም አልነበረው፡፡ ይህ ሁኔታ ለምኒልክ አመቺ ሆኖ ተገኘ፡፡ በ1868 ላይ ቁልፍ የሆነውን የመቅደላን ምሽግ ለመያዝ በቃ፡፡ አባ ዋጠውን አስሮም ሙሐመድ ዓሊን የወሎ ጠቅላይ ገዥ አደረገው፡፡

ዮሐንስ በጉንደትና በጉራ ጦርነት በግብፆች ላይ ድል ሲቀዳጅ ነገር ሁሉ ተለወጠ፡፡ የውጭውን አደጋ ካከሸፈ በኋላ በታላቅ ግርማ ሞገስ ፊቱን ወደ ደቡብ አዞረ፡፡ ሙሐመድ ዓሊ በተካነበት አስደናቂ የፖለቲካ ቅልጥፍና ምኒልክን ከዶ ለኃያሉ ንጉሠ ነገሥት አደረ፡፡ ዮሐንስም ወሎን በጁ አድርጎ ወደ ደቡብ መገስገሱን ቀጠለ፡፡ ዓላማው ለምኒልክ እምቢተኝነት የማያዳግም መፍትሔ ለመስጠት ነበር፡፡ በጥር 1870 መንዝ ገባ፡፡ ምኒልክም የከተት ዓዋጅ ዐወጀ፡፡ ከጥቂት ግጭቶች በኋላ ልቼ ላይ የምኒልክ አማካሪዎች አሜን ብሎ እንዲገባ መከሩት፡፡ ዮሐንስም ቢሆን ዘመቻው እየተራዘመ፣ ስንቅ እየተቸገረ ሲሄድ ነገሩን በእርቅ መጨረሱን አልጠላም፡፡

በመጋቢት 12 1870 የተፈጸመውና የልቼ ስምምነት ተብሎ የታወቀው ውል በኢትዮጵያ መንግሥት ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ የያዘ ድርጊት ነው፡፡ ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ የነበረውን ያልተረጋጋ የሥልጣን ሁኔታ አንድ ዓይነት ማሰሪያ አበጀለት፡፡ ምኒልክ የዮሐንስን የበላይነት በማያሻማ ሁኔታ አወቀ፡፡ ድንጋይ ተሸክሞና በአዝማሪዎች ተረብ ታጅቦ ከዮሐንስ ፊት ማረኝ ብሎ ወደቀ፡፡ በውሉ መሠረት ምኒልክ በየዓመቱ ግብር ሊገብር፣ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር በሸዋ ምድር እስካለ ድረስ ስንቅ ሊያቀብል፣ ከውጭ ጠላት ጋር በሚያደርገው ጦርነትም ሊረዳ ተስማማ፡፡ የልቼ ስምምነት የዮሐንስን የበላይነት በግልፅ ያረጋገጠውን ያህል ከበታቾቹ ጋር ሊኖረው የፈለገውን በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነትንም የሚያመለክት ነበር፡፡ ምኒልክን አንበረከከው እንጂ



አላዋረደውም፡፡ ንጉሠ ነገሥት ነኝ ማለቱን እንዲተው ቢያደርገውም ከአባቶቹ የወረሰውን የሸዋን ንጉሥነት በሚከተሉት ቃላት አጸደቀለት፤

> አባቶችህ ባቀኑት አገር ንጉሥና ጌታ ነህ፡፡ ስምምነታችንን እስካከበርክም ድረስ ሥልጣንህን አከብራለሁ፡፡ መንግሥትህን ያጠቃ እኔን እንዳጠቃ ጦርነት ያወጀብህ በኔ እንዳወጀ እቆጥረዋለሁ፡፡ የበኩር ልጄ ነህ፡፡ (Marcus, *Life and Times*, 56)

ምኒልክም ቢሆን አሜን ብሎ በመግባቱ ብልኀነቱን ነው ያሳየው፡፡ ክብሩ ቢነካም ወታደራዊ ኃይሉ ቅንጣት አልጐደለም፡፡ በግብፅ ምርኮ መሣሪያ ደርጅቶ የመጣውን የንጉሠ ነገሥቱን ጦር መዋጋት ሞኝነት ነበር፡፡ ከልቼ ምኒልክ የተማረው አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር የትዕግሥትን አስፈላጊነት ነው፡፡ ንጉሠ ነገሥትነትን ለመቀዳጀት በትዕግሥትና በትጋት መሥራት ጀመረ፡፡ የልቼ ሌላው ውጤት ወሎን ከምኒልክ ቁጥጥር ፈልቅቆ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ማድረጉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህም ባልታሰበ መንገድ ለምኒልክ የወደፊት እድል በጐ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ምኒልክ የሰሜኑ በር ሲዘጋበት ፊቱን ወደ ደቡብ ለማዞር ተገደደ፡፡ በዚያም በዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ዐቢይ ሥፍራ የያዙትን የደቡብ ኢትዮጵያ ዘመቻዎቹን ከፈተ፡፡ በነሱም አማካይነት በልፅጎና የበለጠ ደርጅቶ ለዙፋን ወራሽነት ራሱን ብቸኛ እጩ ለማድረግ በቃ፡፡ ስለሆነም ዮሐንስ መተማ ላይ ሲሞት በእግሩ የሚተካው ምኒልክ መሆኑ ከቶ አጠያያቂ አልነበረም፡፡

ዮሐንስ ሸዋና ጎጃም በራሳቸው ነገሥታት እንዲተዳደሩ ቢፈቅድም መረብ ምላሽ ተብሎ ይታወቅ በነበረው ግዛት (የዛሬይቱ ኤርትራ) ግን ተመሳሳይ ፖሊሲ ለመከተል ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አካባቢው ለውጭ ጣልቃ ገብነት የተጋለጠ በመሆኑ ነው፡፡ የሐማሴኑ መስፍን ደጃች ወልደ ሚካኤል በጉራ ጦርነት ጊዜ ከግብፆች ጋር ማበሩ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ሆኖለት ነበር፡፡ ስለዚህም መረብ ምላሽን እንዲያስተዳድር ታማኝ ጭፍራው የሆነውን የተምቤኑን ተወላጅ ሻለቃ አሉላ እንግዳን (የኋላውን ራስ አሉላ) ሾመው፡፡ ከመሳፍንት የማይወለደው አሉላም እስከመጨረሻው ንጉሠ ነገሥቱን በታማኝነት አገለገለ፡፡ የጠረፍ ግዛት ሹምነቱንም ሥራ በተለየ ስሜትና ትጋት ማከናወን ቀጠለ፡፡ ይሁንና በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ልዩ መወደድን አግኝቶ ለከፍተኛ ሥልጣን በመታጨቱ በትግራይ መኳንንት ዘንድ ጉምጉምታ ይሰማ ጀመር፡፡ ከነሱም አንዱ የዮሐንስ አጎት ልጅ የሆነው ደጃች ደበብ አርአያ በምዕዋ አካባቢ በመሸፈት በመጨረሻ በ1880 ገብሮ እስከገባ ድረስ አሉላን ሲያውክ ቆየ፡፡ ወልደ ሚካኤልም ከማንም የበለጠ ይገባኛል የሚለውን ግዛቱን መነጠቁን በፀጋ አልተቀበለም፡፡ ቦጎስ ላይ መሽጎ አጋሮቹን ግብፆችን ተገን አድርጎ በየጊዜው ወደ ሐማሴን ግዛት ወረራ ያካሂድ ጀመር፡፡ በመጨረሻ በ1871 ግብፆችም ችላ እያሉት ሲሄዱ እርቅ ጠይቆ ገባ፡፡



2.5 የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ እንግዳ

የዮሐንስ ያንድነት ስልት ሃይማኖታዊ ገጽታም ነበረው። ይሁን እንጂ ዮሐንስ በፖለቲካም መስክ ያሳየውን ሆደ ሰፊነት በሃይማኖት ረገድ ሊያሳይ አልቻለም። የልቼ ስምምነት ከተደረገ በኋላ ዮሐንስ ሐሳቡን ቤተ ክህነትን ሲያራኩት ወደ ነበረው ወደ እምነት ክፍፍል አዞረ። ቦሩ ሜዳ ላይ ትልቅ የሃይማኖት ጉባኤ ተደርጎ የዘመነ መሳፍንት ርእዮታዊ መሠረት የነበረው የእምነት ልዩነት ማሳረጊያውን አገኘ። ንጉሠ ነገሥቱ ይደግፈው የነበረው የተዋሕዶ እምነት ብቸኛው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት እንዲሆንና የሌሎች እምነቶች ተከታዮቹም በተደረገው ክርክር እንደተረቱ ተቆጥረው ተዋሕዶን እንዲቀበሉ ተደነገገ። በድሮ እምነታችን እንጸናለን ያሉት መከራና ስደት ጠበቃቸው፤ አንዱ ምላሱን እስከመቆረጥ ደረሰ። ይህና የመሳሰሉት ድርጊቶች በዮሐንስ ስም ላይ ጥቁር ነጥብ ጥለው አልፈዋል። ቢሆንም የቤተ ክህነትን አንድነት ማረጋገጡ በግብፆች ላይ ባገኘው ድል ላይ ታክሎ ዮሐንስን



በቤተ ክህነትና በክርስቲያን ምእመናን ዘንድ ልዩ ሞገስ አሰጠው። ከዚያም በላይ ለዘመናት ባንድ ጳጳስ ተወስና ለቆየችው ቤተ ክህነት ከግብፅ አራት ጳጳሳት ማስመጣት ሲችል ደግሞ ዮሐንስ ይበልጥ ክብሬታ አገኘ።

በፀጋና በሦስት ልደት ተከታዮች ላይ የደረሰው በደል ግን በእስልምና ተከታዮች ላይ ከደረሰው መዓት ጋር ሲነፃፀር ከቁጥር የሚገባ አልነበረም። የዮሐንስ ዓላማ የእምነትን ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትንም አንድነት መመሥረት ነበር። እስልምና የሚባል ነገር በዮሐንስ ርእዮተ ዓለም ውስጥ ከቶም ሥፍራ አልነበረውም። ስለሆነም በሙስሊሞች ላይ፣ በተለይም በፈረደባቸው የወሎ ሙስሊሞች ላይ፣ የጥፋት ሠይፉን መዘዘ። ሃይማኖታችሁን ለውጡና ክርስትና ተቀበሉ፤ አለዚያ መሬትና ንብረታችሁን አስረክቡ ተባሉ። የፖለቲካ መሪዎቹ መስሎ ለማደር ሲሉ እሺ አሉ። ሙሐመድ ዓሊ ተጠምቆ ሚካኤል ሲባል፤ አባ ዋጠው ኃይለ ማርያም ተባለ። አንዳንዶቹ ለይስሙላ ተጠምቀናል ብለው ውስጥ ውስጡን ግን የእስልምና ሃይማኖታቸውን ቀጠሉ። ቀን ለእግዚአብሔር ማታ ለአላህ መጸለይ ያዙ። ሌሎቹ ወደ አርሲና ጉራጌ አገር ስደትን መረጡ። በርከት ያሉ ግን እንደ ሼክ ጣልሃ በመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎቻቸው አማካይነት አመፁ። ዮሐንስ በወሎ ላይ የሾመው ልጁ አርአያ ሥላሴ ያሳየው ጭካኔ አመፁን ይበልጥ አቀጣጠለው። በመጨረሻ ዮሐንስና ምኒልክ በጣምራ ባካሄዱት የጭፍጨፋ ዘመቻ አማካይነት አመፁ ሊገታ ቻለ። በጊዜ ሠልፉን ያሳመረው ሚካኤልም ራስ ተብሎ የወሎ ገዥነቱንና የኢትዮጵያ አውራ መስፍንነቱን ለማግኘት በቃ።

## የውጭው አደጋ መባባስ

ከመቅደላ በኋላ እንግሊዞች የኢትዮጵያን ፊት እያሳየን ያሉ ይመስላል። ባገራቱ የፈለገው ነገር ቢፈጠር ደንታ የለንም ያሉትን ቃል ለማክበር ቆርጠዋል። የቀድሞ አጋራቸው ካሣ ምርጫ ለመቀራረብ የሚያደርገው ጥረት ስሜትም አልሰጣቸው። ወታደራዊ አማካሪዎች እንዲልኩለት ያቀረበውን ጥያቄ ጆሮ ዳባ ልበስ አሉት። መሣሪያዎችንም ከእንግሊዝ ለመግዛት የቻለው ሄንሪ ኤስ ኪንግ በተባለ የግል ኩባንያ አማካይነት እንጂ የእንግሊዝ መንግሥት እንደሆነ እጁን አላስገባም ብሏል። ኢትዮጵያውያንን የእጅ ጥበብ የሚያስተምሩ ባለሙያዎች ለመመልመል የተላከ ቡድንም በለንደን ትእዛዝ እስክንድርያ ላይ ታግቶ ቀረ። ካሣ፣ እኔ ተክለ ጊዮርጊስን አስም ላይ አሽንፎ ዙፋኑን ሲይዝ ወዳጆቼ ናቸው ብሎ የምሥራች ቢልክላቸውም ከቁም ነገር አልቆጠሩትም። ለደብዳቤውና አብሮ ለላከላቸው ገጸ በረከት መልስ የሰጡት ከሁለት ዓመት በኋላ ነው። በኤደን ላለው ቆንስላቸው በጻፉት የመሸኛ ደብዳቤም እንዲህ ዓይነት የደብዳቤም ሆነ የገጸ በረከት ልውውጥ ዳግመኛ ለማድረግ ፍላጎት ፈጽሞ እንደሌላቸው ለካሣ ግልፅ እንዲያደርግለት ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥተውት ነበር።



2.5 የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ እንግዳ

ይሁን እንጂ፣ እንግሊዞች የመቅደላን ዘመቻ ከቶ ለመርሳት የሚፈልጉ ቢመስሉም፣ ያ ዘመቻ አሻራውን ሳይተው አላለፈም። ከላይ እንደተመለከትነው የካሣ ወታደራዊ የበላይነት አንዱ ምንጭ ከዘመቻው የተረፈው ዘመናዊ መሣሪያ ነበር። እንግሊዞች የመቅደላን መንገድ ጨርቅ ሳረገላቸው ካሣ ስድስት መድፍ 850 ጠመንጃና በርካታ ጥይቶች ትተው ነበር የተመለሱት። በተጨማሪም ምንም እንኳ እንግሊዞች የካሣን የሚሊታሪ አማካሪዎች ጥያቄ አፊሴላዊ ፈቃድ ቢነፍጉትም አንዱ ባልደረባቸው፣ የጎምሣ አለቃ ኪርክሃም፣ በፈቃዱ ቀርቶ የካሣ ጀኔራል ለመሆን በቅቷል። ኪርክሃም ለካሣ ወታደሮች የፈነጠቀላቸው አንዳንድ ዘመናዊ የውጊያ ስልቶችና ካሣ ከእንግሊዞች የወረሳቸው ዘመናዊ መሣሪዎች ተጣምረው ነው አሰም ላይ ካሣን ለድል ያበቁት።

የናፒየር ዘመቻ ባገሪቱ የውጭ ግንኙነት ላይም የተወሰነ እንድምታ ነበረው። እንግሊዞች እንዲህ በቀላሉ ኢትዮጵያ እምብርት ከደረሱ እኛስ ምን ያቅተናል የሚል ክንቱ ሐሳብ በአንዳንድ የውጭ መንግሥታትና ኃይሎች ዘንድ መስረፅ ጀመረ። አይበገሬ የሚባለው ያበሻ ሕዝብ ለካ እንዲህ በቀላሉ የሚንበረከክ ነው የሚል ስሜት ተፈጠረ። ይህ የተሳሳተ ግምት መጀመሪያ የተጠናወተው ግብፅን ነው። ለዚህም ስሜት የመጀመሪያውን ጉልህ ምሳሌ የሰጠውም በኢትዮጵያ ምድር የግብፅ የመስፋፋት ፖሊሲ ቀያሽ ለመባል የበቃው የስዊሱ ተወላጅ ቨርነር ሙንዚንገር በየካቲት 1863 ገና በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል ሆኖ ነው። ካሣ የካቶሊኮችን እንቅስቃሴ ለማገድ የሚያደርገውን ጥረት አስመልክቶ በጻፈው ደብዳቤ ካሣ ጠባዩን ያላሳመረ እንደሆነ የቴዎድሮስ ጽዋ እንደሚጠብቀው አስጠንቅቆታል። ይህ ዛቻ የጉንደትና የጉራ መቅድም ነበር ማለት ይቻላል።

የሙንዚንገር ጌታ የግብፁ መሪ ኸዲቭ እስማኤል ራሱንም ሆነ ግብፅን እንደ አውሮጳዊ የሚያይ ሆኖም ግን የግብፅ እድገትና ብልፅግና በአፍሪቃ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ተገንዝቦ ጥረቱን በዚሁ አቅጣጫ የሚተልም መሪ ነበር። በዚህም ረገድ የዘመናዊት ግብፅ መሥራች ሙሐመድ ዓሊ ካደረገው ይበልጥ የዐባይን ፈለግ ተከትሎ ወደ አፍሪቃ ክርስ መስፋፋት ቀጠለ። እንደ እንግሊዛዊው ሳሙኤል ቤከር ያሉትን ተጓዦች እየቀጠረም የዛሬውን የደቡብ ሱዳን ግዛት ከክልሉ አስገባ። ይህን ሁሉ ሲያደርግ ለአውሮጳውያን መንግሥታት የሚያስተላልፈው መልእክት የሥልጣኔን ችቦ በጨለማይቱ አህጉር እያበራሁና የባርያን ንግድ እያጠፋሁ ነው የሚል ነበር። ከባርያ ንግድ የሚበቃቸውን ያህል ካተረፉ በኋላ፣ ባርነትን ማስወገድ እንደ ታላቅ ተልዕኮ ለያዙት አውሮጳውያን ይህ ዓይነት ሙዚቃ ጣፋጭ ጣዕመ ዜማ ነበረው። እስማኤል ወደ ኢትዮጵያ ምድር መስፋፋቱን ሲጀምርም ለአውሮጳውያን ይህንኑ የፀረ ባርነት ሙዚቃ ነው የተጫወተው።

ባጭሩ የእስማኤል ዓላማ ነጭ ዐባይንና ጥቁር ዐባይን ያቀፈ ሰፊ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ግዛት ለመፍጠር ነበር። ይህንንም ዓላማውን እውን ለማድረግ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ እርምጃዎችን ያቀናጀ ስልት ነደፈ።



በቅርቡ ዙፋኑን የጨበጠውን ዐፄ ዮሐንስን በጦር ከቦ በዲፕሎማሲ ለማራቆት ሥራዬ ብሎ ያዘ። ለዚህም የመጀመሪያው እርምጃ ቦጉስን (የዛሬው ከረንን) መያዝ ነበር። ለዚህም እርምጃ ሰበብ የሆነው የአካባቢው የኢትዮጵያ ሹም በግብፅ ግዛት ላይ ወረራዎች አካሂዷል የሚል ነበር። ዮሐንስም ይህን እርምጃ ባለመቀበል ለእስማኤል ተቃውሞውን፣ ለአውሮጳውያን ስሞታውን አሰማ። የጦር አማካሪው ኪርክሃም ተዘዋዋሪ አምባሳደር ሆኖ የዮሐንስን ደብዳቤዎች ይዞ ወደ እንግሊዝ፣ አውስትሪያ፣ ጀርመን፣ ሩሲያና ፈረንሳይ ተላከ። የደብዳቤዎቹ መሠረተ ሐሳብ አንድ ነበር። የክርስቲያን መንግሥት በእስላም ሲጠቃ የአውሮጳ ክርስቲያን መንግሥታት አጋርነታቸውን እንዲገልጹ የሚማጠን ነበር። ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ ዮሐንስ የተለየ ከበሬታ ስለነበረው ስለ ቦጎስ መያዝ ዘርዘር አርጎ ጽፎላት ነበር።

የዮሐንስ አቤቱታ አለት ላይ የፈሰሰ ውሃ ሆነ። የሩሲያ፣ የፈረንሣይና የጀርመን መንግሥታት አምባሳደር ኪርክሃምን በቅጡም ለማነገር ፈቃደኛ አልነበሩም። እንግሊዞች ከዚያም አልፈው ለእስማኤል በጎ ፈቃድ ዋቢ ለመቆም ተጋበዙ። ይህ ሁሉ ለዮሐንስ እንቆቅልሽ ሆኖበት ነበር። ክርስቲያን ለተጠቃ ክርስቲያን ይደርስለታል ነበር የሱ ግምት። ያልተገነዘበው ነገር ሃይማኖታዊ አንድነት በአውሮጳውያን ዘንድ ያረጀ፣ ያፈጀ መፈክር መሆኑን ነው። የነሱ መመዘኛ ሃይማኖት ሳይሆን ቁሳዊ ጥቅም ሆኗል። በነበረው ሁኔታም ሙስሊም የሆነችው ግብፅ ክርስቲያን ከሆነችው ኢትዮጵያ የበለጠ የንግድና የኢንቨስትሜንት ዕድል ስለምትሰጣቸው ምርጫቸው ግልፅ ነበር። በተለይም የስዊዝ ቦይ በ1861 ከተከፈተ በኋላ የግብፅ ኢኮኖሚያዊም ሆነ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ይበልጥ እየጎላ መጣ። ለዚህም ነው የግብፅን በምድረ ኢትዮጵያ መስፋፋት አበክረው ለመቃወም ዝግጁ ያልነበሩት። እስማኤል፣ ቦጎስ ጥንቱንም ቢሆን የግብፅ ግዛት ነው፤ ቦጎስን መያዝ ማለት የሰው አገር መንጠቅ ሳይሆን ያመፀን ክፍለ ሀገር ማስገበር ነው ሲልም እውነቱን ነው ብለው ተቀበሉት። ከዚያ በኋላ ግብፆች የልብ ልብ እያገኙ መጥተው ሰንሂት (የዛሬው ከረን ከተማ) ላይ አንድ ትልቅ ምሽግ ሠሩ። ያገሬውን ሕዝብ ለመሸንገልም የግብር ምሕረት አደረጉ።

ሌላው የግብፆች ዘመቻ ደግሞ በስተደቡብ በዮሐንስ ላይ አመፅ ማስነሣት ነበር። ለዚህም ዓላማቸው አልገብርም እያለ የሚያንገራግረው ምኒልክ ጥሩ መሣሪያ ይሆናል ብለው ገመቱ። ምኒልክም ራሱ ከግብፆች ጋር አንዳች ስምምነት ለማድረግ መልእክተኞችን መላክ ጀምሯል። ይሁን እንጂ ከግብፆች ጋር አብሮ ዮሐንስን ለመውጋት ወይም እነሱ በሰሜን ሲወጉት እሱ በደቡብ ሌላ የጦር ግንባር ለመክፈት ለማቀዱ ምንም የተጨበጠ ማስረጃ የለም። ያም ሆነ ይህ ግን በመጨረሻው ፍልሚያ ይበልጥ የሠመረላቸው ግን የሐማሴኑን ገዥ ደጃች ወልደ ሚካኤል ሰሎሞንን ማስኮብለሉ ነበር። ምንም እንኳ በጉንደት ጦርነት ከዮሐንስ ስር ተሰልፎ ቢወጋቸውም ከዚያ በኋላ ግን ንጉሡ ነገሥቱን ከድቶ ከግብፆች ጋር ለመሰለፍ በቃ።

ቦጎስ ለግብፆች የመስፋፋት ዓላማ መጀመሪያው እንጂ መጨረሻው አልነበረም፡፡ ለኢትዮጵያ የከፋው አደጋ የመጣውም ከቦጎስ ሳይሆን ግብፅ በ19ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከያዘችው የቀይ ባሕር ግዛት ነበር፡፡ የቀይ ባሕርና የሕንድ ውቅያኖስ ወደቦች ሞት አፋፍ ከሚገኘው ከኦቶማን መንግሥት የይስሙላ ይዞታ ባዲስ ጉልበት ወደሚስፋፋው የግብፅ መንግሥት ቁጥጥር መተላለፋቸው ለኢትዮጵያ የአደጋ ምልክት ነበር፡፡ ግብፆች እንደ ኦቶማኖች በአፍአዊ ቁጥጥር ረክተው የሚቀመጡ አልነበሩም፡፡ ባሕር ጠረፍ ተወስነው የመቅረት ሐሳብም አልነበራቸውም፡፡ በዚህም መሠረት ባባቱ ሱዳናዊ በናቱ ኢትዮጵያዊ እንደነበረ የሚነገርለት መሐመድ ራዑፍ ፖሻ የሚባል የጦር መሪ ከዘይላ (ሰሜን ሶማሊያ) ተነሥቶ በጥቅምት 2፣ 1868 ሐረር ከተማን ያዘ፡፡ በዚያኑ ወቅት ደግሞ በዝነኛው ሙንዚንገር የሚመራ ጦር ከታጁራ (ከጅቡቲ ከፍ ብሎ) ተነሥቶ ወደ ሸዋ አመራ፡፡ የዚህ ጦር እድል ግን ከራዑፍ ጦር በጣም የተለየ ነበር፡፡ አውሳ ሲደርስ አፋሮች ከበው አደጋ ሲጥሉበት ሙንዚንገር ከነሠራዊቱ የአሸዋ ሲሳይ ሆኖ ቀረ፡፡ እነዚህ በስተደቡብ የተደረጉ የግብፅ ወረራዎች የተቀናጀ ሰፊ የወረራ ዕቅድ አካሎች ነበሩ፡፡ የወረራው ዋና መሥመር ግን በሰሜን በኩል ከምፅዋ ዙላና አንፊላ ወደቦች ተነሥቶ ነበር፡፡ መጀመሪያ የጨው ምርት ያለበትን የጥልጣልን በረሃ ለመቆጣጠር የሰነዘሩት ዘመቻ ውሎ አድሮ እየፈረጠመ ወደ ተሟላ ያገር ወረራ ተሸጋገረ፡፡

## ጉንደትና ጉራ፤ ሰላም ያልተገኘበት ድል

በዚህን ዘመን በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል የተከናወኑትን ጦርነቶች ለሚመረምር ሰው ሕሊናን ደጋግሞ የሚኮረኩር አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም የወራሪው ዐይን አውጣነትና የተወራሪው ልዝብነት ነው፡፡ በመስከረም 1868 የግብፅ ጦር ወደ ደጋው መንቀሳቀስ ጀምሮ እያለ ዮሐንስ ጠቡን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረቱን እንደቀጠለ ነበር፡፡ የግብፅ ጦር እየገፋ ሲመጣ እሱ ግጭት እንዳይኖር ብሎ የሐማሴንና የሠራዬ ሠራዊት ወደ ዐድዋ እንዲያፈገፍግ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ ይህን ማድረጉም ዮሐንስ ሰላም ወዳድነቱን ለአውሮጳውያን በማያሻማ ሁኔታ ለማሳየት ስለፈለገ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የጠላትን ጦር ጎትቶ ወደ መሀል አገር በማስገባት የስንቅ አቅርቦት መስመሩን አርዝሞ ለማዳከምም ያቀደ ይመስላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ዮሐንስ የክተት ዐዋጅ ያወጀው በጥቅምት 14 የግብፅ ጦር ሐማሴን ከደረሰ በኋላ ነው፡፡

ክተቱ በታወጀ በሁለት ሳምንት 20000 የሚያህል ጦር ከንጉሠ ነገሥቱ ሥር ተሰለፈ፡፡ የሰሜን ኢትዮጵያ አውራጃዎች በሙሉ፣ የሐማሴኑን ደጃች ወልደ ሚካኤል ሰሎሞንን ጨምሮ፣ ከቶ ነበር፡፡ በግብፅ በኩል በዴንማርኩ አዛዥ በኮሎኔል አረንድሩፕ የሚመራ 2000 ሠራዊት ተሰልፎ ነበር፡፡ ሁለቱ ጦሮች ኅዳር 8 ማለዳ ጉንደት (ጉንዳጉዲ) ላይ ገጠሙ፡፡ በጣም አጭር ግን ውጤቱ የማያሻማ ጦርነት ሆነ፡፡ የግብፅ ጦር በኢትዮጵያ ጦር ስልታዊ እንቅስቃሴዎች ከተመቻቸበት ኮረብታ ወደ ሸለቆው ተታሎ ወርዶ ጭዳ ሆኖ ቀረ፡፡ የግብፅን ጦር



አሳዛኝ ዕጣ ኋላ ጉራ ላይ በአዝማችነት ሊሰለፍ የበቃው አሜሪካዊው ኮሎኔል ዳይ እንዲህ ሲል በማይረሱ ቃላት ዘግቦታል፤

> አንዳችም ዓይነት አቤቱታ፣ አንዳችም ዓይነት ኤሎሄ በደም የተነከረውን እጅ ሊገታው አልቻለም፡፡ በጦር ተቸክለው የተጋደሙ ወይ የሚንጠራሩ፣ እጃቸው የተቆረጠ ወይ አንገታቸው ከትከሻቸው ተቀንጥሶ ሊወድቅ የተቃረበ አካላት ድል አድራጊውን ጠላት ማረኝ ማረኝ ይላሉ፡፡ ግን ማን ሊሰማ፡፡ ጥፍጨፋውን የሚያቆም ምንም ኃይል አልነበረም፡፡ መጽሐፉ እንደሚለው ይህ (የግብፅ) ጦር ተፈርዶበት ነበር፡፡ ከጥይቱ ቢያመልጡ፣ ከጎራዴው አያመልጡም ነበር፡፡ ዱላውን ሲከላከሉ ጦሩ ይቀሥፋቸው ነበር፡፡ (Dye, 139)

ከእንዲህ ያለ መዓት በኋላ ለግብፅ የነበረው ምርጫ ወይ በቃኝ ወይ በቀል ነው፡፡ ኸዲቭ እስማኤል የኋለኛውን መረጠ፡፡ ዓመት ሳይሞላ ከፊተኛው እጅግ የላቀ ጦር (15000) በሙሐመድ ራቲብ ፖሻ የጦር አዝማችነት ላከ፡፡ በአሜሪካ የርስ በርስ ጦርነት የተሳተፉ የጦር መኰንኖችም ያ ጦርነት ካለቀ በኋላ ለእስማኤል አድረው ለግብፅ ጦር አዲስ የውጊያ ስልት ማቅሰም ጀምረዋል፡፡ የኤታማዦር ሹሙና የጦሩ ሁለተኛ አዛዥ አሜሪካዊው ጄኔራል ሎሪንግ ነበር፡፡ ከላይ እንዳየነው ደግሞ ኮሎኔል ዳይ የግብፅ ሽንፈት ዘጋቢነት ዕጣው ሆኗል፡፡ ግብፆች ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ ተዘጋጅተው ስለመጡ የጉንደት ጦርነት በጥቂት ሰዓታት የተጠናቀቀውን ያህል ጉራ ሦስት ቀን የፈጀ ነበር፤ ከመጋቢት 2 እስከ 4፣ 1861 ቆየ፡፡ ግብፆች መጀመሪያ መሽገው ነበር የሚዋጉት፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያውያን ላይ ብዙ ጥፋት ማድረስ ቻሉ፡፡ ነገር ይበላሽባቸው የጀመረው ምሽጋቸውን ለቀው ወደ ሜዳ ሲወጡ ነው፡፡ ስለሆነም የጉራ የመጨረሻ ውጤት ለኢትዮጵያ ድል ሲሆን ለግብፅ ግን የመስፋፋት ዓላማዋ ላንዴም ለሁሌም መቀጨት ሆነ፡፡

ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቆና በዘመናዊ ድርጅት ታንፆ የመጣን ጦር በወኔ በመቋቋም ጉንደትና ጉራን የሚተካከሉ ጦርነቶች በዘመናችን መጥቀስ ያዳግታል፡፡ የዳይ ዜና ጦርነት ይህን ወኔ አጉልቶ ይስለዋል፤

> የመድፍ ግባት ከግብፅ የጦር መሥመር የጀመረ ከሜዳ ባሻገር ያስተጋባ ነበር፡፡ ከቀኝ ከመሐል ሮኬቶች በሚያስፈራ ቅንጅት እየተምዘገዘጉ ይበራሉ፡፡ ከግራ ከቀኝ በፍጥነት እየቀረበ በሚመጣው ጠላት ላይ ሞት አዘል የጥይት ዝናብ ይወርዳል፡፡ ኢትዮጵያውያኑ እርምጃቸውን ሳያጥፉ ወደ ግብፆች ተቃረቡ፡፡ ቀለሀ ሲፈነዳ ጋላቢያቸውን ያጡ ሌጣ ፈረሶች ይደነብራሉ፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ ጠላት ጨክኖ እየገፋ መጣ፡፡ (Dye, 359)

ባንድ በኩል የጉንደትና የጉራ ድሎች ከ20 ዓመታት በኋላ ዓለምን ካስደነቀው ከዐድዋ ድል የበለጠ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው:: ምክንያቱም ዐድዋ ላይ ምኒልክ የተባበረች ኢትዮጵያን መርቶ የተዋጋ ሲሆን ዮሐንስ ግን ግብፆችን የገጠማቸው የግማሽ ኢትዮጵያን ኃይል ብቻ አሰልፎ ነው:: ምኒልክ በገለልተኝነት፣ የጐጃሙ አዳል ተሰማ ደግሞ የውስጥ አመፅ እያከሸፈ በመሆኑ ከጉንደትና ጉራ ጦር ሜዳ አልተሰለፉም:: በተጨማሪም ጉንደትና ጉራ በባላጋራዋ በግብፅ ላይ ያሳደሩት ተጽዕኖ ዐድዋ በኢጣሊያ ላይ ካስከተለው ለውጥ የላቀ ነው:: የጉንደት-ጉራ ሽንፈት የእስማኤልን ውድቀት ከማፋጠኑም በላይ የማታ ማታ ግብፅን የእንግሊዝ ተገዥ ለመሆን አበቃት:: ባንፃሩም ለዮሐንስ ድሉ ከፍተኛ ቁሳዊና ስነ ልቡናዊ ጥቅም አስገኝቶለታል:: ከግብፆች የማረከው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እንደ ምኒልክ ያሉትን ተቀናቃኞቹን ለማንበርከክ እንደረዳው ከላይ ተመልክተናል:: ባጠቃላይም፣ በተለይም በቤተ ክህነትና በአማንያን አካባቢ፣ ዮሐንስ የእስማኤልን የሙስሊም ጦር በመደምሰሱ የሃይማኖትና የሀገር ጠባቂ ተባለ::

ይሁን እንጂ በጉንደትና በጉራ ድል ማግስት ኢትዮጵያ ያገኘችው ጉልህ የሆነ ጥቅም ነበር ለማለት ያዳግታል:: ወታደራዊው ድል ዲፕሎማሲያዊ ድልን አልወለደም:: ግብፆች ለሰላም ድርድር ያቀረቧቸውን ሁኔታዎች ስንመለከት ማን ድል አድራጊ ማን ተሸናፊ እንደነበር እስከመጠራጠር እንደርሳለን:: የጦር ምርኮኞች እንዲመለሱላቸውና ነፃ የንግድ ልውውጥ እንዲከበር ከመጠየቅ አልፈው በዓለም የጦርነት ታሪክ ተደርጐ የማያውቀውን የተማረኩባቸው የጦር መሣሪያዎች እንዲመለሱላቸውና ከዚያም አልፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት በሐማሴን ግዛት እንቅስቃሴውን እንዲያቆም ጠየቁ:: ባንፃሩም ዮሐንስ የተሸናፊን በሐማሴን ግዛት እንቅስቃሴውን ... ለዘብተኝነት ተላብሶ ነበር:: ከድሉ በኋላ ግብፆችን ከቦጎስ ሆነ ከምፅዋ ለማስለቀቅ አንዳችም ወታደራዊ እንቅስቃሴ አላደረገም:: ይልቁንስ እንደበፊቱ ወደ ቪክቶሪያና ወደ እስማኤል የሰላም ጥሪ ደብዳቤ ላከ:: ወታደራዊ እርምጃን ያልመረጠበት የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ::

እንድም የዘመኑ ወታደራዊ ድርጅት ለረጅም ዘመቻ ያላመቸ በመሆኑ ሌላ ድል ስፈልግ ላደጋ ከምጋለጥ ያገኘሁትን ባጣጥም ይሻለኛል ብሎ ይሆናል:: አንድም ደግሞ ዕጣው ሆኖ ከሚገባው በላይ በልዩ ከበሬታ የሚያየው የአውሮጳውያን በጎ ፈቃድ ገሸሽ እንዳይልብኝ ብሎ ይመስላል:: ያም ሆነ ይህ ዮሐንስ የጦርነትን መንገድ ትቶ ለዐሥር ዓመት ያህል ያዳከረውን የሰላም መንገድ መረጠ:: በ1868 ክረምቱ ላይ ብላታ ገብረ እግዚአብሔር የተባለ መልእክተኛውን ወደ ካይሮ ላከ:: ለሰላም ያቀረባቸው ቅድመ ሁኔታዎችም ሁለት ነበሩ፤በግብፅ የተወሰዱት ግዛቶች መመለስና ለኢትዮጵያ ነፃ የባሕር ወደብ ማግኘት:: ይሁን እንጂ ግብፆች ለዮሐንስ የሰላም ጥሪት ምንም ዓይነት በጎ ፈቃድ እንደሌላቸው መልእክተኛውን ሁለት ወር አስረው ያለምንም ድርድር በመመለስ አሳዩት::



በ1869 አጋማሽ ላይ እስማኤል በተራው የሱዳኑን አገረ ገዥ እንግሊዛዊውን ኮሎኔል (ኋላ ጄኔራል) ቻርልስ ጎርደንን የሰላም መልእክተኛው አርጎ ላከው:: ነገር ግን ጎርደን ለድርድር ያቀረባቸው ሁኔታዎች በዮሐንስ ተቀባይነት ማግኘት የሚችሉ ዓይነት አልነበሩም:: የግዛቶችን ይዞታ በተመለከተ ጎርደን ምንም ዓይነት ለውጥ አላቀረበም:: ቦጎስ በግብፅ እንደተያዘ ሊቀር ነበር ማለት ነው:: ምንም እንኳ በምፅዋ ወደብ የንግድ ሸቀጦች መልእክቶችና መልእክተኞች በነፃ መተላለፍ ቢችሉም፣ የጦር መሣሪያን በተመለከተ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው መጠን ግብፆች በፈቀዱት ልክ ብቻ ሊሆን ነበር:: ጎርደን ከተመለሰ በኋላም እርቀ ሠላም እንዲያወርዱ ደጋግሞ የተማጠናቸው እንግሊዞች ዮሐንስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው መሠረት ያደረጎውን የነፃ ወደብ ጉዳይ ለማስተናገድ አልፈለጉም:: ምፅዋን ትቶ ዙላን ወይም አንፊላን እንኳ ፍቀዱልኝ ቢልም አልሰሙትም::

ቁም ነገሩ እንግሊዞች የዮሐንስ ወታደራዊ ድል ዲፕሎማሲያዊ ማሳረጊያ እንዲያገኝ ካለመፈለጋቸው ላይ ነበር:: ቀይ ባሕር ወይ በግብፅ አለዚያም ሌላ የእንግሊዝ ወዳጅ በሆነ መንግሥት ቁጥጥር ስር መቆየት አለበት ብለው ወስነዋል:: የግብፅ መንግሥት እየተዳከመ ሲሄድም በምትኩ አካባቢውን የሚያስተዳድር መንግሥት ማጨት ጀመሩ:: ዐይናቸውም ኢጣልያ ላይ አረፈ:: ኢጣሊያ ቀደም ብላ በስተደቡብ አሰብን ይዛለች:: ጎርደን ከዮሐንስ ጋር ፍሬ አልባ ድርድሩን አከናውኖ ሲሄድ ዙላን ለምን አንመርቅላትም የሚል ሐሳብ ወርወር አድርጎ ነበር:: ይህ እንደ ዋዛ የተጀመረ ነገር የኋላ ኋላ በ1877 እንግሊዞች ለኢጣሊያ ምፅዋን በወርቅ ሰሐን ሲሰጧት ማሳረጊያውን አገኘ:: የኢትዮጵያም ጦስ በዚያው ጀመረ::

ይህ ከመሆኑ በፊት ግን የዮሐንስ ዓላማ የመሳካት አዝማሚያ አሳየ:: ለዚህም አጋዥ ኃይል የሆነው በ1873 የማህዲስት ንቅናቄ በምድረ ሱዳን መከሰት ነው:: የእስልምና ተሐድሶንና የሱዳን ብሔርተኝነትን አጣምሮ የያዘው ይህ ንቅናቄ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰሜንና ማዕከላዊ ሱዳንን አጥለቀለቀው:: በዚህም ሂደት በምሥራቅ ሱዳን ያሉት የግብፅ ጦር ካምፖች ከካርቱምም ሆነ ከግብፅ ተቆርጠው ቀሩ:: በመሐሉም የግብፅም ነፃነት አከትሞ ግብፅ በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር ወድቃ ስለነበር፤ ይህን አዲስና አደገኛ ንቅናቄ የመግታቱና ተቆርጦ የቀረውንም የግብፅ ጦር በሰላም ለሀገሩ የማብቃቱ ኃላፊነት በእንግሊዝ ትከሻ ላይ አረፈ:: ይኸኔ ነው እንግሊዞች ለኢትዮጵያ የነበራቸውን ከንቀት እምብዛም ያልተለየ ቸልተኝነት ትተው እርዳታዋን አጥብቀው ለመሻት የተገደዱት:: ምክንያቱም ምሥራቅ ሱዳን የነበረው የግብፅ ጦር መዳን የሚችለው በኢትዮጵያ ምድር አቋርጦ ማለፍ ከቻለ ብቻ ነበረና:: ስለዚህ እንግሊዞች ሬር አድሚራል ሰር ዊልያም ሂዌት የተባለ መልእክተኛቸውን ወደ ዮሐንስ ልከው፣ በግንቦት 28 1876 ዐድዋ ላይ አንዳንዴ «የዐድዋ ውል» ሌላ ጊዜ በእንግሊዙ መልእክተኛ ስም «የሂዌት ውል» እየተባለ የሚታወቀውን ስምምነት ተፈራረሙ::

የውሉን ቃል ለተመለከተው ዮሐንስ ስምንት ዓመት የደከመበትን ፍሬ ያገኘ ይመስላል፡፡ የጦር መሣሪያን ጨምሮ ማናቸውም ሸቀጥ በነፃ እንዲገባለት ተደንግጓል፡፡ ቦጎስ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ተመልሳለች፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ሁለቱም ወገኖች ወንጀል የፈጸሙ ዜጎቻቸውን አስረው ለመመለስ ተስማምተዋል፡፡ በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ግምት ከፍተኛ ሥፍራ ያለውን ጳጳሳት ከእስክንድርያ የመላኩንም ጉዳይ ግብፆች በተቻለ መንገድ ለማቀላጠፍ ቃል ገብተዋል፡፡ ይህ ሁሉ ለዮሐንስ ድል ይመስላል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ውሉ በዘለቄታው ዮሐንስንም ሆነ ኢትዮጵያን ከጠቀመው ይልቅ ጎድቷል፡፡ በዚያን ጊዜ በነበረው የኃይል ሚዛን፣ የግብፅ ጦር በምሥራቅ ሱዳን ራሱን ለማትረፍ በሚራወጥበት ጊዜ፣ ዮሐንስ ቦጎስን ለማስመለስ የእንግሊዝ አስተናባሪነት አያስፈልገውም ነበር፡፡ እንዲያውም ከውሉ በፊት የመረብ ምላሹ ገዥ ራስ አሉላ ከአካባቢው ግብር መሰብሰብ ጀምሮ ነበር፡፡ ወንጀለኛ የመለዋወጥም ስምምነት እንግሊዞች በዮሐንስ ላይ ሸፍቶ ለነበረው ለደጃች ደበብ አርአያ በምፅዋ ጥገኝነት ሲሰጡት ባጭር ጊዜ ውስጥ ከንቱነቱ ታየ፡፡ በምፅዋ ሸቀጥ በነፃ የማስገባቱም ፈቃድ መሣሪያ ሳይሆን አንድ ለዮሐንስ የተላከ የቤተ ክርስቲያን ደወል በግብፅ ጉምሩክ ሲታገድ ከንቱ ሆኖ ቀረ፡፡ ይህ ሁሉ ብዙ ባልከፋም ነበር፡፡ የግፉ ግፍ ውሉ በተፈረመ በስምንት ወርና የእንግሊዝ ፖርላማ ባጸደቀው በሦስት ወር ውስጥ (በተለምዶ እንደሚባለውም ውሉ የተጻፈበት ቀለም ገና ሳይደርቅ) እንግሊዞች ምፅዋን ለኢጣልያ ሰጡ፡፡ ኢጣልያም አንድ ሳንቲም ሳታወጣ፣ አንድ ጥይት ሳትተኩስ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ያምዘገዘጋትን መቆናጠጫ አገኘች፡፡

የውሉ መዘዝ በዚህም አላለቀም፡፡ በውሉ ሦስተኛ አንቀጽ መሠረት ዮሐንስ በከሰላ፣ በአሚዴብና በሰንሂት ተቆርጦ የቀረው የግብፅ ጦር በኢትዮጵያ ምድር አቋርጦ ወዳገሩ እንዲመለስ አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት ቃል ገባ፡፡ ቃል ከመግባትም አልፎ ከእንግሊዞች ሸፍጥ ጋር በግልፅ በሚቃረን ሐቀኝነት ቃሉን አከበረ፡፡ በዚህ ሂደት የጦር አዛዡ ራስ አሉላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከማህዲስት ጦር ጋር ለመጋጨት በቃ፡፡ በዚያ የተጫረው እሳት የማታ ማታ ዮሐንስን ራሱን አጋየው፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊው ሩቤንሰን እንዳለው ዮሐንስ ከዐድዋው ውል ያተረፈው አንድ ደካማ ጠላት (ግብፅ) በሁለት ጠንካራ ባላጋራዎች (በኢጣልያና በማህዲስት ሱዳን) መተካት ሆነ፡፡

## መተማ፣ የሞት ጉዳና

ከጉንደትና ጉራ ድል በኋላ የነበሩት ጥቂት ዓመታት የዮሐንስ ኃይል እጅግ የገነነበት ወቅት ነበር፡፡ በውጭ የግብፆችን የመስፋፋት ፖሊሲ በማያዳግም ሁኔታ አጨናግፎታል፡፡ በውስጥ ዋና ተቀናቃኙን አንበርክኳል፡፡ በነዚህ ጣምራ ድሎች አማካይነትም በ19ኛው መቶ ዓመት ኢትዮጵያ ፊት ለተደቀኑት ሁለት ዐቢይ ፈተናዎች፣ አንድነትና ነፃነት፣ ዘላቂ መፍትሔ የሰጠ ይመስል ነበር፡፡ ዳሩ ግን ሁኔታው እንዲህ እንደሠመረ አልቆየም፡፡ ነገር እየተበላሸ ሄዶ ከ1877 በኋላ የዮሐንስ እድል ማሽቆልቆል ጀመረ፡፡ የኋላ ኋላም ለሞት በቃ፡፡ በተጠቀሰው ዓመት ጣሊያኖች ምፅዋን ያዙ፤ ኢትዮጵያና ማህዲስት ሱዳንም መዘዘኛ የሆነ ጦርነታቸውን ጀመሩ፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው የምኒልክ አልገዛም ባይነት እንደገና አገርሽቶ ሲብላላ ከቆየ በኋላ በ1880 ገሐድ የወጣው፡፡ በዚያውም ንጉሠ ነገሥቱን በሦስት ማዕዘን ቀልፎ የያዘው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ መተማ ላይ ሲሞት ፍጻሜውን አገኘ፡፡




የዚያ ውጥረት አንዱ ማዕዘን የኢጣልያ ቅኝ ግዛታዊ መስፋፋት ነበር፡፡ ጣልያኖች ምፅዋን ከእንግሊዝ እንደ ገጸ በረከት ካገኙ በኋላ እዚያ ሐሩራዊ የባሕር ጠረፍ ላይ ዝም ብለው አልተቀመጡም፡፡ ወደ ደጋው ክፍል ግዛታቸውን ለማስፋፋት ተጣደፉ፡፡ መጣደፍና የጋለ ስሜት፣ እነዚህ የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ልዩ ባሕርያት ነበሩ፡፡ ተወራራሽነትም ነበራቸው፡፡ ተለያይተው የነበሩት የኢጣልያ የተለያዩ ግዛቶች ተዋሕደው ባንድ መንግሥት ሥር መተዳደር የጀመሩት ገና በ1863 በመሆኑ የኢጣሊያ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የአፍላ ጎረምሳን ትኩስ ስሜት የሚያንጸባርቁ ነበሩ፡፡ መጣደፉ የመጣውም እንደ እንግሊዝና ፈረንሳይ ያሉ የደረጁ ቅኝ ገዥዎች ዓለምን ተቀራምተው ሲንሠራፉ እኔ ከዚህ ቡራኬ ሳልቋደስ ጀንበር ትጠልቅብኛለች ከሚል ሥጋት ነው፡፡ ይሁንና ኢጣልያ ጥረቷ ሁሉ መና ሆኖ እንዳይቀር እንግሊዝን የመሰለ አጋር ጣለላት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባት ፍላጎት የሌላት፣ ግን ደግሞ ጣውንቷን ፈረንሳይን ለማገድ የምትፈልገዋ እንግሊዝ ኢጣልያን ተጠቅማ ጥቅሜንም ታስከብርልኛለች በሚል ስሌት ማደፋፈር ቀጠለች፡፡

እርግጥ የኢጣልያ በቀይ ባሕር ዳርቻ መቆናጠጥ የተጀመረው ከዚህ ሁሉ በፊት ነው፡፡ በ1862 ኢጣልያዊው ሚስዮናዊ ጁሴፔ ሳፔቶና ሩባቲኖ የተባለ የመርከብ ኩባንያ ተቀናጅተው አሰብን ገዝተዋል፡፡ የኋላ ኋላም ይህ የግል ይዞታ የነበረው ወደብ ወደ ኢጣልያ መንግሥት ንብረትነት ተዘዋውሯል፡፡ ይሁን እንጂ የኢጣልያ የቅኝ ግዛት መስፋፋት መሠረት የሆነው አሰብ ሳይሆን ምፅዋ ነው፡፡ እዚህ ላይ ቀደም ሲል የጠቀስነውን የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ልዩ ባሕርያት፣ መጣደፍና የጋለ ስሜት፣ የምንገነዘብበት አንድ ሁኔታ አለ፤ ይኸውም ግብፅ በቀይ ባሕር ዳርቻ ላይ የነበራት ቁጥጥር እየተዳከመ ሲሄድ ወደቦቹ በተለያዩ የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች እጅ ወደቁ፤ ዘይላና በርበራ በእንግሊዞች፣ ታጁራ በፈረንሳይ፣ አሰብና በኋላ ምፅዋ በኢጣልያ፡፡ ልዩነቱ ግን ፈረንሳዮችና እንግሊዞች በባሕር ጠረፍ ቅኝ ግዛቶች (የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሶማሊላንድ ተብለው ለመታወቅ በበቁት) ሲታገሡ፣ የኢጣልያ ዐይን ግን ዘልቆ ወደ መሀል ኢትዮጵያ አማተረ፡፡ በሌላ አነጋገርም ምፅዋ የዐድዋ ጥንስስ ሆነ፡፡ እንደ ነቢይ ሁሉ ዮሐንስ የምፅዋንና የዐድዋን ተዛምዶ ተገንዝቦ ነበር፡፡ በ1879 መጀመሪያ ላይ ለምኒልክ በጻፈው ደብዳቤ «በእግዚአብሔር ቸርነት (ጣልያኖች) በዓለም ፊት ተዋርደውና ተንቀው ይመለሳሉ» ብሎ ነበር (Zewde፤199)፡፡

ዮሐንስ እነዚህን ቃላት ሲጽፍ ጣሊያኖች ከባሕር ዳርቻ ሃያና ሠላሳ ኪሎ ሜትር ያህል ገፍተው ሰሐጢና ዊያ የተባሉ ቦታዎችን ይዘዋል፡፡ ቀድመው

ምፅዋን በመያዛቸው ቢከፋም፣ እዚያው ታግሠው ይቀመጣሉ የሚል ከንቱ ተስፋ አድሮበት ነበር:: አሁን ግን ነገሩ ተለወጠ:: የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ የያዙትን የኢትዮጵያ ምድር እንዲለቁ ለኢጣልያው አዛዥ ደጋግሞ ቢጽፍም ከቁም ነገር አልቆጠሩትም:: የደብዳቤው ልውውጥ ውጤተ አልባ መሆኑን ሲያይ አሉላ ፈረሱን ጭኖ በጥር 20፣ 1879 ሰሓጢ ላይ መሽጎ በተቀመጠው የጣልያን ጦር ላይ ዘመተ:: ሆኖም መሽጎ የሚዋጋን ጦር ማጥቃቱ ቀላል ባለመሆኑ አሉላ ብዙ ሰው ካለቀበት በኋላ ለማፈግፈግ ተገደደ:: በማግስቱ ግን የሰሓጢውን ጦር ለመርዳት ከምፅዋ የተላከ 500 ገደማ ሠራዊት ያለበት የኢጣልያ ጦርን ዶጋሊ ላይ ገጥሞ ዶጋመድ አደረገው::



2.6 የምፅዋ ወደብ በ19ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ላይ


የዶጋሊ ጦርነት ዜና በኢጣልያ አገር በተሰማ ጊዜ ታላቅ ሽብር ፈጠረ:: የበቀል ጩኸት በኢጣልያ ጎዳናዎችና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አካባቢ ተሰማ:: የኢጣልያ ፓርላማ ለምፅዋና ላካባቢዋ መከላከያና ማጠናከሪያ የሚውል የሃያ ሚሊዮን ሊሬ በጀት መደበ:: ነባሩን ጦር የሚያጠናክር 5000 ሠራዊት ያለበት ልዩ ኃይል ተደራጀ:: መንገዶችና ድልድዮችም ለወታደራዊ እንቅስቃሴዎች እንዲያመቹ ተብለው ተሠሩ፣ ተጠገኑ:: ምኒልክን በዮሐንስ ላይ የማሸፈቱንም ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ ቀጠሉበት::



ጠቡን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዮሐንስም ጣልያኖችም የእንግሊዝን እርዳታ ጠየቁ:: ዮሐንስ የሂወት ውል ተሸሮ ጣልያኖች ምፅዋን እንዲይዙ በመደረጉ የተሰማውን ቅሬታ ገለጸ:: የንግሥት ቪክቶሪያ መልስ በተዘዋዋሪ መንገድ የጣልያኖችን ድርጊት ከመደገፋም በላይ ኢጣልያን ከመሰለ ኃያል መንግሥት ጋር መጋጨቱ ቢቀርበት የሚበጀው መሆኑን በመግለጽ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር ነበር:: የኢጣልያን መንገድ ለማመቻቸት ግን አሁንም እንግሊዞች አልተኙም:: ሰር ጀራልድ ፖርታል የተባለ መልእክተኛቸውን በመላክ ዶጋሊ የነሳቸውን በእርቅ ስም ሊያስገኙላቸው ሞከሩ:: አስታራቂ ተብሎ የተላከው ፖርታል ለድርድር ያቀረባቸው ነጥቦች ይህንኑ ሁኔታ በጉልህ የሚያሳዩ ነበሩ:: እነሱም ዮሐንስ ለዶጋሊ «እልቂት» ጣልያኖችን በይፋ ይቅርታ ሊጠይቅ፣ በተጨማሪም ጣልያኖች ሰሓጢን፣ዊያን፣ ከረንንና የአሳውርታና የሐባብ ሕዝቦችን ሀገር እንዲይዙ ነበር:: እንዲህ ያለውን እርቅ አሉላም ዮሐንስም አልተቀበሉትም:: በዚህን ወቅት ነው አሉላ በታሪክ ሲታወስ የሚኖርበትን ቃላት ለፖርታል የተናገረው፤ «ጣልያኖች ኢትዮጵያ ምድር ላይ የሚሰፍሩት እኔ የሮማ አገር ገዥ መሆን የቻልኩ እንደሆነ ብቻ ነው»::

በዚህ የዲፕሎማቲክ ሽፋን ተጠቅመው ግን ጣልያኖች ከዶጋሊ በኋላ ባደረጉት ማፈግፈግ ትተውት የነበረውን ሰሓጢን እንደገና ያዙ:: ለዮሐንስ ይሄ የመጨረሻው ትንኮሳ ነበር:: የጣልያንን ነገር እስከወዲያኛው ለመቋጨት በመጋቢት 1880፣ 80 ሺ ጦር አሰልፎ ወደ ሰሓጢ ዘመተ:: ባጭሩ እገኛለሁ ብሎ ተስፋ ያደረገበት ድል ግን እንደከዳው ቀረ:: ጣልያኖች ከምሽጋቸው አድፍጠው፣ አለምንም ወሳኝ ውጊያ እታክተው እንዲመለስ አስገደዱት:: ከቀድሞ ምሁራን አንዱ ብላታ ገብረ እግዚአብሔር ጊላ ማርያም እንደጻፈው፡ «እንግዲስ የሰው አገር እንገዛለን ብለው መጥተው ከምሽግ መኻል ከተሸሸጉ እኔ ምን አደርጋለሁ ብለው ሳይወጉ ተመለሱ::» (ገብረ እግዚአብሔር፣ 54) ዮሐንስ ፈጥኖ እንዲመለስ የተገደደበት ሌላ ምክንያት ደጀኑም ባስተማማኝ ሁኔታ ላይ ስላልነበረ ነው:: ባንድ በኩል ማህዲስቶች አይለው ጉንደርን በመውረር ቤተ ክርስቲያን ያቃጠሉበትና ቀሳውስት የገደሉበት ዘመን ሲሆን፤ በሌላ ወገን ደግሞ ምኒልክና ተክለ ሃይማኖት ተማምለው አፄውን ከድተዋል የሚል ወሬ በብርቱ ይነፍስ ነበር:: ያም ሆነ ይህ ሰሓጢ ዮሐንስ ከጣልያኖች ጋር ለመጨረሻ ጊዜ የተያየበት መድረክ ሆነ:: ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መተማ ሂዶ ሲሞት፣ ጣልያኖችም ይህንኑ ይጠባበቅ እንደነበር ሰው በፍጥነት የደጋውን ክፍል ወረው ኤርትራ ብለው የሰየሙትን የቅኝ ግዛት ከሰሜን ኢትዮጵያ ቀርፈው ለመፍጠር በቁ::

እዚህ ላይ ለንጉሠ ነገሥቱ ሞት ምክንያት የሆነውን የማህዲስት ንቅናቄ ትንሽ ዘርዘር አርገን እንመልከት:: ባንድ መልኩ የኢጣልያ ምፅዋን መያዝም ሆነ ብዙ ደም ያፋሰሰው የማህዲስቶችና የኢትዮጵያ ጦርነት ሁለቱም የግብፅ የመስፋፋት ፖሊሲ ቅሪቶች ናቸው:: ኢጣልያ በምፅዋ በእንግሊዝ አስተናባሪነት እንዴት የግብፅ አልጋ ወራሽ ለመሆን እንደበቃች አይተናል:: የማህዲስት ንቅናቄም ቢሆን ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ ማዞር የጀመረው ቀንደኛ ጠላቱን ግብፅን



2.6 የምፅዋ ወደብ በ19ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ላይ

ሲያሳድድ ነው። ንቅናቄው ሲጀምር ሁለት መሠረታዊ ባሕርያት ነበሩት፤ አንደኛው የእስልምናን እምነት ለማደስ፤ ሁለተኛ የተጠላውን የግብፅ አገዛዝ ለማስወገድ። ግብፅ የሃይማኖት መናፍቅና የፖለቲካ ጨቋኝ ሆና በመታየቷ የንቅናቄው የመጀመሪያ ዒላማ ነበረች። ነገር ግን ከላይ እንዳየነው ዮሐንስ የንቅናቄው የመጀመሪያ ዒላማ ነበረች። ነገር ግን ከላይ እንዳየነው ዮሐንስ የሂወትን ውል በሐቀኝነት አስፈጽማለሁ ሲል (ማለትም የግብፅ ወታደሮች በኢትዮጵያ ምድር አቋርጠው እንዲያመልጡ ሲረዳ) ኢትዮጵያን የማህዲስት ቀጣ ማሳረፊያ አደረጋት። የማህዲስቶች መርህ የጠላቴ ወዳጅ ከጠላትም ጠላት ነው የሚል ሆነ። በሌላ መልኩም የማህዲስትንና የኢትዮጵያን ጦር አራርቆ የነበረው የግብፅ ጦር ሲነሣ ሁለቱ የሣሉ ብረቶች መፋጨታቸው የማይቀር ነበር።

በኢትዮጵያና በማህዲስት ጦር መካከል የተደረገው የመጀመሪያው ውጊያ ከከሰላ በስተምሥራቅ በዛሬው የኤርትራ ክልል ውስጥ በሚገኝ ኩፊት በተባለ ቦታ ነበር። ሁለቱም ጦሮች በጊዜው ስመ ጥር በነበሩ ጀኔራሎች ነበር የተመሩት፤ የማህዲስቶቹ በኡስማን ዲግና፣ የኢትዮጵያ በአሉላ። መጀመሪያ አሉላም ቆስሉ ድል ወደ ማህዲስቶች የዞረ መስሉ ነበር። ኋላ ግን የኢትዮጵያ ጦር አይሉ ባለድል ሊሆን ቻለ። በሱዳን በኩል 3000 ሠራዊት ሲሞት በኢትዮጵያ ደግሞ የአሉላን ዋና የጦር አዝማች ብላታ ገብሩን ጨምሮ የዚያን ግማሽ የሚያህል አለቀ።

ሌላው የሁለቱ ኃይሎች የውጊያ መድረክ በስተደቡብ በምዕራብ ወለጋ ነበር። በአሶሳ ቤኒ ሻንጉልና ኮምሻ ቀደም ሲል ግብፆች የተወሰነ የአስተዳደር ቁጥጥር ስለነበራቸው ማህዲስቶችም በዚሁ እግር ተተኩ። የእስልምና ሃይማኖትና ንግድም አካባቢውን ከሱዳን ጋር የሚያስተሳስር ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ አካባቢ ያገሬው ሕዝብ ማህዲስቶችን ሆሣዕና ብሎ አልተቀበለም። በዚህ አካባቢ ቁጥጥራቸውን ካጠናከሩ በኋላ ማህዲስቶች ወደ ኦሮሞ ግዛቶችም መስፋፋት ጀመሩ። ይኸን ጊዜ ነው ምኒልክ ዋና የጦር መሪውን ራስ ጉበና ዳጨውን ልከ በጥቅምት 5፣ 1881 ነጆ አጠገብ ጉቴ ዲሊ የተባለ የጦር ሜዳ ላይ ባገኘው ድል እንዲነቱ ያደረጋቸው።

ዋና ፍልሚያ የነበረው ግን ዓለም ሁሉ እንደሚያውቀው መተማ ላይ ነው። ሱዳኖች ጋላባት የሚሏት መተማ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ለረጅም ጊዜ የሰላምም ሆነ የጠብ መገናኛ መድረክ ሆና ቆይታለች። ስለዚህ ይህ አዲስ የግንኙነት ምዕራፍ ውሳኔውን እዚህ ማግኘቱም የሚያስገርም ነገር አይደለም። የግንኙነት ምዕራፍ ውሳኔውን እዚህ ማግኘቱም የሚያስገርም ነገር አይደለም። ምናልባት የሚገርመው ነገር መተማ በነዚህ ዓመታት የጦርነት ዐውድማ ሆናም ቢሆን የንግድ ግንኙነት እስከናካቴው አለመቋረጡ ነው። ባንድ በኩል ነጋዴዎች እንደ ሰላይም ሆነው ያገለግሉ ስለነበር ሁለቱም ወገኖች በንግዱ እንቅስቃሴ ጥቅምም ያገኙበት ነበር።

ግብፆች አካባቢውን ለቀው ከወጡ በኋላ ማህዲስቶች መተማ ተቆጣጥረው ወደ ምድረ ኢትዮጵያ አንዳንድ ዘረፋዎች እያደረጉ መተናኮስ



ጀመሩ። በዚህ ግንባር የንጉሠ ነገሥቱ ተጠሪ ሆኖ ማህዲስቶችን እንዲቋቋም የተመደበው የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ነበር። በጥር 1879 ማህዲስቶች ደምቢያን ከወረሩ በኋላ ተከታትሎ መተማን ወግቶ እቃጥሎ ተመለሰ። ባመቱ ማህዲስቶች አቡ አንጃ በተባለ ሌላ ዝነኛ ጀኔራላቸው እየተመሩ የተክለ ሃይማኖትን ጦር ከጣና በስተሰሜን ምዕራብ ሣር ውሃ በሚባል ሥፍራ ገጥመው አሸነፉ። አከታትለውም ጉንደር ከተማ ድረስ በመዝለቅ እስካሁን ድረስ በከተማው ሕዝብ ዘንድ ጉልህ ሆኖ የሚታወሰውን የማቃጠልና የግድያ ተግባር ፈጸሙ።

ዮሐንስ ከበታቾቹ ጋር የነበረው ግንኙነት እንዳይድን ሆኖ የሻከረውም በዚሁ ዓመት ነው። ወደ ሰሓጢ በሚዘምትበት ወቅት ምኒልክ ታማኝነቱን ለመግለጽ ያህል አብሬ ልዝመት ብሎ ካንገት በላይ ጠይቆ ነበር። ዮሐንስ ለጣልያኖች እኔ እበቃለሁ አንተ ከጉንደር በስተደቡብ እምባጫራ ላይ ሆነህ የማህዲስቶችን እንቅስቃሴ ተቆጣጠር ብሎ መለሰለት። የምኒልክ የሰሜን ኢትዮጵያ ዘመቻ ጉንደርን ከማህዲስት መዓት አላዳናትም። ወደ ሸዋ ሲመለስ ግን ጉጃም ጎራ ብሎ በሣር ውሃ ሽንፈትና በቤተ ሰቡ የማህዲስት ምርኮ መሆን ሲበሳጭ ከነበረው ከተክለ ሃይማኖት ጋር ተገናኝቶ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለማመፅ አሲሮ ተመለሰ። ዮሐንስ ይህን እንደሰማ በጎጃም ላይ ለራሱም የዘገነነውን ፍጅት ዐወጀ።

የሚቀጥለው ዒላማው ሸዋ ነበር። ምኒልክም ነገር መከረሩን ሲያውቅ ጣልያኖች በመሣሪያ እንዲያግዙት ተማጠነ፤ የሸዋ ሕዝብም ለክብሩና ለነፃነቱ እንዲጋደል ክተት ዐወጀ። ኢትዮጵያ ከርስ በርስ ጦርነት ጫፍ ላይ ተንጠለጠለች። በመጨረሻ ግን ዮሐንስ ሐሳቡን ለውጦ ጦሩን ወደ ማህዲስቶች አዞረ። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች በታሪክም በአፈ ታሪክም ተሰጥተዋል። መሠረታዊው ምክንያት የሚመስለው ግን የማህዲስቶች ጉዳይ ብዙ ያልተወሳሰበ ችግር በመሆኑ የነሱን ነገር እንዴ ዳር አድርሼ ተወራራሽ ወደሆኑት ወደ ኢጣልያና የምኒልክ ችግር እመለሳለሁ በማለት ይመስላል። እንደሚታወቀው ይህ ሊሆን አልቻለም። መተማ ጦርነት ላይ (መጋቢት 2፣ 1881) ድል አፋፍ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ንጉሠ ነገሥቱ ቆስሉ ሲወድቅ ተበተነ። ይሸሽ የነበረው የማህዲስት ጦር አባራሪ ለመሆን በቃ። ንጉሠ ነገሥቱም በዚህ ሽንፈት ላይ ሞተ። ማህዲስቶችም ራሱን ቆርጠው በእንጨት ላይ ሰቅለው ለግብፅ ማስፈራሪያ አደረጉት።

## የዘመናዊት ኢትዮጵያ መመሥረት

ከ19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ተበታትነው የነበሩትን የኢትዮጵያ ግዛቶች የማዋሐዱ ተግባር ተቀዳሚ እየሆነ መጥቷል። ይሁን እንጂ የተለያዩ ነገሥታት ተግባሩን በተለያየ መንገድ ነበር የሚተረጉሙት። ለቴዎድሮስ አንድነት ማለት ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት መመሥረት ማለት ነበር። ለዮሐንስ ደግሞ

የውስጥ ነፃነት ያላቸው የክልል ገዥዎችና የበላይነቱ የታወቀለት ንጉሠ ነገሥት ተከባብረው የሚኖሩበት ሥርዓት ማለት ሆነ። ቴዎድሮስ መቅደላ፣ ዮሐንስ መተማ ላይ ሲሞቱ ሁለቱም ስልቶች የተጠበቀውን ውጤት እንዳላመጡ ግልጽ ነበር። ቴዎድሮስም ማዕከላዊ መንግሥት መመሥረት አልቻለም። ዮሐንስም የበላይነቱ አልከበር ማለት እንዳሳበደው የማህዲስት ጥይት እራት ለመሆን በቃ። ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሥታት ዓላማቸው ቢከሽፍም የነደፉት ሐሳብና የተለሙት መንገድ በተከታዩ ትውልድ ላይ አሻራቸውን ሳይተዉ አላለፉም።

ምኒልክ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለው ዓይነተኛ ሥፍራ የሁለቱን ሕልምና ትልም ገሐድ ማድረጉ ነው። እንደ እሳት በሚንቀለቀለው የቴዎድሮስ ሕሊና የተፀነሰውን ያንድነት ሐሳብ ከሞላ ጐደል የዮሐንስን ስልት ተከትሎ ለፍሬ ከማብቃቱ ላይ ነው። ይሁን እንጂ በቴዎድሮስ ሕልምና በምኒልክ እውነታ መካከል ብዙ ልዩነት ነበር። ለቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ማለት በስተደቡብ ሸዋን ጨምሮ የሰሜንና የማዕከላዊ ኢትዮጵያን ግዛቶች ያቀፈ አገር ነው። በዘመነ ዮሐንስ ደግሞ ኢትዮጵያ ሰፋ ያለ ትርጓሜም ይዘትም እየያዘች መጣች፤ በሰሜን በራሱ ጥረት፣ በደቡብ ምዕራብና ደቡብ ምሥራቅ ደግሞ በተዘዋዋሪ ተገዦቹ ናቸው ብሎ በሚተማመንባቸው በተክለ ሃይማኖትና በምኒልክ አማካይነት። በዘመነ ምኒልክ ግን ኢትዮጵያ ከዚህ ሁሉ ገዝፋ ገናና ተብለው በሚታወቁት እንደ አፄ ዐምደ ጽዮን ያሉ የመካከለኛው ዘመን ነገሥታት ጊዜ ከነበራት የሰፋ ይዘት ለማግኘት በቃች። በዚህ ሂደትም ዘመናዊት ኢትዮጵያ ተፈጠረች። ከዐድዋ ድል በኋላ ዙሪያውን ከከበቧት የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች ጋር በተደረገው የድንበር መካለል ስምምነትም ዓለም አቀፋዊ ሰውነቷን አገኘች።

ለዘመናዊት ኢትዮጵያ መፈጠር መሠረት የሆነውን የመስፋፋት ፖሊሲ ምኒልክ የጀመረው ገና የሸዋ ንጉሥ ሆኖ እያለ ነው። በዚህም አዲስ ነገር መጀመሩ ሳይሆን የቀድሞ የሸዋ ገዥዎች፣ እነ አስፋ ወሰን (1768-1800)፣ እነ ወሰን ሰገድ (1800-1805) እና በተለይም ደግሞ የምኒልክ አያት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (1805-1840) የጀመሩትን መንገድ መቀጠሉ ነበር። የምኒልክ መስፋፋት ከቀድሞዎቹ የሚለየው አዳዲስ ክስተቶች ለሂደቱ ስፋትና ግፊት በመስጠታቸው ነው። ከነዚህም አንዱ አትራፊ የሆነውን የንግድ መሥመር ለመቆጣጠር ከጎጃም ጋር የተደረገው ፉክክር ነው። ሸዋና ጎጃም የጊቤን አካባቢ ተቆጣጥሮ ንግዱን ወደየፊናቸው ለመሳብ ያደረጉት ጥረት የኋላ ኋላ ለእምባቦ ጦርነት መንሥኤ ሆኗል።

ዓመታት እየገፉ ሲሄዱ የመስፋፋቱ ሂደት ኢትዮጵያውያንን ብቻ የሚመለከት ድራማ አለመሆኑ ግልጽ እየሆነ መጣ። እንዲያውም ከውጭ መንግሥታት ጥረትና ፍላጎት ጋር የቅርብ ዝምድና እንዳለው ተረጋገጠ። ምኒልክም ይህን በቅጡ መገንዘቡን የምናውቀው ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ሁሉ የአውሮጳውያንን ድጋፍ ለማግኘት በሚያደርገው ጥረት ነው። በዚህም መሠረት እምባቦ ላይ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ባለቤትነት ከተቀዳጀ በኋላ ጠላትም ወዳጅም እንዲያውቀው ብሎ ለአውሮጳ መንግሥታት መልእክት ላከ።



በተመሳሳይ ሁኔታ በ1879 ወደ ሐረር ሲዘምት ለኢጣልያ ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ (በሱም አማካይነት ለመላው አውሮጳ) በጻፈው ደብዳቤ ዘመቻው እንዴት ከታሪክም ሆነ ከጊዜያዊ የኤኮኖሚ ጥቅም አንፃር አስፈላጊ እንደነበረ ለማስረዳት ሞከረ። ከሁሉም በላይ ደግሞ በሚያዝያ 1883 እየገፉ የመጡትን የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች ለማገድ ሲል የኢትዮጵያን ታሪካዊ ድንበር ዕወቁልኝ ብሎ ዝነኛ በሆነው መልእክቱ ለአውሮጳ መንግሥታት ዘርዝሮ ገለጸ። ከዐድዋ ድል በኋላ የምኒልክ ሠራዊት በታደሰ ወኔ ድንበር ሲያሰፋ አውሮጳውያን፣ በተለይም እንግሊዞች፣ ደግሞ ይህን ለመግታት ሲሯሯጡ ቆይተው በመጨረሻ የድንበር ውል ሲፈራረሙ ነገሩ ማሰሪያ አገኘ።

## የመስፋፋቱ ሂደት

የሸዋ ኦሮሞ ግዛቶች ባብዛኛው ከምኒልክ ቀደም ብለው በነበሩት የሸዋ ገዥዎች ዘመን ከሸዋ መንግሥት ክልል ገብተዋል። ምኒልክ መስፋፋቱን ሲጀምር መጀመሪያ ያተኰረው ከኦሮሞዎች ቀጥለው በሚገኙት በጉራጌዎች ላይ ነበር። የጉራጌን አገር ለማስገበር ምኒልክ የመጀመሪያ ዘመቻዎቹን በ1867 አደረገ። በዚህም ወቅት ኋላም በሌሎች ግዛቶች ተደጋግመው የታዩት የመስፋፋቱ ዒላማ የሆኑት ሕዝቦች የሚሰጡት የተለያዩ ምላሾች መታየት ጀመሩ። እነሱም በሰላም መገበርና አሻፈረኝ ብሎ መዋጋት ናቸው። ጉራጌዎችን በተመለከተ የሰሜን ጉራጌዎች ወይም በትክክለኛ አጠራራቸው ክስታኔዎች የመጀመሪያው ዓይነት ምላሽ ምሳሌ ነበሩ። ክስታኔዎች በሰላም ስለመገበራቸው ሦስት ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል። እነሱም ለሸዋ መንግሥት የነበራቸው አንፃራዊ የጂኦግራፊ ቅርበት፣ የሃይማኖት አንድነት (ክርስቲያን መሆናቸው) እና ዙሪያውን ከከበቧቸው ኦሮሞዎች ጋር ከነበራቸው የዘመናት ግጭት የተነሣ አጋር መፈለጋቸው ናቸው። በተቃራኒው የምዕራብ ጉራጌ ሕዝብ ሊገብር የተገደደው ከረጅም ጊዜ ጦርነት በኋላ ነው። እንዲያውም ሐሰን እንጃሞ በተባለ የቀቤና መሪ አዝማችነት ጠንካራ የእስልምና ተሐድሶ ንቅናቄ ምዕራብ ጉራጌን አጥለቅልቆ የሸዋን አገዛዝ ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥሎት ነበር። ከወሎ የዮሐንስን በግድ የማጥመቅ ፖሊሲ የሸሹ ሙስሊሞች አዲስ ነፍስ እየዘሩበትና በማህዲስት ሱዳንም እየተደገፈ የሐሰን እንጃሞ ንቅናቄ አብዛኛውን ምዕራብ ጉራጌን ለማስለም በቃ። በሸዋም ጦር ላይ ብዙ ሽንፈት ካደረሰ በኋላ በመጨረሻ በራስ ጐበና የሚመራ ጦር በ1880 ድል አድርጎት ንቅናቄው ሊገታ ችሏል።

ይህ ከጊቤ ወንዝ በስተምሥራቅ የነበረው ሁኔታ ነው። በስተምዕራብ ያለው አገር የሸዋና የጎጃም መፋለሚያ ዐውድማ ሆነ። ጎጃሜዎች ቀደም ብለው ባካባቢው የበላይነት መመሥረት ችለው ነበር። ቀደም ብለን የጠቀስነው የልቼ ስምምነትም ምኒልክን ከአዋሽ ወንዝ በስተምዕራብ እንዳያልፍ አግዶት ነበር። ባንፃሩ ዮሐንስ ተክለ ሃይማኖትን የጎጃምና የከፋ ንጉሥ ብሎ በመሰየም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ግዛበት ንዳበት ብሎ ሰጥቶት ነበር። በአዝማቹ በራስ ደረሶ ጥረትም ጎጃም ከዐባይ በስተደቡብ ባሉት የኦሮሞ ግዛቶች ላይ የበላይነቷን



2.7 የሌቃ ነቀምቴው ገዥ ደጃች ገብረ እግዚአብሔር (ኩምሳ) ሞሮዳ

መሥርታለች። እነዚህ የኦሮሞ ግዛቶች ለጎጃም ግብር መክፈል፣ አንዳንድ ዜጎቻቸውም በጎጃም ሠራዊት እየተመለመሉ መሰለፍ ጀምረዋል። ቀሳውስቱም የወታደሮቹን ኮቴ እየተከተሉ የክርስትና ሃይማኖትን ማስፋፋት ይዘዋል።

የምኒልክ አዝማች ራስ ጐበና ዳጬ ወደዚህ አካባቢ ሲመጣ ይህን ቀደም ብሎ የተመሠረተውን የጎጃም የበላይነት ብርቱ ፈተና ላይ ጣለው። የኦሮሞ ግዛቶችም ለየትኛው እንገብር ሲሉ ማወላወል አደረባቸው። በሁለቱ የጦር አዝማቾች መካከል ግጭት መፈጠሩ የማይቀር ነበርና በጥር 1874 ጉልበት ተፈታተሹ፤ ይህ የእምባቦ መቅድም መሆኑ ነው። የራስ ደረሶ ጦር በግብርም በዘረፋም የሰበሰበውን የዝሆን ጥርስ ጥሎ ለመሸሽ ተገደደ። በዚህም ምክንያትም እንዲህ ሲባል ተተረተ፤

እንግዲህ ጎጃሞች በምን ይስቃሉ፣<br>ጥርሳቸውን ሊሙ ትተውት ሄዱ አሉ።

ከዚህ በኋላ አውራዎቹ ተክለ ሃይማኖትና ምኒልክ፣ ለዋናው ፍልሚያ ሥነ ልቡናዊ ዝግጅት ይመስል ንቀት የተመላበት የደብዳቤ ልውውጥ አደረጉ። በመጀመሪያ ከተክለ ሃይማኖት ለምኒልክ በቃል የተላለፈው መልእክት ይህን ይመስል ነበር (ጎሩይ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፤ 129)፤







2.8 የጅማው ገዥ ዳግማዊ አባ ጅፋር 2.9 የሐረሩ ገዥ አሚር ዐብዱላሂ

ምነው እርስዎ እኔን ሁልግዜ ያዋርዱኛል። ከዚህ ቀድሞ በኃይል መጥተው አገሬን ጐጃምን አጥፍተውት ሔዱ። አሁን ደግሞ ያቀናሁትን የጋላውን አገር እያጠፉ ሹም ሽር አደረጉበት። ከእንግዲህስ ወዲህ መጣሁ አይሒዱ፤ ከጉድሩና ከሖሮ ከጅማና ከጨሌያ በወደዱት አገር የጠራ ሜዳ ይዘው ይቆዩኝ። ይህንንም ቃል በደብዳቤ አለመላኬ ደብዳቤውን ብቻውን አይተው ቀደው ጥለው፣ ሰምተው እንዳልሰማ ሆነው ሸሽተው ይሄዳሉ። በቃል የሆነ እንደሆነ ግን አሽከርዎችዎ ይታዘቡዎታልና በቃል መላኬ ስለዚህ ነው።

የምኒልክም ዐጸፋ ከዚህ የሚተናነስ አልነበረም።

እኔ ለአንተ ጦርነት ሰግቼ ሸሽቼ አልሔድም፤ ግን ከኔ ጋራ ለመዋጋት ከአፄ ዮሐንስ ፈቃድ አግኝተህ እንደ ሆን ፈቃድ ማግኘትህን በደብዳቤ እንድትልክብኝ ነው እንጂ ለጦርነቱስ እዚያው አገርህ ደረቤ ሜዳ ላይም ቢሆን እመጣልሃለሁና አንተን መንገድ አይምታህ፤ ይህንም በደብዳቤ አለመላኬ አንተ ደብዳቤውን ስትጠላው ዓይቼ ነው።



2.7 የሌቃ ነቀምቴው ገዥ ደጃች ገብረ እግዚአብሔር (ኩምሳ) ሞሮዳ

መሥርታለች። እነዚህ የኦሮሞ ግዛቶች ለጎጃም ግብር መክፈል፣ አንዳንድ ዜጎቻቸውም በጎጃም ሠራዊት እየተመለመሉ መሰለፍ ጀምረዋል። ቀሳውስቱም የወታደሮቹን ኮቴ እየተከተሉ የክርስትና ሃይማኖትን ማስፋፋት ይዘዋል።





2.8 የጅማው ገዥ ዳግማዊ አባ ጅፋር



2.9 የሐረሩ ገዥ አሚር ዐብዱላሂ

ምነው እርስም እኔን ሁልግዜ ያዋርዱኛል። ከዚህ



2.10 የወላይታ ንጉሥ ካዎ ጦና

እንደ ተፎካከሩትም ግንቦት 29 1874 የጠራ ሜዳ ፈልገው ሆሮ ጉድሩ ውስጥ እምባቦ ላይ ተዋጉ:: ብርቱ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ የጎጃም ነፍጥና መድፍ በሸዋ ፈረሰኛ (በተለይም በሰላሌና በወሎ ጦረኞች) ተንዶ ምኒልክ ለድል፣ ተክለ ሃይማኖት ለምርኮ በቁ::

የእምባቦ ድል ለምኒልክ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ መግቢያ ፓስፖርቱ ነበር:: ያለ ብዙ ተቃውሞ የኦሮሞ ግዛቶች አንድ ባንድ ለምኒልክ ገበሩ:: ከእምባቦ ድል በኋላ በሚከተሉት አራት ዓመታት የሌቃ ነቀምቴው ኩምሳ ሞሮዳ (ከገበረና ክርስትና ከተነሣ በኋላ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር የተሰኘው)፣ የጂማው አባ ጂፋርና ሌሎቹ የጊቤ ነገሥታት እና የኢሉባቦር መሪዎች በሙሉ የምኒልክን የበላይነት ተቀበሉ:: የእነዚህ ግዛቶች መገበር ለምኒልክ የማያቋርጥ



የገቢ ምንጭ በመፍጠር ፖለቲካዊና ወታደራዊ አቋሙን አደርጅቶ ለአፄያዊ ዙፋን ዋነኛ ተፎካካሪ ለመሆን አበቃው:: ስለዚህ እምባቦ ለምኒልክ ተጨማሪ ግዛት ብቻ ሳይሆን ማዕከላዊውንም ሥልጣን ነው ያስጨበጠው ማለት ይቻላል::

ምኒልክ የሩቁ እንደዚህ ሲሠምርለት የቅርቡ ግን በጣም አስጨንቆት ነበር:: ገናና የነበሩት የወለጋና የጊቤ ኦሮሞ ነገሥታት በሰላም ሲገቡለት ያን ያህል ያልደረጁት የአርሲ ኦሮሞዎች ከባድ ሥጋት ላይ ጣሉት:: በመጨረሻ ሊገብሩ የቻሉትም ከአራት ዓመታትና ከስድስት ዘመቻዎች በኋላ ነው::



2.11 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክና ከዘመኑ መኳንንት ጥቂቶቹ


እንደተለመደው መጀመሪያ ምኒልክ የሱን የበላይነት እስካወቁ ድረስ በውስጥ አስተዳደራቸው እንደማይገባ አረጋግጦ ለአርሲ አውራዎች ልኮ ነበር:: ከነዚህ ውስጥ ሉፋ ኩሶና ዳሙ ኡሱ የተባሉት ባላባቶች ሐሳቡን ቢቀበሉትም ሌሎቹን አውራዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ማሳመን አልቻሉም:: ከዚያ በኋላ አርሲዎች የጦርነቱን ጎዳና መርጠው ከየጎሳው ሠራዊት እየተውጣጣ መጠነኛ ጦር አሠልፈው የስሜኑን ግፊት ለመቋቋም ቆረጡ:: ነፍጥ ታጥቆ የመጣውን የምኒልክ ሠራዊት በጦር መመከቱ ብዙ ቢያስጠቃቸውም የደፈጣ ውጊያ በማድረግ የሸዋን ጦር አዋከቡት:: ጉዳዩ ስላሳሰበው ምኒልክ ራሱ ባንዳንዶቹ ዘመቻዎች ተሳትፎ ነበር፤ እንዲያውም ባንደኛው ሕይወቱ ለጥቂት ነው የተረፈችው:: የመጨረሻው ወሳኝ ውጊያ አዙሌ በተባለ ሥፍራ በመስከረም 1879 ተካሄደ:: በንጉሡ አጎት በራስ ዳርጌ የሚመራው የሸዋ ጦር ባንድ ወገን የአርሲዎችን መከፋፈል ተጠቅሞ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአርሲን ተዋጊዎች እያዋዛ የሸዋ ጦር በደንብ ወደ መሸገበት ቦታ አምጥቶ ወሳኝ ድል ለማግኘት በቃ::



2.10 የወላይታ ንጉሥ ካዎ ጦና

የገቢ ምንጭ በመፍጠር ፖለቲካዊና ወታደራዊ አቋሙን አደርጅቶ ለአፄያዊ ዙፋን ዋነኛ ተፎካካሪ ለመሆን አበቃው:: ስለዚህ እምባቦ ለምኒልክ ተጨማሪ ግዛት ብቻ ሳይሆን ማዕከላዊውንም ሥልጣን ነው ያስጨበጠው ማለት ይቻላል::

ምኒልክ የሩቁ እንደዚህ ሲሠምርለት የቅርቡ ግን በጣም አስጨንቆት ነበር:: ገናና የነበሩት የወለጋና የጊቤ ኦሮሞ ነገሥታት በሰላም ሲገቡለት ያን ያህል ያልደረጁት የአርሲ ኦሮሞዎች ከባድ ሥጋት ላይ ጣሉት:: በመጨረሻ ሊገብሩ የቻሉትም ከአራት ዓመታትና ከስድስት ዘመቻዎች በኋላ ነው::



2.11 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክና ከዘመኑ መኳንንት ጥቂቶቹ

አርሲ ለምኒልክ ወደ ሐረር መሸጋገሪያ መሰላል ሆነች፡፡ ግብፆች ይቺን የምሥራቅ ኢትዮጵያን የንግድና የባህል መዲና ከዐሥር ዓመታት አገዛዝ በኋላ በ1877 ትተው ሲወጡ የአሚሩን ሥልጣን መልሰው ነበር፡፡ የመጨረሻው አሚር ለመሆን እጣው የሆነው አሚር ዐብዱላሂ ባጭር ዘመን እስልምናን የማጠናከርና የአካባቢውን ኦሮሞዎች የማስገበር ፖሊሲ ጀመረ፡፡ ምኒልክ የግብፆችን መውጣት ያየው የሐረር ነፃነት ከመመለሱ አኳያ አልነበረም፡፡ ነፃነቱን ይዘልቃል ብሎ ስለማያምን የሱ ሥጋት ከዛሬ ነገ ዳር ከሚያንዣብቡበት የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች አንዱ ወደ መሀል አገር ሰርጎ መግቢያ ቀዳዳ ያደርገዋል የሚል ነበር፡፡ በዐብዱላሂ ዘመን የነበረው ጠቅላላ አለመረጋጋትና በተለይም በሚያዝያ 1878 አንድ የኢጣልያኖች ቡድን ጀልዴሳ ላይ አደጋ ተጥሎበት አባላቱ ማለቃቸው አካባቢውን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ አውሮጳውያንን የሚያሳምንበት ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ታየው፡፡ ከዘመቻው በፊት ለኢጣልያው ንጉሥ ኡምቤርቶ የጻፈው ደብዳቤም ይህንኑ የተመረኮዘ ነበር፡፡ ምኒልክ ዲፕሎማሲያዊ ቅድመ ዝግጅቱን ካጠናቀቀ በኋላ በሐረር ላይ ዘመተ፡፡ በደጃች ወልደ ገብርኤል ይመራ የነበረው ቀዳሚ የሸዋ ጦር ግን ወታደሮቹ እየከዱ ስላስቸገሩት ብዙም አልተሳካለትም፡፡ ነገር ግን መጨረሻ ታኅሣሥ 29፣ 1879 በዕለተ ገና ዋናው ጦርነት ጨለንቆ ላይ ተደረገ፡፡ የሐረር ጦር በመሣሪያ፣ በሰው ኃይልና በጦር ስልት ተበልጦ ተሸነፈ፡፡ አሚሩ ወደ ጅጅጋ ሲሸሽ ምኒልክ በድል አድራጊነት ሐረር ከተማ ገባ፡፡ ከዚያም የአክስቱን ልጅ ደጃች (ኋላ ራስ) መኰንን ወልደ ሚካኤልን የሐረር ገዥ አድርጎ ሹሞ ተመለሰ፡፡

ከሐረር ዘመቻ በኋላ ለሰባት ዓመት ያህል የምኒልክ ግዛት የማስፋፋት ፖሊሲ ጋብ አለ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ምኒልክ ሙሉ ሐሳቡን በሁለት ዋና ነገሮች ላይ ማሳረፍ ስለነበረበት ይመስላል፡፡ እነሱም አፄያዊውን ዙፋን መውረስና የኢጣልያን ኢትዮጵያን ቅኝ የማድረግ ጥረት መቋቋም ነበሩ፡፡ የመስፋፋቱ ሂደት እንደገና የቀጠለው በ1887 ከዘመቻዎቹ ሁሉ ከአሰቃቂነቱ ምናልባት ወደር በሌለው በወላይታ ዘመቻ ነው፡፡ የወላይታው ንጉሥ ጦና ከሱ በፊት የነገሠው ካዎ በሰላም ለምኒልክ ለመገበር የጀመረውን እርምጃ ተቃውሞ በሕዝብ ድጋፍ ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ሕዝቡን ለጦርነት አንቀሳቀሰ፡፡ ወላይታ በለምለምነቷ የታወቀች ግዛት በመሆኗ ክፉ ቀን እየተባለ በሚታወቀውና አራት ዓመት ያህል በቆየው ታላቅ ረሃብ ለሰለለው የምኒልክ ጦር የተለየ ማራኪነት ነበራት፡፡ ስለሆነም ከግብሩ ለመቋደስ ያልዘመተ ስመጥር የምኒልክ ጀኔራል አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ምኒልክ ራሱ በሚመራው ትልቅ ጦር ውስጥ ከሁለት ዓመት በኋላ ዐድዋ ላይ ስማቸውን የሚያስጠሩት እነ ራስ ሚካኤል፣ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ሊቀ መኳስ አባተ እና ደጃች ባልቻ ተሠልፈው ነበር፡፡ በተጨማሪም ራስ ወልደ ጊዮርጊስና የጅማው አባ ጅፋርም ተሳትፈው ነበር፡፡ የወላይታ ሕዝብ ይህን የመሰለ የኃይል ቅንጅት ለረጅም ጊዜ የሚቋቋምበት አቅም አልነበረውም፡፡ የተከተለውም ጦርነት ሳይሆን እልቂት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እልቂቱ ያባራውም አሻፈረኝ ብሎ መዋጋቱን የቀጠለው ጦና ቆስሎ ሲማረክ ነው፡፡



ከሦስት ዓመት በኋላ ከፋን ለማስገበር የተደረገው ዘመቻም ተመሳሳይ እልቂት የታየበት ነበር፡፡ ለአሥር ዓመት ያህል ኩሩው የከፋ ንጉሥ መጀመሪያ የጎጃምን፣ ኋላ የሸዋን የበላይነት አልቀበልም ብሎ በነፃነት ይኖር ነበር፡፡ ካንዴም ሁለቴም ለማስገበር የተላኩ ዘመቻዎችም እከፋ የማይበገር የመከላከያ አጥር ላይ ነጥረው ተመልሰዋል፡፡ የቁርጡ ቀን በ1889 መጣ፡፡ ገና ከጅምሩ የከፋ ገዥ ተብሎ በተሾመው በራስ ወልደ ጊዮርጊስ የሚመራ ጦር በአካባቢው ገዥዎች በእነ ደጃች ተሰማ (ኢሉባቦር)፣ ደጃች ደምስ (ወለጋ)፣ አባ ጅፋርና የኩሎና ኮንታ መሪዎች እየታገዘ በአራት ግንባር ከፋን ከበበ፡፡ የአባ ጅፋርና የኩሎና ኮንታ መሪዎች ዐቢይ ሚና በውል የሚያውቁትን የከፋ የመከላከያ አጥር የሚሰበርበትን መንገድ ለወራሪው ኃይል ማሳየት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ደከም ያለው በኩሎ በኩል የነበረው ድንበር በራስ ወልደ ጊዮርጊስ በሚመራው ጦር ተሰበረ፡፡ ወልደ ጊዮርጊስ ከፋ ዋና ከተማ አንዳራቻ በድል አድራጊነት ሲገባ ባምባገነናዊ አገዛዙ ምክንያት በሕዝቡ ዘንድ እምብዛም ተወዳጅ ያልነበረው ጋኪ ሼሮቾ ሸሽቶ አመለጠ፡፡ ዘጠኝ ወር ሲሳደድ ከቆየ በኋላ ተያዘ፡፡ በብረት ሰንሰለት ሲታሰርም ገናናው የከፋ ንጉሥ እንደ ተራ ወንጀለኛ በብረት አይታሰርም ብሎ ራሱ ባዘጋጀው የብር ሠንሠለት ታሰረ እየተባለ ይነገርለታል፡፡ የቀረውን ዘመኑን በእስራት እንዲያሳልፍ ሲደረግ፣ ወልደ ጊዮርጊስ ደግሞ በስም የነበረው የከፋ ገዥነት በተግባር ጸደቀለት፡፡


በዚሁ ዓመት ራስ መኰንን የሌቃ መሪዎች የሆኑትን ደጃች ጆቴንና ደጃች ገብረ እግዚአብሔርን አስከትሎ የኢትዮጵያን ድንበር ወደ ሱዳን ጠረፍ አሰፋ፡፡ እንግሊዞች ከሰሜን ትልቅ ጦር አሰልፈው እየገፉባቸው ሲመጡ ማህዲስቶች በአሶሳ፣ በቤኒ ሻንጉልና በኽሞሻ ላይ የነበራቸው ቁጥጥር እየላላ መጣ፡፡ እንዲያውም የሱዳኑ መሪ ኸሊፋ ዐብዱላሂ ይህን እያመፀ ያስቸግረው የነበረውን ግዛት ለምኒልክ መርቆለትም ነበር ይባላል፡፡ ሆኖም የምኒልክ ጦር በቀላሉ ሰተት ብሎ አልገባም፡፡ ዘላቂነት ባይኖረውም በቤኒ ሻንጉሉ መሪ በዐብዱራሕማን ኾጀሌ (በቅጽል ስሙ ቶር አል ጉራ) አማካይነት የተባበረ የጦር ግንባር መኰንንን ለመቋቋም ተነሣሥቶ ነበር፡፡ ሆኖም የአሶሳው ሸይኽ ኾጀሌ አፈንግጦ ከራስ መኰንን ጋር መላላክና የወርቅ ገጸ በረከት መላክ ሲጀምር የጋራው ግንባር ተሸነቆረ፡፡ ሸይኽ ኾጀሌ ለራስ መኰንን ያቀበለው መረጃ ኋላ ጦሩ ላገኘው ድልም አጋዥነት ነበረው፡፡ የመጨረሻው ፍልሚያ ፋዶኞ በተባለ ጦር ሜዳ ተደርጎ የግንባሩ ጦር መሪ ዐብዱራሕማን ተሸንፎ እንዲሸሽ ተገደደ፡፡ በተከታታይም የኽሞሻው ሙሐመድ ወድ ማሕሙድ ጠቅሎ ወደ ራስ መኰንን በገባው በሼኽ ኾጀሌ ሲሸነፍ በአካባቢው የምኒልክ መንግሥት የበላይነት ተረጋገጠ፡፡ ራስ መኰንን ዘመቻውን ፈጽሞ ከተመለሰ በኋላ ደጃች ደምስ እስከ ፋማካ ድረስ ጦሩን በመምራት ግዛት የማስፋቱን ተግባር ቀጠለ፡፡ ተሸናፊዎቹ ለጥቂት ዓመታት አዲስ አበባ በእስራት ቆዩ፡፡ እስራት ግን በስውር ከእንግሊዞች ጋር ሲላላክ ለተገኘው ለሸይኽ ኾጀሌም አልቀረለትም፡፡ ይሁን እንጂ በመጨረሻ ሁሉም በምኒልክ ስር የአካባቢ ገዥነታቸው ጸድቆላቸው ወደ ቀድሞ ግዛታቸው



2.12 የከፋው ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ




ተመለሱ:: ዐብዱራሕማን የደጃዝማችነት፣ ሙሐመድ የፊታውራሪነት ማዕረግ ሲሰጣቸው ኸጀሌ በመረጠው ብሸይኽነቱ ጸና::



2.13 ከእንጦጦና ከአዲስ አበባ በፊት የሸዋ ነገሥታት መዲና የነበረችው አንኮበር

## የአዲስ አበባ ልደት


ይህ ከላይ የተጠቀሰው የምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ሂደት እየቀጠለ እያለ የአገሪቱ ዘመናዊ መዲና ህልውናዋን አገኘች:: አዲስ አበባ በሚል ስያሜ ልትታወቅ የበቃችው ከተማ ከአክሱምና ከጎንደር ቀጥሎ ባገሪቱ ውስጥ ሦስተኛዋ ዋና ከተማ ሆነች:: በተጨማሪም ከዚያ በፊት ያገሪቱ ዋና ከተማ እንዲህ ወደ ደቡብ ዝቅ ብሎ የታየበት ጊዜ አልነበረም:: አዲስ አበባን ልዩ የሚያደርጋት ሌላው ነገር ከፖለቲካ ማዕከላዊነት በተጨማሪ በመልክዐ ምድራዊ አቀማመጧም አገሪቱ እምብርት ላይ መገኘቷ ነው::



2.12 የከፋው ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ



ተመለሱ:: ዐብዱራሕማን የደጃዝማችነት፣ ሙሐመድ የፊታውራሪነት ማዕረግ ሲሰጣቸው ኾጀሌ በመረጠው ብሸይኾነቱ ጸና::



2.13 ከእንጦጦና ከአዲስ አበባ በፊት የሸዋ ነገሥታት መዲና የነበረችው አንኰብር


## የአዲስ አበባ ልደት

ይህ ከላይ የተጠቀሰው የምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ሂደት እየቀጠለ እያለ የአገሪቱ ዘመናዊ መዲና ህልውናዋን አገኘች:: አዲስ አበባ በሚል ስያሜ ልትታወቅ የበቃችው ከተማ ከአክሱምና ከጐንደር ቀጥሎ ባገሪቱ ውስጥ ሦስተኛዋ ዋና ከተማ ሆነች:: በተጨማሪም ከዚያ በፊት ያገሪቱ ዋና ከተማ እንዲህ ወደ ደቡብ ዝቅ ብሎ የታየበት ጊዜ አልነበረም:: አዲስ አበባን ልዩ የሚያደርጋት ሌላው ነገር ከፖለቲካ ማዕከላዊነት በተጨማሪ በመልክዐ ምድራዊ አቀማመጧም አገሪቱ እምብርት ላይ መገኘቷ ነው::


ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ በነበረበት ዓመታት እንደ መካከለኛው ዘመን መሪዎች ከቦታ ቦታ እየተንቀራጠጠ ይገዛ ነበር:: የሸዋ መንግሥት ማዕከል ከነበረችው ከአንኮብር በተጨማሪ በልቼ (ሰሜን ሸዋ) እና በወረኢሉ (ደቡብ ወሎ) ጊዜያዊ መዲናዎች መሥርቶ ነበር:: ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ግዛቶች የመስፋፋት ፖሊሲውን በጽኑ ሲያያዘው የእንጦጦ ኮረብታዎች ዐይናቹን ይስቡት ጀመር:: ለጥቂት ጊዜ ያኔ እንጦጦ አሁን ግን ወጨጫ ተብሎ በሚታወቀው ኮረብታ ላይ ሰፈሩን ካደረገ በኋላ በ1874 ያኔ ዲልዲላ አሁን ግን እንጦጦ ተብሎ እሚታወቀው ገኸ ቦታ ላይ ማዕከለ መንግሥቱን መሠረተ:: የእንጦጦ ማራኪነት ከስትራቴጂካዊ ጥቅሙ ባሻገር ምኒልክ በልዩ አክብሮትና በአርአያነት የሚመለከታቸው የመካከለኛው ዘመን መሪዎች መዲና በዚህ አካባቢ ይገኝል የሚል አፈ ታሪክም በመኖሩ ነው:: ምኒልክ ባነፀው ቤተ መንግሥቱ ዙሪያም የደራ የመኳንንትና የቤተ መንግሥት አገልጋዮች ሠፈር ተመሠረተ:: በተጨማሪም ለአካባቢው ልዩ ሞገስ የሰጡትና አሁንም የሚሰጡት፣ ለንጉሣዊ ልግስናና ለበላይነት የሚፎካከሩት የማርያምና የራጉኤል አብያተ ክርስቲያን ተተከሉ::

ይሁንና የእንጦጦ ማዕከላዊነት ዘላቂነት አልነበረውም:: እንጦጦ ቋሚ የማዕከላዊነት መልክ መያዝ በጀመረች በአምስት ዓመት፣ በኅዳር 1879፣ ኋላ የአፄያዊው ግዛት ማዕከል ለመሆን የበቃው ሰፈር ከእንጦጦ በስተደቡብ በተንጣለለው ሜዳ ላይ ተመሠረተ:: ይህ ታሪካዊ እርምጃ የተወሰደው ምኒልክ በሐረር ዘመቻ ላይ እንዳለ በባለቤቱ በእቴጌ ጣይቱ ነው:: ለአዲስ አበባ መመሥረት መነሾ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ቀድሞውንም በእንጦጦ ሰፋሪዎች ዘንድ በሙቀቱና በፈዋሽነቱ ይዘወተር የነበረው ፍልውሀ ነው:: የመጀመሪያው ሰፈር እዚሁ ፍልውሀ አጠገብ መመሥረቱ ለዚህ አንድ ማስረጃ ነው:: በተጨማሪም በአካባቢው የነበሩ ኦሮሞዎች እንዲገብሩ ከተደረገ በኋላ የእንጦጦ ተራራ እስትራቴጂካዊ ጥቅም እየቀነሰ መጣ:: በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ ብርዳማነቱ፣ ሥርዓት በሌለው ጭፍጨፋም ዛፎቹ ተቆርጠው ማለቃቸውና ሠርክ ፍልውሀ ሲኬድ አቀበት የመውጣት የመውረዱ አታካችነት ተደማምረው እንጦጦን የቀድሞ ማራኪነቱን ነሡት::

አዲስ አበባ የተቆረቆረችው በ1879 ነው ቢባልም በርእሰ ከተማነት እንጦጦን መተካት የጀመረችው ግን ካንድ ስድስት ዓመት በኋላ ነው:: ግቢ ተብሎ የሚታወቀው ቤተ መንግሥት (ያሁኑ ታላቁ ቤተ መንግሥት) ሲታነፅ ከተማዋ ዋና መልኳን አገኘች:: ከዚያ በኋላ በስተምዕራብ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሲተከልና ባካባቢውም አራዳ የተባለው ገበያ ሲደራ ደግሞ የከተማይቱ የሃይማኖትም የንግድም ማዕከል ተመሠረተ:: መኳንንቱም የንጉሡን ፈለግ በመከተል በየጉብታዎቹ ላይ ሰፈራቸውን ተከሉ:: የያንዳንዱ ራስና ደጃዝማች ግቢ እንደ ንጉሡ ግቢ በአሽከሮችና በተከታዮች መኖሪያዎች የተከበበ ነበር::



2.14 አራዳ የአዲስ አበባ የንግድ ማዕከል፣ 1928



**2.14 አራዳ የአዲስ አበባ የንግድ ማዕከል፣ 1928**

በዚህ ሁኔታ ነው ራስ ብሩ ሰፈር፣ ራስ ተሰማ ሰፈር፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሰፈር እየተባሉ የታወቁት አምባዎች የተፈጠሩት:: ሁለተኛዎቹ የሰፈር ዓይነቶች ደግሞ የሥራ ጠባይን የሚያመለክቱና የቤተ መንግሥቱ ሠራተኞች መኖሪያዎች ነበሩ:: ለምሳሌም የሠራተኛ ሰፈር፣ የዘበኛ ሰፈር፣ የውሀ ስንቁ ሰፈር አፈጣጠር ይህን ስልት የተከተለ ነበር::

አዲስ አበባ ዋና መዲናነቷ እየጸደቀላት የመጣው በተለይም ከዐድዋ ድል በኋላ ነው:: 19ኛው መቶ ዓመት ዘመነ ጦርነት ከተባለ ባንፃሩ ዐድዋ የጦርነቶች ማሳረጊያ ነበር ማለት ይቻላል:: ስለሆነም የዘመቻ ባህል በተደላደለ ሰላማዊ ኑሮ ተተካ:: ጦረኞቹ መኳንንት የሲቪል አስተዳዳሪዎች ሆኑ:: በዋና መዲናይቱም ቋሚና ያጌጡ መኖሪያዎች መገንባት አስፈለጋቸው:: አሁን አልፎ አልፎ ለታሪክ የቆዩት አዳራሾች (ለምሳሌ የአዲስ አበባ ሙዚየም የሆነው የራስ ብሩ ቤት) የዘመኑ የሕንፃ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው:: በሌላ ወገን ደግሞ የዐድዋው ድል መሪ የምኒልክ ዝና በዓለም ሲናኝ የውጭ አገር ሰዎች በግልም በኦፊሲዬልም ወደ አዲስ አበባ መጉረፍ ጀመሩ:: እስካሁን እንደምናየውም ሌጋሲዮኖች የእንጦጦን ተዳፋት ይዘው የተንጣለለ ግቢያቸውን ከለሉ:: ነጋዴዎችና የእጅ ባለሙያዎች ደግሞ አራዳ ሰፈሩ::

ይሁን እንጂ አዲስ አበባም የእንጦጦ አደጋ አንዣበባት ነበር:: ጥቅጥቅ ብሎ የነበረው ደን እየተመነጠረ አልቆ ለማገዶም ሆነ ለሕንፃ የሚሆን እንጨት ሲጠፋ ምኒልክ ዋና ከተማውን ወደ አዲስ ዓለም ሳማዘዋወር በጽኑ አስቦ ነበር:: አዲስ ቤተ መንግሥት አሳንፆ ሁለቱ ከተሞች በአውራ ጐዳና እንዲገናኙም አድርጎ ነበር:: አዲስ አበባን ያዳኗት ሁለት ነገሮች ናቸው:: አንደኛው በሰፊ ግቢያቸው ተደላድለው የነበሩት ሌጋስዮኖች ተቃውሞ ሲሆን ሁለተኛው፣ ምናልባትም ዋነኛው፣ ምኒልክ የባሕር ዛፍ ችግኝ ከአውስትራሊያ ማስመጣቱ ነው:: ከዚያ በኋላ ከ1900 ጀምሮ የከተማ ቦታዎች እየተመዘገቡ የባለንብረትነት ካርታ ሲታደል በከተማይቱ ላይ ያንዣብብ የነበረው አደጋ እስከናካቴው ተገፈፈ:: በመጨረሻም ከጅቡቲ የተነሣው የምድር ባቡር በ1909 አዲስ አበባ ሲደርስ የኢትዮጵያ ዋና ከተማነቷ ለዘለቄታው ተረጋገጠ::

## ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ «ክፉ ቀን» (1880-1884)

ያገሪቱ ማዕከል ወደ ደቡብ እየተዘዋወረ ባለበት ጊዜ ኢትዮጵያን የረሀብ መቅሠፍት መታት:: ባገሪቱ የውስጥም የውጭም ጉዳዮች ላይ አሻራውን ትቶ የሄደው ይህ ዐቢይ ማኅበራዊ ቀውስ ቀደም ብለን ለጠቀስነው የመስፋፋት ሂደት ግፊት ከሰጡት ኃይሎች አንዱ ነበር:: መስፋፋቱ የጦር ዘመቻ ብቻ ሳይሆን ቀጠና ያባረረው ሕዝብ ፍልሰትም ጭምር ነበር:: ይሁን እንጂ ብዙ የተጠቃው ክፍል የሰሜኑ ቢሆንም ከመዓቱ ያመለጠ ክልል እምብዛም አልነበረም:: እንዲያውም ችግሩ ከኢትዮጵያም አልፎ በሱዳንና በሌሎች የምሥራቅ አፍሪቃ አገሮች ታይቶ ነበር:: የዚህ የዘመነ ቀጠና ሌላ ዐቢይ ውጤት ለኢጣልያ ወደ



ደጋው ክፍል የመስፋፋት ዕቅድ አጋዥ መሆኑ ነው:: ጣልያኖች የኤርትራ ቅኝ ግዛታቸውን መመሥረት የቻሉት በአፄ ዮሐንስ ሞትና ረሀቡ ባስከተለው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መናጋት ተጠቅመው ነው:: ምኒልክ ከዐድዋ ድል በኋላ ጣልያኖችን ከኤርትራ ለማስወጣት ያልቻለበት አንዱ ምክንያትም ረሀቡ ያስከተለው የስንቅ እጥረት ነው:: በአጠቃላይም ያዚህ ዘመን ረሀብ በሕዝብ ሕሊና የማይፋቅ ጠባሳ ትቶ ነው ያለፈው:: «ክፉ ቀን» በሚል ስም እየተዘከረ የኋለኛ ዘመን ረሀቦችን ማመዛዘኛና ማነፃፀሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል::

ላይ ላዩን ሲመለከቱት የረሃቡ መነሾ ጣልያኖች ወደ ምፅዋ ባመጧቸው ከብቶች አማካይነት የተላለፈ የደስታ በሽታ ነው:: በዚህ ሳቢያ ባንዳንድ አካባቢዎች ከመቶ ዘጠና የሚያህለው ከብት አልቋል:: አንዳንድ ሰዎች መላ የከብት ሀብታቸውን አጥተዋል:: ከብት በማለቁ ገበሬው ዋነኛ የምርት መሣሪያውን አጣ:: ባምና መኸር ያገግማል እንዳይባል እሱንም አንበጣና ድርቅ አጠናቆለታል:: ይሁን እንጂ የከብት በሽታ፣ የአንበጣ ወረራም ሆነ ድርቅ የችግሩ አፍአዊ ገጽታዎች ናቸው እንጂ ምንጮቹ አልነበሩም:: የረሀቡ መሠረት ያገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነበር:: የዘመኑ የጦርነት ወግ ገበሬውን በሞትና በሕይወት አፋፍ ላይ ተንጠልጥሎ እንዲኖር አስገድዶታል:: አንፃራዊ ሰላም ተገኘ በተባለበትም ወቅት ቢሆን ከዘረፋ ያልተለየው የግብር አሰባሰብ ሁኔታ ለክፉ ቀን መጠባበቂያ ይሆናል ብሎ የሚያስቀምጠውን እህል እንኳ አሟጦ እንዲያስረክብ አስገድዶታል::

ችግሩ በግልጽ መከሰት የጀመረው እህልና የከብት ዋጋ አለመጠን ሲንር ነው:: ይህ ለረሀብና ለሞት መቅድም ሆነ:: ይሁን እንጂ ሕዝቡ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ችግሩን ለመወጣት ብዙ ዘዴዎችን ሞከረ:: በማረሻ ፈንታ ዶማን፣ በጥማድ በሬ ምትክ አህያን፣ በቅሎን ወይ ፈረስን ተጠቀመ:: ጭንቅ ሲበዛበትም ልማድን ሽሮ ጠያፍ ይባሉ የነበሩትን ምግቦች ለመብላት ተገደደ:: ክልክል የሆኑ ዕፀዋት፣ ነውር ነው የሚባል ምግብ ጠፋ:: የባሰባቸው ከእበት ውስጥ ሳይታኘክ የተረፈ ጥራጥሬ ፈልገው ይበሉ ነበር ይባላል:: ከዚህም ሲከፋ ደግሞ ትርፉ ወዲያው መንፈራፈር ቢሆንም የሞተ ከብት ሬሳም እስከ መብላት የደረሱ ነበሩ:: ሰው ሰውን የበላበት፣ ከረሀብ ለማምለጥ ራሱን ለባርነት የሸጠበት፣ ወይ ነገር ሁሉ ሲጨልም ሕይወቱን ያሳለፈበት ወቅት ነበር::

የመንግሥት መዋቅር ይህን ያህልም ባልደረጀበት በዚያን ወቅት ረሀቡን ለማገድም ሆነ ለማቃለል የሚወሰዱት እርምጃዎች አመርቂ ሊሆኑ አይችሉም ነበር:: እንኳን ያኔ የዘመናችን ፍጹማዊ መንግሥታትም ረሀብን መቋቋም አልቻሉም:: ቢጨንቃቸው ምኒልክና ጣይቱ ዜጎቻቸውን እግዚአብሔርን አጥብቀው እንዲማለዱ መከሯቸው! ረሀቡ በዚህም አልበገር ሲል ምኒልክ ከልብ አልጸለያችሁም ብሎ ወቀሳቸው:: ከዚያ በመለስ ደግሞ ምግብ በማደል ቢያንስ ለቤተ መንግሥቱ ሩቅ ያልሆኑትን ዜጎቹን ረሀብ ለማቃለል ሞከረ:: ዜና መዋዕል ጸሐፊው ገብረ ሥላሴ እንደሚዘክርልን ምፅዋቱን ለማግኘት «የአራቱ ማዕዘን ሰው» (ማለትም ረሀብተኞች) እንጦጦን አጥለቀለቋት:: በቅርቡ ከገበሩት የሐረርና

የባሌ ግዛቶች የመጡ ሰንጋዎችም በተለይ ለመኳንንቱ እየታደሉ በነፍስ ደረሱላቸው:: አንዳንድ የተደበቀ እህልንም መንግሥት ውርስ እያደረገ ለተራበው ሕዝብ አደለ:: ሕዝቡ እንዲህ አራት ዓመት ከታመሰ በኋላ ነው ረሀቡ ጋብ ማለት የጀመረው::

## የውጭው አደጋ መወገድ

አንዳንዴ በአንድ ዓመት ውስጥ እንኳ ብዙ ልዩነት ይፈጠራል:: በ1860 በጄኔራል ናፒየር የሚመራው ግዙፍ የእንግሊዝ ጦር ኢትዮጵያ እምብርት ድረስ ዘልቆ አውሮጳውያን እስረኞችን ነፃ ካወጣ በኋላ አገሪቱን እንደ ዋዛ ለቆ ወጣ:: የእንግሊዝን መንግሥት በወዳጅ ዐይን የሚመለከት ገዢ በቴዎድሮስ እግር መተካቱን ለማረጋገጥ እንኳ አልተጨነቀም:: ከዚያም የበለጠ ግዴለሽነት ለማሰብ ያዳግታል:: በሚቀጥለው ዓመት ግን ነገር ሁሉ ተለዋወጠ:: የስዊዝ ቦይ ሲከፈት የቀይ ባሕር እስትራቴጂካዊም ሆነ የንግድ ጠቀሜታ ከፍ አለ:: የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎችም በባሕር ጠረፉ ላይ ግዛታቸውን ለመመሥረት መጣደፍ ጀመሩ:: የኋላ ኋላም የቦዩ ዓለም አቀፋዊ ዋጋ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ አውሮጳውያን መንግሥታት ይህ የመገናኛ መሥመር ለግብፅ የውስጥ ፖለቲካ ውጣ ውረድ ተገዥ መሆን አይገባውም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደረሱ:: የኸዲቭ እስማኤል መንግሥት ከተዘፈቀበት የእዳ ማጥ ውስጥ መውጣት ሲያቅተው፣ በሌላ ወገን ደግሞ እያደገ የመጣው ያውሮጳውያን ጣልቃ ገብነት ያስቆጣው የግብፅ ብሔረተኛ እንቅስቃሴ ሲያይል፣ እንግሊዞች ምድረ ግብፅን በቁጥጥራቸው ሥር አዋሏት::

ይህ ድርጊት የመላ አፍሪቃን ሕይወት የለወጠ ድርጊት ነበር:: አውሮጳውያን መንግሥታት አፍሪቃን ለመቃረጥ የጀመሩትም ከዚህ በኋላ ነው:: እንግሊዞች ግብፅን ይዘው ሊቆሙ አልቻሉም:: ግብፅን ሲይዙ የዐባይ ነገር ያባንናቸው ጀመር፤ ያለ ዐባይ ግብፅ ምድረ በዳ፣ ከትርፍ ይልቅ ዕዳ ነችና:: ስለዚህም አውራ ጠላቷ ፈረንሳይ የዐባይን ፈለግ ተቆጣጥራ ማነቆ እንዳትፈጥርባት መከላከል የእንግሊዝ ተቀዳሚ ተግባር ሆነ:: ነጭ ዐባይን እራሷ ለመከላከል ዝግጁ ስትሆን ለጥቁር ዐባይ ቃፊር አስፈለጋት:: ለዚህም ሚና ኢጣልያ ተመቻችታ ቀረበች:: ለዘመናት የቆየው እንግሊዝና ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የሸረቡት ሴራ መሠረቱ ይኸው ነው:: ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የተክለፈለፉትን ያህል እንግሊዝም ኢጣልያ የቃፊርነት ሚናዋን በሚገባ እስከተወጣችላት ድረስ እርዳታዋን ለመለገስ ዝግጁ ነበረች::

በኢትዮጵያም በኩል ለአውሮጳውያን ሠርጎ መግባት አጋዥ ሁኔታዎች አልጠፉም:: የኢትዮጵያ መሣፍንት በዋናው በሀገር ነፃነት ጉዳይ ላይ ቀናዒ ይሁኑ እንጂ የግል ኃይላቸውን ለማደርጀት የሚከተሉት ፖሊሲ የውጭ ጣልቃ ገብነትን የሚጋብዝ ነበር:: ከቴዎድሮስም በፊት ቢሆን፣ በተለይ ግን ከቴዎድሮስ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መሪዎች በተለያየ ምክንያት አውሮጳውያን አጋሮችን



እንደፈለጉ ነው:: ለዚህም አንዱና ዋነኛው ምክንያት ዘመናዊ መሣሪያ ፍለጋ ነው፤ የሚለገስ፣ የሚገዛ ሆነ ወይ እንደቴዎድሮስ አገር ውስጥ የሚፈበረክ:: ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ ከግብፅ ከበባ ለመውጣትና ነፃ የባሕር ወደብ የማግኘት ፍላጎት ናቸው:: የኢትዮጵያ መሳፍንት ከአውሮጳውያን ነገሥታት ጋር የሚያደርጓቸው የደብዳቤ ልውውጦች በእንዲህ ዓይነቱ ውትወታ የተሞሉ ነበሩ:: ከዚህም ጋር ተጣምሮ የአውሮጳውያን ነገሥታት ክርስቲያን ናቸውና ክርስቲያን ሲጠቃ ዝም ብለው አያዩም የሚል የዋህ አስተሳሰብም ነበር:: ቴዎድሮስ በ1855 ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፈውን ጣጠኛ ደብዳቤ «እናንተም ተገፉልኝ፣ ክርስቲያኑን, እስላም አጠቃህ ሲለኝ» በሚሉ ቃላት ነበር የደመደመው:: ከውጭው ዓለም ጋር በነፃ የባሕር በር ገደብ የሌለበት ግንኙነት ማድረግ የኢትዮጵያ ነገሥታት የማያቋርጥ ጥረት ነበር:: ይህንኑ ጉዳይ ምኒልክ በሚያዝያ 1883 ድንበሩን ለዓለም ባስታወቀበት ዝነኛ ሰርኩላር ማሳረጊያ ላይ በተለመደ ዲፕሎማሲያዊ ስልቱ እንዲህ ሲል ገልጾታል፤

> ቀድሞማ የኢትዮጵያ ድንበር ባሕር ዳር ነበር:: የኢትዮጵያ ጉልበት ቢያንስ የሚረዳን ክርስቲያን ብናጣ የባሕር ድምበራችን ከእስላሞች እጅ ገባ:: አሁንም የባሕር ዳር ድምበራችንን በጉልበታችን እናገኛለን አንልም:: የክርስቲያን ነገሥታት ትመልሱልናላችሁ:: ባይሆንም ከባሕር ዳር አንዳንድ ቦታ ትሰጡናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: (FO95/751)

የኢትዮጵያ መሳፍንት የውጭ አጋር የሚፈልጉበት ሌላ ምክንያት አፄያዊ ሥልጣንን በማዳከም ራሳቸው ዙፋኑን ለመያዝ ስለሚሹ ነበር:: ለምሳሌ ካሣ ምርጫ (የኋላው አፄ ዮሐንስ) የራሱን ሥልጣን ለማጠናከር በቴዎድሮስ ላይ ከእንግሊዞች ጋር አበረ:: በተመሳሳይ ሁኔታ ዮሐንስና ጣልያኖች በሰሜን ኢትዮጵያ ደም ሲቃቡ ምኒልክ የኢጣልያን ወዳጅነት ለመኮትኮት ያላሰለሰ ጥረት ያደርግ ነበር:: ኢጣልያኖችም ዐጸፋውን ለመመለስ ወደኋላ አላሉም:: ምኒልክ ለነሱ የዮሐንስን ደጀን መገዝገዣ ሁነኛ መሣሪያ ነበር:: የሚገርመው ነገር ግን ምኒልክና ኢጣልያ ግንኙነታቸውን በሞቀ ወዳጅነት ጀምረው ደመኛ ጠላት ለመሆን በቁ:: ይሁንና ነገሩ ላይ ላዩን ሲያዩት ይግረም እንጂ የራሱ የሆነ ምክንያት ወይም ሕግ ነበረው:: ምኒልክ በሸዋ ንጉሥነቱና በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነቱ ለኢጣልያ ያለው አመለካከት አንድ ዓይነት ሊሆን አይችልም:: መጀመሪያ አፄያዊ ሥልጣን ለመጨበጥ ሲል የተባበራቸውን ያህል ኋላ የራሱ ሥልጣንና ያገሩ ነፃነት ጥያቄ ላይ ሲወድቅ መሣሪያውን በነሱ ላይ ማዞሩ የሚጠበቅ ነበር::

የምኒልክና የኢጣልያ ግንኙነት በኦፊሲዬል የተጀመረው በማርኬዜ ኦራዚዮ አንቲኖሪ የሚመራ የመልክዐ ምድራዊ ጥናት ቡድን በ1869 ሸዋን

ሲጎበኝ ነው ማለት ይቻላል:: ጣልያኖች አሰብ ላይ ከተቆናጠጡ በኋላ ወደ መሀል አገር ለመግፋት ሲያስቡ ሸዋን ዒላማቸው አደረጉ:: በሌላ በኩል፣ ቀደም ብለን እንዳመለከትነው ይህ የኢጣልያ የጥናት ቡድን ተልእኮው ሙሉ በሙሉ አካዴሚያዊ አልነበረም:: በመላ አፍሪቃ እንደታየው ሁሉ እዚህም ምርምርና የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ተደጋጋፊ ነበሩ:: ምኒልክና አንቲኖሪ በመጨረሻ ባደረጉት ስምምነት ምኒልክ ከአውሮጳ ጦር መሣሪያ የሚገዛለት ወኪል ሲያገኝ፣ ጣልያኖች ደግሞ ለረጅም ዘመን የምርምርና የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ ሆኖ የሚያገለግላቸውን «ልጥ ማረፊያ» የተባለውን አንኮበር አጠገብ ያለ ቦታ አገኙ::

እንዲህ ቀስ በቀስ የጀመረው የምኒልክና የኢጣልያ ግንኙነት ጥልቀትና ዘላቂነት ያገኘው ካውንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ የተባለው ኢጣልያዊ ልዑክ በ1875 ወደ ሸዋ ከመጣ በኋላ ነው:: ይህ ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰውና መሻከር የጀመረውም በዚሁ በአንቶኔሊ አጋፋሪነት ነው:: በ1881 ሁለቱ የተፈራረሙት የውጫሌ ውል የዚህ ሁለት ተፃራሪ ገጽታ ያለው ግንኙነት መለያ ነቁጥ ነበር:: ወዳጅነታቸው ፍጹም የተረጋገጠ በመሰለ ማግስት ማሳረጊያው የዐድዋ ጦርነት የሆነው መቃቃር ጀመረ::

የውጫሌ ውል ድንገት የመጣ ነገር አልነበረም:: ምኒልክና ኢጣልያ ቀደም ሲል የውጫሌ ጥንስስ ሊባሉ የሚችሉ ሁለት የወዳጅነት ውሎች ተፈራርመዋል:: የመጀመሪያው በግንቦት 14፣ 1875 ሲሆን አንቀፆቹም የቆንስላ ልውውጥን፣ ነፃ ንግድን፣ የሁለቱ አገር ዜጎች በሌላው አገር በነፃ መንቀሳቀስንና በሁለቱም አገር በነፃ የሃይማኖት ስብከት ማካሄድን ያረጋገጡ ነበሩ:: እዚህ ላይ ልናስተውል የሚገባን አንድ ነገር እነዚህ መብቶች ለሁለቱም ዜጎች የተረጋገጡ ይምሰሉ እንጂ በነበረው ሁኔታ ተጠቃሚዎቹ ጣልያኖች ብቻ እንደሚሆኑ ነው:: በዚያን ዘመን ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ሮማና ሚላኖ ሄደው ሲነግዱ፣ ቀሳውስቱም በምድረ ቫቲካን ሲሰብኩ ከቶም የማይታለም ነበርና:: የዚህ የ1875 ውል ሁለት ዐቢይ አንቀጾች 12ኛውና 13ኛው ነበሩ:: የመጀመሪያው የኢጣልያ ዜጎችን ከኢትዮጵያ ሕግ ክልል ውጪ አደረጋቸው:: ይህም በ1900 ምኒልክ ከፈረንሳዩ አምባሳደር ክሎቡኮውስኪ ጋር የተፈራረመውና ፈረንጆችን ከኢትዮጵያ ሕጋዊ ሥልጣን በላይ ያደረጋቸው ውል መቅድም ነበር:: የሸዋ መንግሥት የውጭ ግንኙነቱን በኢጣልያ አማካይነት ማድረግ እንደሚችል የገለጸው አንቀጽ 13 ደግሞ የመዘዘኛው የወጫሌ ውል አንቀጽ 17 መቅድም ነበር ማለት ይቻላል::

ምኒልክና አንቶኔሊ ሁለተኛውን ውል የተዋዋሉት ደግሞ በጥቅምት 1880 ጣልያኖች በዶጋሊ ጦርነት ተሸንፈው የበቀል እርምጃ ለመውሰድ በሚዘጋጁበት ወቅት ነው:: ጣልያኖች ከአፄ ዮሐንስ ጋር ጦርነት መግጠማቸው ቁርጥ እየሆነ ሲመጣ ምኒልክ ሲሆን ሲሆን አጋር፣ ቢያንስ ግን ገለልተኛ እንዲሆንላቸው ፈለጉ:: ምኒልክ ገለልተኛ ለመሆን በመስማማቱ አምስት ሺ ሬሚንግተን ጠመንጃ ሊሰጡት ተስማሙ:: በተጨማሪም ሁለቱም ወገኖች




የይስሙላ ቃል ገቡ፤ ምኒልክ ጣልያኖች የሰጡትን መሣሪያ በነሱ ላየ ላያዞር፣ ጣልያኖችም የኢትዮጵያን ግዛት ላይነኩ::

እነዚህ ቃል ኪዳኖች ምን ያህል ለይስሙላ እንደሆኑ ሁለት ዓመት ሳይሞላ የተፈራረሙት የውጫሌ ውል ሊያሳይ ነው:: በውሉ ሦስተኛ አንቀጽ አማካይነት ጣልያኖች ከዛሬይቱ ኤርትራ ቆላማ ክፍል አብዛኛውንና ከደጋውም ጥቂቱን በጅ አደረጉ:: ይህም አልበቃ ብሏቸው ከጥቂት ወራት በኋላ ሮማ ላይ ኢጣልያን ይጎበኝ ከነበረው ከደጃች (ኋላ ራስ) መኰንን ጋር በተፈራረሙት ውል የይርጋ አንቀጽ አስገብተው የግዛት ክፍላቸውን እስከ መረብ ወንዝ ለማስፋት ቻሉ::

እንዲህ ዳር ዳር ካሉ በኋላ ጣልያኖች በውጫሌ ውል አንቀጽ 17 የጣልያንኛ ትርጓሜው አማካይነት ምኒልክ የውጭ ግንኙነቱን በሙሉ በኢጣልያ በኩል ማድረግ ይገባዋል ሲሉ የመጨረሻ የቅኝ ግዛት ዕቅዳቸውን ገሃድ አወጡት:: የውሉ የአማርኛ ቃል ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይህን ግንኙነት በኢጣልያ አጋዥነት ማድረግ ይቻላቸዋል በማለት ምርጫው የምኒልክ መሆኑን በግልጽ ያስረዳል:: እንግዲህ የጣልያንኛው ቃል ኢትዮጵያን የኢጣልያ ጥገኛ ሲያደርጋት፣ በአማርኛው ቃልና በምኒልክ ሐሳብ ግን የኢጣልያ ሚና ከፖስታ አቀባይነት እጅግም ከፍ ያላለ ነበር:: ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ እንኳ የኢጣልያን ጥገኝነት ለመቀበል ይቃጣዋል ብሎ መገመት ያዳግታል:: ከፍተኛውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ከተቀዳጀ በኋላ ግን ምን ቀረኝ ብሎ ራሱን የባዕድ ተገዥ ያደርጋል? ይህ የምኒልክ የኃይል ሚዛን መሰወጥ ነው የኢጣልያን የቅኝ ግዛት ሐሳብ በፅንሱ ያጨናገፈው::

ጣልያኖች ትንሽ የሚያጽናና ሁኔታ ያገኙት በውጭው ዓለም ነው:: ከሩሲያ በስተቀር ኃያላኑ መንግሥታት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የውጫሌ ውል ሰጥቶኛል የምትለውን ሥልጣን ዕውቅና ለመስጠት ዝግጁ ነበሩ:: ይህም አያስገርምም:: በዚያን ዘመን አንድ የአፍሪቃ መሪ የአንድ የአውሮጳ መንግሥት ጥገኛ ለመሆን መስማማቱ የተለመደ ነገር ነበር:: እንግሊዝ እንደሆን ለራሷ ጥቅም ስትል ኢጣልያን ማደፋፈር ከጀመረች ውላ ስላደረች ይህን ዕውቅና ለመስጠት ዐይኗንም አላሸች:: ይሁን እንጂ የማታ ማታ ነገሩ እልባት የሚያገኘው በኢትዮጵያ ምድር እንጂ በአውሮጳ እንዳልሆነ ጣልያኖች በሚገባ ተረድተው ይህን ውጤት ለማግኘት ጣምራ ግን ተፃራሪ የሆኑ ፖሊሲዎች ማካሄድ ጀመሩ:: ባጭር አነጋገር በሰሜን ቡርቦራ፣ በደቡብ ዲፕሎማሲ፤ በሰሜን ኢትዮጵያ የትግሬን መሳፍንት በምኒልክ ላይ ማሸፈት፣ በደቡብ ምኒልክ አንቀጽ 17ን በጣልያንኛ አተረጓጐሙ እንዲቀበል ማግባባት:: አንቶኔሊን ጨምሮ የተለያዩ የጣልያን መልእክተኞች ምኒልክን ለማሳመን ወደ ሸዋ ይመላለሱ ጀመር:: ዳሩ ግን የነበራቸው ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ምኒልክ በየካቲት 1885 የውጫሌን ውል በይፋ ሲሽረው ፈጽሞ ጨለመ::




3. የ19ኛው‑ና የ20ኛው መቶ ዓመት ዐበይት የጦር ዐውድማዎች



በሰሜን በኩል የኤርትራ አገረ ገዥ በሆነው በአንቶኒዮ ባልዲሴራ ይቀነባበር የነበረው የቡርቦራ ፖሊሲ ሁለት ገጽታዎች ነበሩት፤ ድንበር መግፋትና የትግሬ መሳፍንትን ማሸፈት:: በኅዳር 30፣ 1884 መሳፍንቱ በራስ መንገሻ ዮሐንስ እየተመሩ ከጣልያኖች ጋር የመረብ ቃል ኪዳን እየተባለ የሚታወቀውን የመተጋገዝ ቃለ መሐላ ሲፈጽሙ የማሸፈቱ ተግባር ግቡን የመታ መሰለ:: ግን ዘለቄታ አልነበረውም:: መጀመሪያ በአካለ ጉዛዩ መሪ በደጃች ባሕታ ሐጎስ የሚመራ የገበሬዎች አመፅ የኢጣልያን ቅኝ አስተዳደር ሲያናውጥ ለቡርቦራው ፖሊሲ የሞት ቃጭል ነበር:: ጣልያኖች ከዚህ ገና ሳያገግሙ የምኒልክ ባላንጣ ይሆናል ብለው እጅግ የተመኩበት ራስ መንገሻ በታላቅ ሥነ ሥርዓት እንጦጦ ድረስ መጥቶ ለምኒልክ ታማኝነቱን ከገለጸ በኋላ ከጣልያኖች ጋር ጦርነት ገጠመ:: ምንም እንኳ ድሉ የጣልያኖች ቢሆንም በመንገሻና በጣልያኖች መካከል የተደረጉት የሰናፌና የኮአቲት ጦርነቶች የታላቁ የዐድዋ ጦርነት ማሟሻ ነበሩ:: በዐድዋ ዘመቻ ወቅት ራስ ስብሐት አረጋዊና ደጃች ሐጎስ ተፈሪ የመንገሻን አርአያ ተከትለው ወደ ምኒልክ ወገን ሲዞሩ የጣልያኖች የቡርቦራ ፖሊሲ እርቃኑን ቀረ::

## የዐድዋ ዘመቻ

እንግዲህ ዲፕሎማሲም ቡርቦራም እንዳልሠራላቸው ሲገነዘቡ ጣልያኖች የቀራቸው አማራጭ ጦርነት ሆነ:: በመስከረም 1888 ያን አማራጭ ወስደው፣ መረብን ተሻግረው ትግራይን ወረሩ:: በሚከተሉት ሳምንታትም ምኒልክ የክተት ዐዋጅ ዐውጆ መቶ ሺ የሚያህል ሠራዊት ከባለቤቱ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር እየመራ ወደ ሰሜን ዘመተ:: የምኒልክ ጦር በቁጥሩ ብዛት ብቻ ሳይሆን ድፍን ኢትዮጵያን የወከለ በመሆኑም ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነበር:: ለንጉሠ ነገሥቱ ነፃነትና የአገር ድንበርን የማስከበር ጥሪ ጦር ያልላከ የአገሪቱ ክፍል አልነበረም::

በኢጣልያና በኢትዮጵያ ጦር መካከል የመጀመሪያው ውጊያ አምባ አላጌ ላይ በኅዳር 29፣ 1888 ሆነ:: ይህን የተፈጥሮ ምሽግ በሻለቃ ቶዜሊ የሚመራ የኢጣልያ ጦር ቀደም ብሎ ተቆጣጥሮት ነበር:: የኢትዮጵያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ራስ መኰንን ጣልያኖቹ የያዙትን ቦታ በሰላም ለቀው እንዲወጡ በመደራደር ላይ እያለ፣ የግንባር ቀደሙ ጦር መሪ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ የራሱ ሕመም ሳይገታው፣ ሠራዊቱን ሊታሰብ በማይችል ድፍረትና ወኔ እየመራ የአምባ አላጌን አቀበት እየተዋጋ ወጥቶ የኢጣልያን ጦር ድል ለማድረግ በቃ:: ቶዜሊ ከሞቱት መሀል አንዱ ሲሆን የቀረው የኢጣልያ ጦር ተበተነ::

አምባ አላጌ አጭርና ድራማ የበዛበት ውጊያ የሆነውን ያህል የዘመቻው ሁለተኛ ምዕራፍ የሆነው የመቀሌ ከበባ ደግሞ የተንዛዛና ብዙም ውጤት ያልታየበት ነበር:: ከአምባ አላጌ ሸሽተው ያመለጡትን ጨምሮ ትልቅ የኢጣልያ ጦር አዲስ በተሠራው የእንዳ ኢየሱስ ምሽግ ከትሞ ነበር:: በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር በቦታው እንደደረሰ ምሽጉን ለማጥቃት ሞክሮ

**የማይበገር መሆኑን ከተረዳ በኋላ የጠላትን ጦር ከቦ ስንቅና የድጋፍ ጦር እንዳይደርስ በማገዱ ቀረጠ። በተለይም ጣልያኖች ቀድሞ ውሀ ያገኙበት የነበረው ምንጭ በእቴጌ ጣይቱ ጦር ከተዘጋባቸው በኋላ በጥም ተሠቃዩ። የኢጣሊያን ጦር በመጨረሻ የፈታውም ይኸው ነው ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ በምኒልክና በኢጣልያው ልዑክ ፌልተር መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት የጣልያን ጦር ሳይበተንና ትጥቁን ሳይፈታ፣ ይባስ ብሎ ለጓዙ የሚሆን በቅሎና አጋሰስ ተሰጥቶት በሰላም ምሽጉን ለቆ ለመውጣት ቻለ። ምኒልክ በዚህ ለብዙ ኢትዮጵያውያንም እንግዳ ሆኖ በታየ ድርጊት የጣልያኖችን ልብ በልቶ ጠቡን በሰላም ለመጨረስ ያሰበ ይመስላል። ዳሩ ግን አልተሳካለትም።**



**2.15 የትግራዩ ገገር፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ**

**ጣልያኖች ከጦርነት ዓላማቸው ንቅንቅም አላሉም። የያዙትን ቦታ ከመልቀቅ ይልቅ የማይጥም የሰላም ቅድመ ሁኔታዎች መደርደራቸውን ቀጠሉ። በዚህ ሁኔታ የመጨረሻው የዐድዋ ጦርነት የማይቀር ነገር ሆነ። ምኒልክ**



ጦሩን ወደ ዐድዋ መርቶ ጣልያኖች ከአዲግራትና ከእንጢቾ ምሽጋቸው ወጥተውጦርነት የሚገጥሙበትን ቀን በናፍቆት መጠባበቅ ጀመረ። በናፍቆት የሚጠብቅበት ምክንያት የሠራዊቱ የስንቅ ሁኔታ አሳሳቢ ስለነበረ በስንቅ እጦት ሠራዊቱ እንዳይበተንበት ስለሠጋ ነው። ስለዚህም የኢጣልያው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ኦሬስቴ ባራቲዬሪ የካቲት 23 በማለዳ ድንገተኛ አደጋ ለመጣል ጦሩን ማንቀሳቀሱ ሲታወቅ በኢትዮጵያ የጦር ካምፕ ከፍተኛ እፎይታ ተሰማ። ባራቲዬሪ ይኸን እንቅስቃሴ ያደረገው ዕለቱ አንድም እሑድ፣ አንድም ደግሞ ዕለተ ጊዮርጊስ ስለሆነ፣ ኢትዮጵያውያን ድርብ ሰንበት ሲያከብሩ ድንገት አገኛቸዋለሁ በሚል ግምት ነው። በዚህ ግምት እንዲገፋበት ያደረጉትም ለምኒልክ መረጃ በማቀበል፣ ለጣልያኖች ደግሞ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት፣ ለዐድዋ ድል አስተዋፅኦ ያደረጉት እንደነአውዓሎም ያሉ አርበኞች ናቸው።

በዚህ ታሪካዊ ፍልሚያ የኢትዮጵያ የጦር አበጋዞች ራስ ሚካኤል፣ ራስ መኰንን፣ ራስ መንገሻና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሲሆኑ፣ በጣልያን በኩል ደግሞ የነበሩት የጦር ጄኔራሎች ጁሴፔ ኤሌና፣ ቪቶርዮ ዳቦርሚዳ፣ ጁሴፔ አሪሞንዲና ማቴኦ አልቤርቶኒ ነበሩ። በሦስት መሥመር ያጠቃ የነበረው የኢጣልያ ጦር እርምጃዎቹን ማቀነጃጀት ሲሳነው ነው የኢጣልያ ሽንፈት የጀመረው። በተለይም በአልቤርቶኒ የሚመራው ብርጌድ በተሳሳተ የካርታ ንባብ ምክንያት ከሁለቱ ሌሎች ብርጌዶች ተነጥሎ ስለተገኘ ለተባበረው የኢትዮጵያ ጦር ጥቃት ተዳረገ። አልቤርቶኒን ለማዳን ሲገሰግስ የነበረው የዳቦርሚዳ ጦርም መንገድ በመሳቱ እንዲሁ በባዶ ሜዳ ቀረ። በትልቅ የአገር ፍቅር ስሜት ይዋጋ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በስልትና በቅንጅትም ከጠላት ልቆ በመገኘቱ ምንም እንኳ ብዙ ሰው ቢያልቅም በጠላት ላይ የማያወላውል ድል ተቀዳጀ። እኩለ ቀን ላይ ጦርነቱ አከተመ። የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ሕልም ዐድዋ ሜዳ ላይ ሲቀበር፣ ኢትዮጵያ በነፃነት መኖሯ ተረጋገጠ።